




Noble Printing Press

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
# ሰበር ሰሚ ችሎት



## ቅጽ 4

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሚያዝያ 2001 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
# ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔዎች

## ቅፅ 4

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

<u>አዲስ አበባ</u>



## <u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መልዕክት</u>

የዳኝነት አካሉን አሰራር ግልጽነት እና ተጠያቂነት ለማረጋገጥ ሲባል እንዲሁም ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ወጥነት ባለው የሕግ ትርጉም ችሎቶቹ የሰጧቸውን ውሳኔዎች ከአሁን ቀደም በተለያዩ እትሞች አሳትሞ ማሰራጨቱ የሚታወቅ ነው፡፡ ይህ የአሁኑ እትምም በአንድ በኩል የዚሁ ሂደት ቀጣይ ክንውን ሆኖ መታየት የሚችል ሲሆን በሌላ በኩል ለእትሙ መውጣት ከፍ ሲል ከተመለከቱት ምክንያቶች ሌላ አብይ ምክንያት አለው፡፡ ይኸውም የፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ወጥነት ባለው የሕግ ትርጉም ላይ የተመሠረተ ለማድረግ ሲባል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች ተሰይመው በሚሰጠው ውሳኔ የሰጠው የህግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ ፍርድ ቤት ዘንድ አስገዳጅነት እንደሚኖረውና አስገዳጅ የህግ ትርጉም የያዙ ውሳኔዎችን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አሳትሞ እንደሚያሰራጭ በአዋጅ ቁ.454/97 መደንገጉ ነው፡፡

በዚህ እትም የተካተቱት ውሳኔዎች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የሰጣቸውና አስገዳጁ የህግ ትርጉም የያዙ ውሳኔዎች ናቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቀጣይነትም ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጣቸውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የያዙ ውሳኔዎችን በተከታታይነት አሳትሞ የሚያሰራጭ ሲሆን ዳኞች፣ ሌሎች የህግ ባለሙያዎች እንዲሁም የህግ ተማሪዎች ለአዋጁ ተፈጻሚነት የበኩላችሁን ሚና እንድትወጡ እየጠየቅኩ ለግቡ መሳካት ይጠቅማሉ የምትሏቸውን ሃሳቦች እንድለግሱን ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡

**ከማል በድሪ**

**የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት**

# ማውጫ

## አሰሪና ሠራተኛ


1. ለተወሰነና ላልተወሰነ ጊዜ ስለማደረግ የስራ ውል /የሰ.መ.ቁ. 20885/ የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ገቢሳ የማነ/
2. የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን /የሰ/መ/ቁ/ 15533/ የኢት/ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ አዱኛ ገመዳ/
3. ወደ ሥራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሰራተኛ የሚከፈለው ውዝፍ ደሞዝ /የሰ/መ/ቁ/ 21730/ ወ/ሮ ፍሬህይወት እርቄ እና የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን/
4. የህመም ፈቃድ ጊዜ አቆጣጠር /የሰ.መ.ቁ. 21119/ ቃሊቲ ምግብ አክሲዮን ማህበር እና ማስተዋል ጫኔ/
5. የስራ ውልን ስለማቋረጥ /የሰ.መ.ቁ. 21961/ አቶ ግርማ ነጋሽ እና ቢግ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር/
6. የስራ ውል በተቋረጠ ጊዜ ስራ ላልተሰራበት ውዝፍ ደሞዝ የሚከፈልበት ስላለመሆኑ /የሰ.መ.ቁ. 20457/ የኢት/ንግድ ባንክ እና ወ/ሮ አለሚቱ ሞገስ/
7. ስለ መሠረታዊ የህግ ክርክር /የሰ.መ.ቁ. 24153/ አቶ መንግሥቱ አባተ እና የባህር ትራንዚት ድርጅት/
8. የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን /የሰ.መ.ቁ. 16653/ ግዮን ሆቴሎች ድርጅት እና ወ/ሮ ስለእናት ወርቅነህ/
9. ሰራተኛው በየአመቱ ውሉ እየታደሰ ሲሰራ መቆየቱና የሰራተኛው የቅጥር ውል በጊዜ የተገደበ መሆኑ ብቻ ለተወሰነ ጊዜ ተቀጣሪ የሚያደርገው ስላለመሆኑ /የሰ.መ.ቁ. 25526/ መምህር ጥላሁን አስፋው እና አዲስ ኮሌጅ/


## ውል


1. ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ዳኞች ግልጽ ከሆነው በመራቅ የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር ለመተርጐም ስላለመቻላቸው /የሰ.መ.ቁ. 15662/ የኢት/ልማት ባንክ እና ሐጂ አብዱራህማን ቴሊሳ/
2. ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የተገናኙ ተከሳሾች በአንድ ላይ በተከሰሱ ጊዜ አንዱ ተከሳሽ የሚያነሳውን የይርጋ መቃወሚያ በሌሎች ላይ ስላለው ውጤት /የሰ.መ.ቁ. 19081/ አቶ ዓሊ ቃሴብ አህመድ እና እነ አቶ ሚሊዮን ተፈራ/





3. የኪራይ ውል በአከራይና በተከራይ መካከል የሚደረግ ስለመሆኑ /የሰ.መ.ቁ. 23320/ አቶ ገብሩ አብሴ እና እነ አቶ ሁሴን አብዱረህማን ወራሾች/
4. ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ዳኞች ግልጽ ከሆነው በመራቅ የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር ለመተርጐም ስላለመቻላቸው /የሰ.መ.ቁ. 14493/ የኢት/ልማት ባንክ እና አቶ ሚደቅሳ ቱለማ/
5. የውል አብዛኛው ግዴታ በተፈፀመ ጊዜ የተወሰነ ቀሪ ገንዘብ አለመከፈሉ ውሉን ለማፍረስ የሚያበቃ መሰረታዊ የሆነ የግዴታ መጣስ የሚያሰኝ ምክንያት ስላለመሆኑ /የሰ.መ.ቁ. 18768/ ወ/ሮ አለሚቱ አግዛቸው እና እነ ወ/ሮ ዝናሽ ሀይሌ/
6. የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በአዋዋይ ወይም በፍርድ ቤት ፊት መደረግ ያለበት ስለመሆኑ የሰ/መ/ቁ 21448/ ወ/ሮ ጉርፌ ወርቀነህ እና እነ ወ/ሮ አበራሽ ዱባርጌ


## የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ


1. በአፈጻጸም ጉዳይ በስህተት በፍ/ባለመብት እጅ ስለገባ የከተማ መሬት ይዞታ /የሰ.መ.ቁ. 15557/ ወ/ሮ አልማዝ ዓለማየሁና አቶ ብርሃኑ ተሊላ/
2. የወጪና ኪሣራ አወሳሰን /የሰ.መ.ቁ. 22260/ የጎንደር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ገደሪፍ ውብነህ/
3. ጉድለት ያለበት ሃራጅ ቀሪ ሲደረግ ሻጭና ገዢን ወደነበሩበት ለመመለስ ስላለመቻል /የሰ.መ.ቁ. 17984/ የጌዲዮ ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት እና ወ/ሮ አስናቀች ታደሰ/
4. አንድ ፍርድ ተፈጸመ ሲባል የሚገባው ለፍርድ ቤቱ ገቢ የተደረገ ገንዘብ ለፍርድ ባለመብቱ ሲደርሰው ስለመሆኑ /የሰ.መ.ቁ. 19205/ አቶ ሽኩር ሲራጅ እና አቶ ሙላት ካሳ/


## ንብረት


1. አከራካሪ የሆነው ቤት የግልም ሆነ የጋራ ቤቱ ያረፈበት ቦታ የመንግሥት በመሆኑ ከቤቱ ተነጥሎ እንዲገወትና አስፈላጊም ከሆነ

እንዲሸጥ የሚያደርግ ውሣኔ መሬት የመንግሥት ለማድረግ የወጣውን ሕግ የሚፃረር ስለመሆኑ /የሰ.መ.ቁ. 19479/ ወ/ሮ አመለወርቅ ገሰቱ ወራሾች እና እነ አቶ ቢሻው አሻሜ/

2. የሽያጭ ውል በሶስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረው በተዋዋዮች ላይ ውላቸውን በመዝገቡ እንዲፃፍ ከማድረግ የዘለለ ግዴታ የማይጥልባቸው ስለመሆኑ /የሰ.መ.ቁ. 16109/ አቶ ከበደ አርጋው እና የኢት/ንግድ ባንክ/
3. ለረጅም አመታት በመንግሥት እጅ የነበረ ቤትን በተመለከተ ባለቤት ነኝ የሚል ወገን ቤቱ በአዋጅ ቁ. 47/67 የተፈቀደለት መሆኑን ወይም ያለአግባብ ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል ጥያቄውን አቅርቦ ውሳኔ አግኝቶ ባለመብት ስለመሆኑ ማስረዳት ያለበት ስለመሆኑ /የሰ.መ.ቁ. 14094/ የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና የአቶ ሰለሞን ወረዳ ወራሽ/

### ጋብቻ

1. ጋብቻ በአንደኛው ተጋቢ ሞት ምክንያት በፈረሰ ጊዜ የጋራም ሆነ የግል ንብረት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መጠየቅ እንዳለበት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677 መሠረት በቁ. 1845 ላይ የተቀመጠው ይርጋ ተፈጻሚ ስለመሆኑ /የሰ.መ.ቁ. 17937/ ወ/ሮ ድንቂ ተድላ እና እነ አቶ አባተ ጫኔ/
2. ስለ ጋብቻ መፍረስ /የሰ.መ.ቁ. 20938/ ወ/ሮ ሸዋዬ ተሰማ እና ወ/ሮ ሣራ ልነጋነ/

### ልጅነት ይታወቅልኝ

ልጅነትን ስለማስረዳት /የሰ.መ.ቁ. 22243/ እነ ወ/ሮ ደሐብ ሰኢድ እና አቶ አብርሃም ካሳ/

### ውርስ

1. ኑዛዜ ህጋዊ ነው መባሉ ሌሎች ሰዎች በሰነዱ ላይ ተቃውሞ ካላቸው ጉዳዩ በዳኝነት መታየትን የሚከለክል ስላለመሆኑ /የሰ.መ.ቁ. 17058/ አቶ አንበሶ ወ/ገብርአል እና አቶ መሣይ መኮንን/
2. የኑዛዜ እያንዳንዱ መስፈርት መሟላት መመዘን የሚገባው የኑዛዜውን አጠቃላይ ሁኔታ በመመልከትና ተናዛዡም ሆነ ምስክሮች /እማኞች/ በኑዛዜው ባሰፈሩት



ቃላትና ሃረጎች ሊሰጡ የሚችለውን ትርጉም ግምት ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ /የሰ.መ.ቁ. 22172/ አቶ እንደሻው በቀለ እና እነ ወ/ት አይናለም ያለው/

### ኢንሹራንስ

መድን ሰጪ የካሳን ክፍያ በተመለከተ በመድን ውሉ ላይ ከተመለከተው በላይ ሊጠየቅ ስላለመቻሉ /የሰ.መ.ቁ. 22162/ አፍሪካ ኢንሹራንስ እና አቶ ብስራት ጎላ/

### የአስተዳደር ህግ

1. የጉምሩክ ባለስልጣን ሰራተኞች የፌዴራል ገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚተዳደሩ ስለመሆናቸው /የሰ.መ.ቁ. 23339/ የኢት/ጉምሩክ ባለሥልጣን እና እነ አበሮ ኢ.ርጋኖ/
2. ሚኒስቴር መ/ቤቶች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የፈፀሙትን ስህተት ማረምና ማስተካከል በጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣን ስር የሚወድቅ ስለመሆኑ /የሰ.መ.ቁ. 16195/ የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና እነ ልዕልት ተናኘወርቅ ኃ/ስላሴ/
3. የጉምሩክ ባለስልጣን በኮንትሮባንድ ወደ አገር የሚገቡትን ወይም ከአገር የሚወጡትን እቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠር፣ የሚንቀሳቀሱ እቃዎችንና ማጓጓዣዎችን የመያዝና አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ስልጣን የተሰጠው ስለመሆኑ /የሰ.መ.ቁ. 22317/ የምስራቅ ጉምሩክ የሐረር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ እና አቶ አብዱ አሉ አዩ/

### ወንጀል

ጥብቅና ፈቃድ ከተሰረዘ በኋላ የጥብቅና ስራ እሰራለሁ ብሎ ገንዘብ መቀበል የማታለል ወንጀል ስለመሆኑ /የሰ.መ.ቁ. 12025/ አቶ ምናሴ አልማውና ዓቃቤ ህግ/

የሰ/መ/ቁ/ 20885

ጥር 3/1999

ዳኞች፡- አቶ ከማል በድሪ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ
አቶ መስፍን እቁበዮናስ
ወ/ት ሒሩት መለሠ

አመልካች፡- የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን

ተጠሪ፡- አቶ ገቢሣ የማነ

*የስራ ክርክር - ለተወሰነና ላልተወሰነ ጊዜ የሚደረግ የስራ ውል - የስራ ውል መቋረጥ - አዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 9፣ 10*

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪው ከስራ የተሰናበቱት በህገ ወጥ መንገድ ስለሆነ ወደ ስራ ሊመለሱ ይገባል ሲል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

**ውሣኔ፡ -** የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 9 በአንድ አሰሪና ሠራተኛ መካከል የተደረገ የስራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ እንደሆነ ግምት ቢወስድም አሰሪ ይህንን ግምት አንቀጽ 10 ላይ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች በማስረዳት ማፍረስ ይችላል፡፡
2. አሰሪው ከሰራተኛው ጋር በጽሁፍም ሆነ በቃል ያደረገው ውል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ መደረጉን የሚያሳይ ጥቅል ሃሳብ ማስቀመጡ ብቻውን ውሉ በአንቀጽ 10 መሠረት የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ በቂ አይሆንም፡፡
3. በአሰሪና ሠራተኛ መካከል የተደረገውን ውል ለመተርጐም ተዋዋዮች ውሉን ባደረጉበት ጊዜ የነበራቸውን የሃሳብ አንድነት መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡



የሰ/መ/ቁ/ 20885

ጥር 3/1999

ዳኞች፡- 1. አቶ ከማል በድሪ
2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
3. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ
4. አቶ መስፍን እቁበዮናስ
5. ወ/ት ሒሩት መለሠ

አመልካች፡- የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን

ተጠሪ፡- አቶ ገቢሣ የማነ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ የተደረገን የሥራ ውል የሚመለከት ነው፡፡

ተጠሪ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ከሥራ ያላግባብ ያሠናበታቸው መሆኑን በመግለጽ ወደ ሥራ እንዲመልሣቸው ክስ ያቀርባሉ፡፡ አመልካች ደግሞ ወቅታዊ ሥራ ለማከናወን ለተወሠነ ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኛ በመሆናቸው የተቀጠሩበት ሥራና ጊዜ ሲያበቃ መሠናበታቸው ተገቢ ነው በማለት ይከራከራል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው ፍ/ቤትም ሥንብቱ ሕገ ወጥ ነው በማለት ተጠሪ ወደ ሥራ እንዲመለሱ ይወስናል፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ያፀናል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የሥራ ውል የተወሰነ ሥራ ለመስራት የተደረገ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ጉዳዩን ለሠበር ችሎት በማስቀረቡ ግራ ቀኙ ክርራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠው ውሉ የተደረገው ወቅታዊ ሥራን ለማከናወን በመሆኑ የተቀጠሩበት ሥራና ጊዜ በማለቁ መሆኑን ገልጿል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የተቀጠሩት ላልተወሰነ ጊዜ ነው ወይስ ለተወሰነ ሥራና ለተወሰነ ጊዜ ነው የሚለው ሊታይ የሚገባው ነጥብ ነው፡፡

የሥራ ውል ስለሚቆይበት ጊዜ የሚመለከተው የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 9 በአንድ አሠሪና ሠራተኛ የሚደረገው የሥራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ መሆኑን የሕግ ግምት ይወስዳል፡፡ ሆኖም ይህ የሕግ ግምት ሊፈርስ የሚችልባቸው ሁኔታዎች ደግሞ በአንቀጽ 10 ሥር

ተመልክተዋል፡፡ በመሆኑም አንድ አሠሪ ሠራተኛው የተቀጠረው ላልተወሰነ ጊዜ ሣይሆን ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ መሆኑን በማስረዳት በአንቀጽ 9 ሥር የተመለከተውን የሕግ ግምት ማፍረስ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ አሠሪው ከሠራተኛው ጋር በጽሁፍም ሆነ በቃል ያደረገው ውል ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ መደረጉን የሚያሣይ ጥቅል ሃሣብ ማስቀመጡ ብቻውን ውሉ በአንቀጽ 10 መሠረት የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ በቂ አይሆንም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ውሉ በአንቀጽ 10 ሥር በተዘረዘሩት ሁኔታዎች በአግባቡ መደረጉን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በሁለቱ መሃከል የተደረገውን ውል ለመተርጎምም ተዋዋዮቹ ውሉን ባደረጉበት ወቅት የነበራቸው የሃሣብ አንድነት መመርመር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ የተደረገን የሥራ ውል በተመለከተ ይህ ችሎት የሰጠውን የሕግ ትንታኔ ከመ/ቁ 11924 መመልከት ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ወቅታዊ ሥራ ለማከናወን እ.ኤ.አ. ከ14/4/2000-15/10/2000 የተቀጠሩ መሆኑን በሁለቱ መሃከል የተደረገው የጽሁፍ ውል ያመለክታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ የተቀጠሩት ሠልጣኞች ሥልጠና አጠናቀው እስኪወጡ የማሠልጠኛው ምግብ ቤት ምግብ አዘጋጅ ሆነው እንዲሠሩ መሆኑን በአመልካች በኩል በሥር ጀምሮ የቀረበውን ክርክር ተጠሪ በዚህ ሁኔታ አልተቀጠርኩም በማለት ክደው አልተከራከሩም፡፡ ማሠልጠኛው ወደ ኮሌጅ ያደገ በመሆኑ ሥራው ቀጣይነት ስላለው ልሰናበት አይገባም በማለት ነው የሚከራከሩት፡፡ ነገር ግን አንድ አሠሪ ሥራው ቀጣይነት ቢኖረውም እንኳን የሥራ ብዛትን ለማቃለል፣ እየተቋረጠ የሚሠራ ሥራ ወይም ቋሚ ሣይሆን አንዳንዴ የሚሠራን ሥራ ለማሠራት ሠራተኛን ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ ለመቅጠር የሚችል መሆኑ በአዋጅ አንቀጽ 10 ሥር ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም አመልካች ተጠሪን የቀጠረው በወቅቱ ለነበሩት ሠልጣኞች ምግብ እንዲያዘጋጅ በመሆኑና ሠልጣኞቹ ሥልጠናውን ጨርሰው ስለወጡና ተጠሪ የተቀጠሩበት ወቅታዊ ሥራና ጊዜ ሲጠናቀቅ መሠናበታቸው ሕጉን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ስለዚህም የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ከሥራ የተሰናበቱበት ሁኔታ ከሕግ ውጪ ነው በማለት የደረሱበት መደምደሚያ የሕግ ሥህተት ያለበት ነው፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 1774 በ14/06/97 እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 37579 በ23/10/97 የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

2/ ተጠሪ ከሥራ የተሰናበቱት በአግባቡ በመሆኑ ወደ ሥራ እንዲመለሱ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡

3/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡



የሰበር መ/ቁ.15531

የካቲት 6/99 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

” አሰግድ ጋሻው

” መስፍን ዕቁበዮናስ

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- የኢት/ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን

መልስ ሰጭ፡- አቶ አዱኛ ገመዳ

*የስራ ክርክር - የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን የወል የስራ ክርክር - የግል የሥራ ክርክር - የግል የስራ ክርክር - የሰ/መ/ቁ/18180*

ተጠሪው ከደረጃዬ ዝቅ ተደርጌያለሁ ብለው በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ያቀረቡትን ክስ ቦርዱ የማየት ስልጣን አለው ሲሉ የምዕ/ኦሮሚያ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ በመቃወም የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የምዕ/ኦሮሚያ የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የማየት ስልጣን የተሰጠው የወል የስራ ክርክር ጉዳዮችን ነው፡፡
2. አንድ የሥራ ክርክር የወል የስራ ክርክር ነው የሚባለው ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡
3. አንድ የስራ ክርክር የግል የስራ ክርክር ጉዳይ ነው የሚባለው የክርክሩ ውጤት በተከራካሪው ሰራተኛ (ሰራተኞች) ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀርብ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡
4. ከደረጃዬ ዝቅ ተደርጌያለሁ ተብሎ የሚቀርብ ክስ የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት የሚያስከትል አይደለም፡፡

የሰበር መ/ቁ.15531

የካቲት 6/99 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. ” አሰግድ ጋሻው
3. ” መስፍን ዕቁበዮናስ
4. ወ/ት ሂሩት መለሠ
5. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- የኢት/ኤሌክትሪክ ኃ/ኩ/ነ/ፈጅ እመቤት ለማ ቀረበች

መልስ ሰጭ፡- አቶ አዱኛ ገመዳ ቀረበ

## ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ ለሰበር ችሎት የቀረበው ክርክር የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድን ስልጣን የሚመለከት ነው፡፡

በመ/ሰጭ በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ክሱ የቀረበው ደረጃዬ ዝቅ ተደርጓል በሚል ነው፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ክሱን ለማየት ስልጣን አለው በማለት የተሰጠ ነው፡፡ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለዚህ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት መ/ሰጭ መልሱን አቅርቧል፡፡

ችሎቱም በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የሚታዩ የስራ ክርክሮች ምን አይነቶች ናቸው የሚለውን የሕግ ነጥብ መሰረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበለትን ውሣኔ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡

ይህ ችሎት በመ/ቁ. 18180 አግባብነት ያላቸውን የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ድንጋጌዎች በመተርጎም የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የማየት ስልጣን የተሰጠው የወል የስራ ክርክር ጉዳዩችን ነው፣ አንድ የስራ ክርክር የወል የስራ ክርክር ነው የሚባለው ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፤ በአንፃሩ አንድ የስራ ክርክር የወል ሣይሆን የግል የስራ ክርክር ጉዳይ ነው የሚባለው የክርክሩ ውጤት በተከራካሪው ሰራተኛ (ሰራተኞች) ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀርብ ሆኖ ሲገኝ ነው በማለት የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

መ/ሰጭ በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ደረጃዬ ዝቅ ተደርጓል በሚል ያቀረበው ክስ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ውጤት የሚያስከትል ባለመሆኑ የወል የስራ ክርክር አይደለም በመሆኑም ጉዳዩን ለማየት የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ስልጣን ያለው ባለመሆኑ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

የምዕ/ኦሮሚያ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ በመ.ቁ. ታህሣሥ 25/1995 የሰጠው ውሣኔና ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 00692 በ21/7/96 የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡

- ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡



የሰ/መ/ቁ. 21730

11/7/99

ዳኞች፡- 1. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ጌታቸው ምህረቱ
4. አቶ መስፍን እቁበዮናስ
5. ወ/ት ሒሩት መለሠ

አመልካች፡- ፍሬህይወት እርቄ

ተጠሪ፡- የኢት. ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን

*የስራ ክርክር - ህግ ወጥ የስራ ውል ማቋረጥ - ወደ ስራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሰራተኛ የሚከፈለው ውዝፍ ደሞዝ - አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43(5)*

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃና ከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ከስራ የተሰናበቱት በህገ ወጥ መንገድ ስለሆነ ወደ ሥራ ሊመለሱ ይገባል ሲሉ ቢወስኑም ውዝፍ ደሞዝን በተመለከተ ሳይወስኑ በዝምታ በማለፋቸው የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃና ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡና ውሳኔ ተሻሽሎ ተጠሪ የዘጠኝ ወር ከ23 ቀን ውዝፍ ደሞዝ እንዲከፈላቸውና ሌሎች ወጪና ኪሳራዎች እንደመሰለው እንዲወስን ጉዳዩ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ተወስኗል፡፡

1. የስራ ውሉ በሕገ ወጥ መንገድ የተቋረጠና ወደ ስራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሠራተኛ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት ከስድስት ወር የማይበልጥ ደሞዝ ሊወሰንለት ይገባል፡፡
2. ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ የሰራተኛው መመለስ ውሳኔ ከፀና ከአንድ አመት ያልበለጠ ውዝፍ ደሞዝ ፍርድ ቤቱ ሊወሰንለት ይገባል፡፡

የሰ/መ/ቁ. 21730

11/7/99

**ዳኞች፡-** 1. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

3. አቶ ጌታቸው ምህረቱ

4. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

5. ወ/ት ሒሩት መለሠ

**አመልካች፡-** ፍሬህይወት እርቁ

**ተጠሪ፡-** የኢት. ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን

*መዝረቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡*

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ የቻለው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ግንቦት 19 ቀን 1997 ዓ.ም. 01990 በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ነው፡፡ አመልካች ነሐሴ 16 ቀን 1997 ዓ.ም. ጽፋ ባቀረበችው የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ የሥራ ውሌን ያቋረጠው በሕገወጥ መንገድ መሆኑን ተቀብለው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/5/ ድንጋጌን በመጣስ የውዝፍ ደመወዝ ጥያቄዬን በዝምታ አልፈውታል በማለት አመልክታለች፡፡ ይህ ችሎት የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰኔ 9 ቀን 1998 በዋለው ችሎት አድምጧል፡፡ የአመልካች የሥራ ውል በሕገ ወጥ መንገድ መቋረጡ ከተረጋገጠና ወደ ሥራ እንዲመለስ ከተወሰነ ውዝፍ ደመወዝ ሳይወሰን ማለፉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ይህ ችሎት መርምሯል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/5/ መሠረት የሥራ ውሉ በሕገወጥ መንገድ የተቋረጠና ወደ ሥራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሠራተኛ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሥራ ክርክር ችሎት ከስድስት ወር የሚይበልጥ ውዝፍ ደመወዝ ሊወሰንለት የሚገባ መሆኑን፣ ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ የሠተኛው ወደ ሥራ መመለስ ውሣኔ ከፀና ከአንድ ዓመት ያልበለጠ ውዝፍ ደሞዝ ፍ/ቤቱ ሊወስን እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች የአመልካች የስራ ውል የተቋረጠው በሕገወጥ መንገድ ነው በማለት አመልካች ወደ ሥራ እንድትመለስ ወስነው የጠየቀችው ውዝፍ ደሞዝ እንዲከፈላት አለመወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

ይህ ችሎት የጉዳዩን አጠቃላይ ሁኔታ በመመርመር አመልካች ከሥራ ታግዳ በነበረችበት ጊዜ ያለው ከመጋቢት 23 ቀን 1996 እስከ ነሐሴ 20 ቀን 1996 /የ4 ወር ከ28 ቀናት ደሞዝ/ በተጨማሪ የሥራ ውሉ ከተቋረጠ ከነሐሴ 21 ቀን 1996 ጀምሮ ወደ ምድብ ሥራዋ ተመለሰች እስከተባለበት ጥር 16 ቀን 1997 ዓ.ም. ድረስ ያለው የ4 ወር ከ25 ቀን ደሞዝ እና ሌሎች ወጭና ኪሣራዎች ሊከፈል በሚገባው መጠን ላይ የመሰለውን እንዲወስን መዝገቡ ለፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፍ/ሕ/ቁ. 343/1/ እንዲመለስ ታዟል፡፡

*መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡*



**የሠበር መ/ቁ.** 21119

**መጋቢት** 18/99 **ዓ.ም**

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

” አሰግድ ጋሻው

” መስፍን ዕቁበዮናስ

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** ቃሊቲ ምግብ አክሲዮን ማህበር

**መልስ ሰጭ፡-** ማስተዋል ጫኔ

*የስራ ክርክር - የህመም ፈቃድ - የእረፍት ፈቃድ - የስራ ውል መቋረጥ - አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 85(2)*

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪው ከስራ የተሰናበቱት በህገ ወጥ መንገድ ስለሆነ ወደ ሥራ ሊመለሱ ይገባል ሲል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

**ውሣኔ፡ -** የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1. የህመም ፈቃድ ህመሙ ከደረሰበት የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ባለው የ12 ወር ጊዜ ውስጥ በተከታታይ ወይም በተለያዩ ጊዜያት ቢወስድም በማንኛውም ሁኔታ ከስድስት ወር አይበልጥም፡፡
2. የህመም ፈቃድ ጊዜ አቆጣጠር የስራ ቀናትን ብቻ በመለየት ሳይሆን ህመሙ ከደረሰበት ቀን አንስቶ በመቁጠር በጠቅላላው ከ6 ወር መብለጥ የለበትም፡፡
3. በህመም ምክንያት 6 ወር በላይ በስራ ላይ አለመገኘት የስራ ውልን ለማቋረጥ ህጋዊ ምክንያት ነው፡፡

የሰ/መ/ቁ. 21119

መጋቢት 18/99 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. ” አሰግድ ጋሻው
3. ” መስፍን ዕቁበዮናስ
4. ወ/ት ሂሩት መለሠ
5. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** ቃሊቲ ምግብ አክሲዮን ማህበር ነ/ፈጅ ፈለቀ ዋቆ ቀረበ

**መልስ ሰጭ፡-** ማስተዋል ጫኔ ቀረበ

## ፍ ር ድ

አቤቱታው የቀረበው የፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10144 የካቲት 24/97 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሣኔ የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 38753 ሐምሌ 12/97 ዓ.ም የቀረበለትን ይግባኝ በመሠረዝ በሰጠው ትእዛዝ ላይ ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጪ በሥር ያቀረበው ክስ በየካቲት ወር 1994 ዓ.ም በድንገት በመታመሙ ለ9 ወር ያህል ህክምና ሲከታተል መቆየቱን ገልፆ፣ በህመም ምክንያት የቀረበት የሥራ ቀን ታስቦ 6 ወር በህመም ፈቃድ ቀሪው 3 ወር ደግሞ የሥራ ቀን ብቻ ተቆጥሮ በዓመት ፈቃድ ታስቦ በግል ማህደሩ ተመዝግቦ እያለ ተከሣሽ ታህሣሥ 4/95 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ያላግባብ የሥራ ውሉን በማቋረጡ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደሥራው እንዲመለስ ያመለከተበት ነው፡፡

ክሱ የቀረበለት የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመርና በፍ/ቤቱ ትእዛዝ መሠረትም የሰዓት መቆጣጠሪያው እንዲቀርብ ካደረገ በኋላ ከታህሣሥ 01/94 ዓ.ም እስከ ታህሣሥ 01/95 ዓ.ም በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ በሰዓት መቆጣጠሪያው ላይ ምልክት ተደርጐ በህመም ፈቃድ ተጠሪው የቀረበት ጊዜ ለ164 ቀናት ብቻ በመሆኑ፣ እንዲሁም ለ38 ቀናት ደግሞ የዓመት ፈቃድ እንደተሰጠው በአጠቃላይ በሕመም ምክንያት የቀረው ለ164 ቀናት ብቻ በመሆኑ 6 ወር ስላልሞላው ተከሣሽ የከሣሽን የሥራ ውል ያቋረጠው በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 85(2) ውጪ ስለሆነ ሕገወጥ የሥራ ውል ማቋረጥ ነው በማለት የ6 ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደሥራው እንዲመለስ ወስኗል፡፡ ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ቀርቦም ይግባኙ ተሠርዞ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

ይህ አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሣኔ ላይ ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ይቀርባል የተባለውም ተጠሪ በህመም ምክንያት ከሥራ ቀረባቸው የተባሉበትን ቀናት የሥር ፍ/ቤቱ የተከተለው ስሌት በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ነው፡፡



ይግባኝ ከቀረበበት ፍርድ ወይም ውሣኔ ላይ መረዳት እንደተቻለው የአሁን ተጠሪ በህመም ምክንያት ከየካቲት ወር 1994 ዓ.ም ጀምሮ የሥራ ውሉ እስከተቋረጠበት ታህሣሥ ወር 1995 ዓ.ም ድረስ ከ9 ወር በላይ በሥራው ላይ ያልተገኘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ፍ/ቤቱ የጊዜውን አቆጣጠር ያሰላው በሰዓት መቆጣጠሪያው ላይ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ለ164 የሥራ ቀናት ከሥራ መቅረቱን ምልክት የተደረገበትን ብቻ በመውሰድ ሲሆን፣ ይህም በአዋጁ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 85(2) መሠረት የ6 ወር ጊዜ አላለፈም በማለት ነው፡፡

የህመም ፈቃድ ጊዜን አስመልክቶ በአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 85(2) ላይ በግልጽ የተደነገገው ግን ሕመሙ ከደረሰበት የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ባለው የ12 ወር ጊዜ ውስጥ በተከታታይ ወይም በተለያዩ ጊዜያት ቢወሰድም በማንኛውም ሁኔታ የህመም ፈቃድ ከ6 ወር አይበልጥም የሚል ነው ይህም የህመም ፈቃድ ጊዜ አቆጣጠሩ የሥራ ቀናትን ብቻ በመለየት ሣይሆን ህመሙ ከደረሰበት የመጀመሪያው ቀን አንስቶ በመቁጠር በጠቅላላው ከ6 ወር መብለጥ እንደሌለበት ሕጉ በግልጽ የደነገገው ነው፡፡

ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቱ ከዚህ የሕግ ድንጋጌ ውጪ የ6 ወራት የህመም ፈቃድ ጊዜ አቆጣጠሩ የሥራ ቀናትን ብቻ የሚመለከት እንደሆነ አድርጐ በመውሰድ በሕጉ አተረጓጐሙ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10144 የካቲት 24/97 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 38753 ሐምሌ 12/97 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. መልስ ሰጪው በህመም ምክንያት ከ6 ወር በላይ ሥራው ላይ ባለመገኘቱ የአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 85(2) ድንጋጌን መሠረት በማድረግ የሥራ ውሉ መቋረጡ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
4. የዚህ ውሣኔ ቅጅም ለሥር ፍ/ቤቶቹ ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰ/መ/ቁ. 21961

መጋቢት 18/99 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
” አሰግድ ጋሻው
” መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ት ሂሩት መለሠ
አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** አቶ ግርማ ነጋሽ

**ተጠሪ፡-** ቢግ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማ

*የስራ ክርክር - የስራ ውል ማቋረጥ - አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)ሐ*

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ከስራ የተሰናበቱት በህገ ወጥ መንገድ ስለሆነ ወደ ሥራ ሊመለሱ አይገባም ሲል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻሩ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

**ውሣኔ: -** የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሮ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡

ግራ ቀኙ በስር ፍርድ ቤት ያልተከራከሩበትንና በጭብጥ ያልተያዘን መሰረት አድርጐ ውሳኔ መስጠት መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡



የሰ/መ/ቁ. 21961

መጋቢት 18/99 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. ” አሰግድ ጋሻው
3. ” መስፍን ዕቁበዮናስ
4. ወ/ት ሂሩት መለሠ
5. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- አቶ ግርማ ነጋሽ = ጠበቃ አቶ መስፍን አዲስ ቀረበ

ተጠሪ፡- ቢግ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማ = የቀረበ የለም

## ፍ ር ድ

አቤቱታው የቀረበው የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 35171 ጥቅምት 10/98 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፌዴ/የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16343 ጥቅምት 29/97 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በመሻር በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡

የአሁን አመልካች በሥር ያቀረበው ክስ በተጠሪው ድርጅት ውስጥ ከጥር 21/95 ዓ.ም ጀምሮ በሹፌርነት ተቀጥሮ ሲያገለግል መቆየቱን ጠቅሶ፣ ተከሣሽ ሰኔ 8/96 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ 50 ኪ.ግ.ማዳበሪያ አጉድለሀል በሚል ውንጀላ ከሕግ ውጪ የሥራ ውሌን በማቋረጡ የአገልግሎትና ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

የአሁን ተጠሪም ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ፡- አመልካች እንዲያስረክብ ከተሰጠው 400 ኩንታል ማዳበሪያ ውስጥ 50 ኪ.ግ.ወይም አንድ ከረጢት ማዳበሪያ አጉድሎ በሸቀጥ መረከቢያ ሠነድ ቁጥር 4191 በሆነ 399.5 ኩንታል ብቻ ማስረከቡ ስለተረጋገጠና እርሱም ስላመነ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ሐ) መሠረት የሥራ ውሉ መቋረጡ በአግባቡ ነው ሲል ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤትም በግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ በተከሣሽ ድርጅት የጭነት ትእዛዝ መሠረት ከጅቡቲ ወደብ ከሣሽ ይዞ የመጣውን 400 ኩንታል ማዳበሪያ ሙሉ በሙሉ ግንደወየን የሚባል ቦታ I S C O ጥቁር አባይ ለተባለ ድርጅት በተረካቢዋ በወ/ሮ ቅድስት ማሞ ተረካቢነት እንዳስረከበ በማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን መዝግቦታል፡፡ በተከሣሽ ድርጅት የቀረበውን የሠነድ ማስረጃ በተመለከተም በከሣሽ መኪና አምባሰል የንግድ ሥ/ኃ/የተ/የግል ማህበር የደረሰው ማዳበሪያ 399.5 ኩንታል መሆኑን ከማስረዳት በስተቀር ከሣሽ 400 ኩንታል ማዳበሪያ ተረክቦ 399.5 ኩንታል ለአምባሰል ማስረከቡን ስለማያረጋግጥ ከሣሽን ለጉደለው 50 ኪ.ግ. ማዳበሪያ ተጠያቂ የሚያደርገው አይደለም ሲል የከሣሽ የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጭ ነው በማለት ባቀረበው የክፍያ ጥያቄ ላይ መርምሮ ክፍያው እንዲፈፀም ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ ይግባኝ ለፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቅረቡ የይግባኝ ክርክሩ ከተካሄደ በኋላ ፍ/ቤቱ በመጨረሻ የሰጠው ውሣኔ የአሁን አመልካች 400

ኩንታል ማዳበሪያ ስለመረከቡና 50 ኪ.ግ.መጉደሉ አከራካሪ ባለመሆኑ፣ አመልካች በተጠሪው ትእዛዝ ለታዘዘበት ድርጅት አስረክቤያለሁ ቢልም አስረከብኩ ያለበት የሠነድ ማስረጃ ግን ስርዝ ድልዝ ያለው በመሆኑ፣ዋናው ቅጅም የቀረበ ስላልሆነ ማስረጃው ተዓማኒነት የሌለው ነው፡፡በዚህም መሠረት አመልካቹ የተረከበውን ማዳበሪያ ሲያስረክብ መጉደሉ አከራካሪ ባለመሆኑ አመልካች ለጉድለቱ ኃላፊ ተደርጎ የሥራ ውሉ መቋረጡ በአግባቡ ነው በማለት የፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤቱን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

ይህ አቤቱታ የቀረበውም በመጨረሻ የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ሲሆን፣ ጉዳዩ ለሰበር ይቀርባል የተባለውም የፌዴራ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በሥር ፍ/ቤት ክርክር ያልተነሣበትን በማስረጃነት የቀረበን ሠነድ ተዓማኒነት የለውም ሲል የሥር ፍ/ቤቱን ውሣኔ መሻሩ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ነው፡፡

አመልካች በአቤቱታው ላይ እንደገለፀው ከተጠሪው በተሰጠኝ የጭነት ትእዛዝ መሠረት 400 ኩንታል ማዳበሪያ ከጅቡቲ ወደብ ተነስቼ ግንደወይኒ በመድረስ I S C O ጥቁር አባይ ለተባለው ድርጅት ቅድስት ማሞ ለተባለች ተረካቢ አስፈርሜ ሙሉ በሙሉ ስለማስረከቤ ከተከሣሽ የተሰጠኝ የጭነት ማዘዣው ያስረዳል፡፡ ይህ የጭነት ማዘዣም የራሱ የተጠሪው መሆኑን አልካደም፡፡ ተጠሪው በስር ሲከራከር የነበረውም ያቀረብኩትን የጭነት ማዘዣ ሠነድ ማስረጃ አምኖ ነው፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት የጭነት ማዘዣ ሠነዱን የተቸው ተጠሪው ያልተከራከረበትንና ያልካደውን ይልቁንም ያመነውን ነጥብ ፍ/ቤቱ በራሱ አነሻሽነት ማስረጃው ተዓማኒነት የለውም ሲል የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤቱ የሰጠውን ውሣኔ የሻረው የዳኝነት አሰጣጥ መርህን የሚያፋልስ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ውሣኔው ተሽሮ የመጀ/ደረጃ ፍ/ቤቱ ውሣኔ እንዲፀናልኝ የሚል ነው፡፡

ችሎቱም ጉዳዩ ለሠበር ይቀርባል በተባለው ነጥብ ዙሪያ የሥር ክርክርና ማስረጃውን አቤቱታ ከቀረበበት ፍርድ ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡

አመልካች ከተጠሪ በተሰጠው የጭነት ማዘዣ መሠረት ከጅቡቲ ወደብ 400 ኩንታል ማዳበሪያ ጭኖ ግንደወይኒ በተባለ ቦታ I S C O ጥቁር አባይ ለተባለ ድርጅት እንዲያስረክብ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት 400 ኩንታል ማዳበሪያውን በተባለው ቦታ አድርሶ ወ/ሮ ቅድስት ማሞ ለተባለች ተረካቢ አስፈርሞ ያለጉድለት ሙሉ በሙሉ ያስረከበበትን ማሰረጃ ማቅረቡ በሥር ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይህ የማስረከቢያ የሠነድ ማሰረጃም በማስረጃነት ቀርቦ ተከሣሽ (የአሁን ተጠሪ) በሠነዱ ላይ ያቀረበው ተቃውሞ ወይም ክዶ የተከራከረበት ነገር እንደሌለም የሥር ክርክሩ ያስረዳል፡፡ ኋላ ግን ንብረቱን ግንደወይን ጣቢያ ከሣሽ/የአሁን አመልካች/ እንዲያስረክብ የታዘዘው ስህተት እንደሆነ ተገልፆ እንደገና ጭነቱን ጭኖ ከአምባሰል የንገድ ሥራዎች ኃ/ይተ/የግል ማህበር እንዲወሰድ ሲታዘዝ አስቀድሞ ያስረከበውን ንብረት እንደገና ሲጭን አንድ ከረጢት ወይም 50 ኪ.ግ.ማዳበሪያ መጉደሉ መረጋገጡ በአመልካች በኩል የተፈጠረ ጉድለት ስለመሆኑ ተጠሪው ያስረዳበት ነገር የለም፡፡ በተጠሪው በኩል የቀረበው ማስረጃ የሚያሣየው አምባሰል የንግድ ሥ/ኃ/የተ/የግል ማህበር ንብረቱን ሲረከብ 399.5 ኩንታል ማዳበሪያ ለመሆኑና የመረከቢያ ሠነድ ቁጥር 4191 አንድ ከረጢት ወይም 50 ኪ.ግ. ማዳበሪያ የጉደለ መሆኑን ከሚያስረዳ በስተቀር ጉድለቱ በከሣሽ የተፈፀመ መሆኑን የሚያስረዳ አይደለም፡፡ በዚህም አንድ የማይካድ ነገር ቢኖር 50 ኪ.ግ ማዳበሪያ መጉደሉ ግልጽ ነው፡፡ የአሁን አመልካች ግን በመጀመሪያ አስረክብ በተባለው ቦታ ሙሉ በሙሉ ያለጉድለት 400 ኩንታል ማዳበሪያ አስፈርሞ ማስረከቡን የሚያስረዳ ማስረጃ ሲያቀርብ ማስረጃው ሀሰተኛ ነው ተብሎ



በተጠሪው የተካደ አይደለም፡፡ አስረክቦት የነበረውን ንብረት እንደገና ሲጭን ግን አንድ ከረጢት ወይም 50 ኪ.ግ ማዳበሪያ ጉደለ መባሉ በአመልካች የተፈጠረ ጉድለት መሆኑን የሚያሣይ አይደለም፡፡

የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ለጉድለቱ አመልካችን ተጠያቂ ያደረገው አስቀድሞ ሙሉ በሙሉ ያለጉድለት አስረከብኩ ያለበትን የሠነድ ማስረጃ ተጠሪው አምኖ የተቀበለውንና ክዶ ያልተከራከረበትን እምነት የሚጣልበት ማስረጃ አይደለም በማለት ተችቶ ውድቅ ካደረገ በኋላ ጉድለት መኖሩ ብቻ መረጋገጡን መሠረት አድርጎ አመልካችን ተጠያቂ ያደርገዋል በሚል ነው፡፡ ይህ ደግሞ የግራ ቀኙን ክርክርና ጭብጥ ያላገናዘበና መሠረት ያላደረገ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 35171 ጥቅምት 10/98 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16343 ጥቅምት 29/97 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ተጠሪው ለአመልካች ብር 1000 (አንድ ሺህ ብር) ይከፈል ብለናል፡፡
4. የፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት የወጪና ኪሣራውን ጨምሮ እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሠበር መ/ቁ. 20457

መጋቢት 20/99 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

" አሰግድ ጋሻው

" መስፍን ዕቁበዮናስ

ወ/ት ሂሩት መለሰ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** የኢት/ንግድ ባንክ

**መልስ ሰጭ፡-** ወ/ሮ ዓለሚቱ ሞገስ ወራሽ

*የስራ ክርክር - የስራ ውል ማቋረጥ - ውዝፍ ደሞዝ ክፍያ፡፡ አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 43፣ 53(1)፣ 54 የሰ/መ/ቁ. 17189*

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪው ከስራ የተሰናበተችው በህገ ወጥ መንገድ ስለሆነ የስድስት ወር ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሏት ወደ ስራ ልትመለስ ይገባል ሲል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሸሯል፡፡

1. በአሰሪና ሠራተኛ ክርክር አንድ ሰራተኛ በክርክር ላይ እያለ በሞት ቢለይ ወደ ስራ የመመለስ ወይም አለመመለስ ጉዳይን ማጣራቱ አስፈላጊ አይደለም፡፡
2. የስራ ውል በተቋረጠ ጊዜ ስራ ላልተሰራበት ውዝፍ ደሞዝ የሚከፈልበት አይደለም፡፡



የሠበር መ/ቁ. 20457

መጋቢት 20/99 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. " አሰግድ ጋሻው

3. " መስፍን ዕቁበዮናስ

4. ወ/ት ሂሩት መለሰ

5. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** የኢት/ንግድ ባንክ ነ/ፈጅ ዘውዱ ዓሊ ቀረበ

**መልስ ሰጭ፡-** ወ/ሮ ዓለሚቱ ሞገስ ወራሽ የቀረበ የለም

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ለአቤቱታው ምክንያት የሆነው ጉዳይ የአሁን መ/ሰጭ የሥራ ውሌ ከሕግ ውጪ የተቋረጠ ስለሆነ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎኝ ወደሥራዬ እንድመለስ በማለት ክስ በማቅረቧ፣ ጉዳዩ የቀረበለት የፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10440 የካቲት 28/97 ዓ.ም በዋለው ችሎት እንደከሣሽ ጥያቄ የሥራ ውሉ ከሕግ ውጪ በመቋረጡ የ6 ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏት ወደሥራዋ ትመለስ ሲል ውሣኔ የሰጠበት ነው፡፡ የአሁን አመልካች በውሣኔው ላይ ቅር ተሰኝቶ ለፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ይግባኙ ተሠርዞበታል፡፡

አመልካች ይህን አቤቱታ ያቀረበውም በዚሁ ውሣኔ ላይ ሲሆን፣ ለሰበር ይቀርባል የተባለበት ነጥብም መልስ ሰጭዋ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏት ወደ ሥራዋ ትመለስ የሚለው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ነው፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ለመስማት ቀጠሮ እንደተያዘ መልስ ሰጪ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየቷ ወራሾች የወራሽነት ማስረጃ ይዘው ቀርበዋል፡፡

መልስ ሰጪ ከዚህ ዓለም በሞት መለየቷ ከተረጋገጠ ደግሞ ወደ ሥራ የመመለስ አለመመለስ ጉዳዩን ማጣራቱ አስፈላጊ ስላልሆነ የክርክሩ ሂደት በዚሁ ተቋርጧል፡፡

የውዝፍ ደመወዝ ክፍያውን በተመለከተም ይህ ችሎት በመ/ቁ. 17189 አግባብነት ያለው የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 53(1)፣ 54 እና 43 ድንጋጌዎችን በመተርጐም የሥራ ውሉ በተቋረጠበት ጊዜ ሥራ ላልተሠራበት ውዝፍ ደመወዝ የሚከፈልበት አይደለም ሲል አስቀድሞ ውሣኔ ሠጥቶበታል፡፡

በመሆኑም በዚህ ጉዳይም የሥራ ውሉ ተቋርጦ በነበረበት ጊዜ ላልተሠራበት ሥራ ውዝፍ ደመወዝ እንዲከፈል በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 10440 የካቲት 28/97 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 38002 ሰኔ 22/97 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሰሯል፡፡
2. የዚህ ውሣኔ ቅጂም ለሥር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሠበር መ/ቁ. 24153

መጋቢት 26/99 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

” አብዱልቃድር መሐመድ

” አሰግድ ጋሻው

” መስፍን ዕቁበዮናስ

ወ/ሪት ሂሩት መለሠ

አመልካች፡- አቶ መንግሥቱ አባተ

ተጠሪ፡- የባህርና ትራንዚት ድርጅት

*የስራ ክርክር - የስራ ውል መቋረጥ - ያለማስጠንቀቂያ ከስራ መሰናበት -አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ተ)*

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪው ከስራ የተሰናበተው በህጋዊ መንገድ ነው ሲል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማፅናቱ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>**ውሣኔ፡ -**</u> የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

ሀሰተኛ የተባለ የትምህርት ማስረጃ ቀርቦ አልታየም፣ የቅጥር ፎርም ላይ ተጠቀሰ የተባለ በእኔ የተሞላ አይደለም የሚለው ክርክር የማስረጃ ጥያቄ እንጂ መሠረታዊ የህግ ክርክር አይደለም፡፡



የሠበር መ/ቁ. 24153

መጋቢት 26/99 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ” አብዱልቃድር መሐመድ

3. ” አሰግድ ጋሻው

4. ” መስፍን ዕቁበዮናስ

5. ወ/ሪት ሂሩት መለሠ

አመልካች፡- አቶ መንግሥቱ አባተ ቀረበ

መልስ ሰጪ፡- የባህርና ትራንዚት ድርጅት የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

አመልካች የፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19788 በ14/4/98 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔና የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 43690 በ21/7/98 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ሲል ግንቦት 24/98 ዓ.ም የተፃፈ የተሻሻለ አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ለመ/ሰጪ ደርሶ የካቲት 1/98 ዓ.ም የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል፡፡

ለአቤቱታው ምክንያት የሆነው አመልካች ለቅጥር ያቀረበው የትምህርት ማስረጃ ሀሰተኛ መሆኑ ስለተረጋገጠ በሕ/ስምምነቱም ሆነ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ተ) መሠረት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ መሠናበቱ በአግባቡ ነው ተብሎ ውሣኔ በመሰጠቱ ነው፡፡

አመልካች በአቀረበው አቤቱታም ሀሰተኛ የተባለው የትምህርት ማስረጃ ቀርቦ አልታየም፣ የቅጥር ፎርሙ ላይ ተጠቀሰ የተባለውም በእኔ የተሞላ አይደለም የሚለው ክርክር የማስረጃ ጥያቀን የሚመለከት እንጂ መሠረታዊ የሕግ ክርክር ያለው ሆኖ ባለመገኘቱ በፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19788 በ14/4/98 የተሰጠው ውሣኔም ሆነ የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 43690 በ21/7/98 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ፀንቷል፡፡ ግራ ቀኙ ኪሣራቸውን ለየራሣቸው ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የሰበር መ.ቁ. 16653

ቀን መጋቢት 27/99 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ” አሰግድ ጋሻው

3. ” መስፍን ዕቁበዮናስ

4. ወ/ት ሂሩት መለሠ

5. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** ግዮን ሆቴሎች ድርጅት

**መልስ ሰጭ፡-** ወ/ሮ ስለእናት ወርቅነህ

*የስራ ክርክር - የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን - የወል የስራ ክርክር - የሰ/መ/ቁ/18180*

ተጠሪዋ የስራ መደቡ እንዲሁም ለቦታው የተመደበው ደሞዝና ጥቅማ ጥቅሞች እንዲሰጡኝ ብለው በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ያቀረቡትን ክስ ቦርዱ የማየት ስልጣን አለው ሲሉ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድና የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ በመቃወም የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

**<u>ውሣኔ፡ -</u>** የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የማየት ስልጣን የተሰጠው የወል የስራ ክርክር ጉዳዮችን ነው፡፡
2. አንድ የሥራ ክርክር የወል የስራ ክርክር ነው የሚባለው ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡
3. አንድ የስራ ክርክር የግል የስራ ክርክር ጉዳይ ነው የሚባለው የክርክሩ ውጤት በተከራካሪው ሰራተኛ (ሰራተኞች) ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀርብ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡
4. የሥራ መደቡ እንዲሁም ለቦታው የተመደበው ደሞዝና ጥቅማ ጥቅሞች እንዲሰጡኝ ተብሎ የሚቀርብ ክስ የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት የሚያስከትል አይደለም፡፡



የሰበር መ.ቁ. 16653

ቀን መጋቢት 27/99 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ” አሰግድ ጋሻው

3. ” መስፍን ዕቁበዮናስ

4. ወ/ት ሂሩት መለሠ

5. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** ግዮን ሆቴሎች ድርጅት ነ/ፈጅ አቶ ስለሺ ቀረበ

**መልስ ሰጭ፡-** ወ/ሮ ስለእናት ወርቅነህ አልቀረበችም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

በዚህ ጉዳይ ለሰበር ችሎት የቀረበው ክርክር የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድን ሥልጣን የሚመለከት ነው፡፡

መልስ ሰጪ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ክሱን ያቀረበችው የሥራ መደቡ እንዲሁም ለቦታው የተመደበው ደመወዝና ጥቅማጥቅሞች እንዲሰጡኝ በሚል ነው፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔም የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ክሱን ለማየት ሥልጣን አለው በማለት የተሰጠ ነው፡፡ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ያቀረበው የሠበር አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት መ/ሰጪ መልሷን አቅርባለች፡፡

ችሎቱም የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የቀረበለትን የሥራ ክርክር ጉዳይ ለማየት ሥልጣን ነበረው ወይስ አልነበረውም? የሚለውን የሕግ ነጥብ መሠረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ይህ ችሎት በመ.ቁ. 18180 አግባብነት ያላቸውን የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ድንጋጌዎች በመተርጐም የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የማየት ሥልጣን የተሰጠው የወል የሥራ ክርክር ጉዳዮችን መሆኑን፣ አንድ የሥራ ክርክር የወል የሥራ ክርክር ነው የሚባለውም ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ውጤት የማያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ መሆኑን በአንፃሩም አንድ የሥራ ክርክር የወል ሣይሆን የግል የሥራ ክርክር ጉደይ ነው የሚባለው የክርክሩ ውጤት በተከራካሪው ሠርተኛ /ሠራተኞች/ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሆኖ ሲገኝ መሆኑን በዝርዝር የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በዚህ የሕግ ትርጉም መሠረት መልስ ሰጪ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የሥራ መደቡና ለቦታው የተመደበው ደመወዝና ጥቅማጥቅሞች ይሰጡኝ በማለት ያቀረበችው ክስ የጋራ በሆነ የሠራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ውጤት የሚያስከትል ባለመሆኑ የወል የሥራ ክርክር አይደለም፡፡ በመሆኑም የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ሥልጣን ሣይኖረው ጉዳዩን አይቶ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

- የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ በመ/ቁ. 193/02/94 ጥር 13/96 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 28606 ሐምሌ 5/96 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
- ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰ/መ/ቁ. 25526

*ሚያዝያ 16/99 ዓ.ም.*

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** መምህር ጥላሁን አስፋው

**መልስ ሰጪ፡-** አዲስ ኮሌጅ

*የስራ ክርክር - ለተወሰነና ላልተወሰነ ጊዜ የሚደረግ የስራ ውል - የስራ ውል መቋረጥ - አዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 9፣ 10*

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪው ከስራ የተሰናበቱት ህጋዊ በሆነ መንገድ ስለሆነ ወደ ስራ ሊመለሱ አይገባም ሲል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻሩ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

**ውሣኔ፡ -** የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሮ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

1. የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 9 በአንድ አሰሪና ሠራተኛ መካከል የተደረገ የስራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ እንደሆነ ግምት ቢወስድም አሰሪ ይህንን ግምት አንቀጽ 10 ላይ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች በማስረዳት ማፍረስ ይችላል፡፡
2. ሰራተኛው በየአመቱ ውሉ እየታደሰ ሲሰራ መቆየቱና የሰራተኛው የቅጥር ውል በጊዜ የተገደበ መሆኑ ብቻ ለተወሰነ ጊዜ ተቀጣሪ የሚያደርገው አይሆንም፡፡



የሰ/መ/ቁ. 25526

*ሚያዝያ 16/99 ዓ.ም.*

**ዳኞች፡-** 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

4. አቶ አሰግድ ጋሻው

5. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** መምህር ጥላሁን አስፋው ቀረበ፡፡

**መልስ ሰጪ፡-** አዲስ ኮሌጅ ጠበቃ አምዴ አበበ ቀረበ

መዝገቡ ተመረምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

አመልካች ሰኔ 15/98 ዓ.ም. በተፃፈ ያቀረበው አቤቱታ የፌዴ/ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሰኔ 5/98 ዓ.ም. በመ/ቁ. 46514 በዋለው ችሎት በሰጠው ውሣኔ ላይ ነው፡፡

አቤቱታው የቀረበበት የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔም፡- የቅጥሩ ሁኔታ በአንድ ድርጅት ቋሚ ሥራ ላይ ቢሆንም ሠራተኛን ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ሥራ ማሠራት እንደሚቻል በፌዴ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 11924 ከተሰጠው የሕግ ትርጉም መረዳት ስለሚቻል አመልካች የተቀጠሩበት የተወሰነው ጊዜ በማለቁ ምክንያት መሰናበታቸው ሕገወጥ ነው አያሰኝም በማለት የፌዴ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሚያዝያ 4/98 ዓ.ም. በቁ. 16344 የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች ባቀረበው አቤቱታ መነሻነትም አመልካች የተቀጠረው ለተወሰነ ጊዜ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ይቀርባል የተባለ ሲሆን መ/ሰጪም መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎ ታሕሣሥ 7/98 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ በመስጠት ተከራክሯል፡፡

የመልስ ሰጪ ዋና መከራከሪያ የሥራ ውሉ ለአንድ ዓመት ሆኖ የውሉ ዘመን ሲያልቅ በዚሁ ሁኔታ ውሉ እየተደረገ ሲሠሩ የቆዩ ሲሆን ግራ ቀኙ ካልፈለጉ ሊያቋርጡ ከፈለጉም ያለፈው የአገልግሎት ሂሣብ ተዘግቶ እንደገና በሌላ ውል የኮንትራት የቅጥር ውል በስምምነት እየተፈረመ ሲሠሩ የቆዩ በመሆኑ የከሣሽ አቤቱታ ውድቅ ሊሆን ይገባል፡፡ አመልካች በ11/01/98 በተፃፈ ማመልከቻ ብቻ የሥራ መልቀቂያ ጠይቀው የተሰናበቱ ናቸው ሲልም በተጨማሪም የተከራከረበት ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የአሁን አመልካች የሥራ መልቀቂያ ጠይቆ የተሠናበተ ነው የተባለበትን በዚህ ችሎትም አስቀርበን እንደተመለከትነው በ11/01/98 ዓ.ም. አመልካች የዓፈው ኮሌጁን በመልቀቁ ምክንያት የሥራ ልምድ ይሰጠኝ ከሚል በስተቀር ሥራውን በገዛ ፈቃዴ ለቅቄያለሁ በማለት ያስታወቀበት ነው ሊባል የሚችል እንዳልሆነ ተመልክተናል። የሥራ ልምድ ይፃፍልኝ ብሎ መጠየቅ ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ለቀቀ የሚያስብለው ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበው መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው አይደለም።

የቅጥሩ ሁኔታ ለተወሰነ ጊዜ ለአንድ ዓመት እየተባለ ጊዜው ሲያልቅ እንደገና እየታደሰ እንደ አዲስ የሚታይ ነው። በዚህም ጊዜው ሳያልቅ ውሉን ማቋረጥ ይችላል የሚለውን ክርክር በተመለከተ ቀደም ሲል የሰበር ችሎቱ በመ/ቁ 11924 በሰጠው ትርጉም፡- አንድ ከአሰሪ ጋር የሥራ ውል ያለው ሠራተኛ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠረ ሊቆጠር እንደሚገባ የአዋጅ ቁጥር 42/85/377/96/ አንቀጽ 9 ግምት እንደሚወሰድለት፣ በዚህ የሕግ ግምት የሥራ ውሉ ያልተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ነው ሲል የሚከራከረው ሠራተኛ ተጠቃሚ በመሆኑ ይህን ክርክሩን የሚደግፍለት ማስረጃ በቅድሚያ ያቀርብ ዘንድ እንደማይጠበቅበት፣ ይልቁንም በሕግ የተወሰደለት ግምት ክርክሩን ከማስረዳቱ ግዴታው ነፃ እንዲሆን እንደሚያደርገው፣ በውጤቱም በቅድሚያ የማስረዳቱ ግዴታ የሥራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ሥራ የተደረጉ ለውጥ በአንቀጽ 10 የሚሸፈን ነው ሲል በሚከራከረው በአሠሪው ላይ የሚወድቅ መሆኑን በዝርዝር ጠቅሶ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ነው።

በዚህም መሠረት አመልካች በየአመቱ ውሉ እየታደሰ ሲሠራ መቆየቱና የአመልካች የቅጥር ውል በጊዜ የተገደበ መሆኑ ብቻ አመልካችን ለተወሰነ ጊዜ ተቀጣሪ የሚያደርገው አይሆንም። መ/ሰጪው ይህንን አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 10/1/ መሠረት አመልካች ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ እንደሌለ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ መሆኑን ከፍርዱ ግልባጭ መረዳት ይቻላል።

ስለዚህ የቅጥር ውሉ በጊዜ የተገደበ መሆኑን ብቻ የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በማየትና የሰበር ችሎቱ በመ/ቁ. 11924 የሰጠውን የሕግ ትርጉም በአግባቡ ባለመረዳት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ተወስኗል።

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ሰኔ 5/98 ዓ.ም. በመ/ቁ. 46514 የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል። ይፃፍ።
2. የፌዴ/መጀ/ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ ሚያዝያ 4/98 ዓ.ም. በቁ. 16344 የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት በማጽናት ወስነናል።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።



**የሰበር መ/ቁ.** 15662

**መጋቢት** 13 **ቀን** 1999 **ዓ.ም**

**ዳኞች፡-** *አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ*

*አቶ አብዱልቃድር መሐመድ*

*አቶ አሰግድ ጋሻው*

*ወ/ት ሂሩት መለሠ*

*አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ*

**አመልካች፡- የኢት/ልማት ባንክ**

**ተጠሪ፡-** *ሀጅ አብድራህማን ቱሊሳ*

*የውል ክርክር - የብድር ውል - የሽያጭ ውል - በሽያጭ ምክንያት ጉድለት ያለበት ነው በማለት የሚቀርብ ክስ ይርጋ - ስለ ውል ትርጉም - በተንኮል የተፈጸመ ውል - የፍ/ብ/ሕግ ቁ.2298፣ 1733*

አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት የብድር ውል ፈርሶ ከውሉ በፊት ወደነበሩበት ቦታ ሊመለሱ ይገባል ሲሉ የአሳባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ በመቃወም የቀረበ አቤቱታ ነው።

**<u>ውሣኔ፡ -</u>** የአሳባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል።

ውሉታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ግልጽ ሆኖ ከሚሰማው በመራቅ የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር ዳኞች ለመተርጎም አይችሉም።

የሰበር መ/ቁ. 15662

መጋቢት 13 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፦ መንበረፀሐይ ታደሰ

አብዱልቃድር መሐመድ

አሰግድ ጋሻው

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፦** የኢት/የ ልማት ባንክ ነገረፈጅ አቶ አክሊሉ ተስፋዬ

**ተጠሪ፦** ሀጅ አብድራህማን ቱሊሳ አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው ለውሣኔ ሲሆን፤ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

አመልካች የሰበር አቤቱታውን ያቀረበው የአላባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ባፀናው ውሣኔ ቅር በመሰኘቱ ነው፡፡

የጉዳዩም መነሻ የአሁን ተጠሪ በልዩ ወረዳው ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሣሽ ሆኖ በአመልካች ላይ ያቀረበው ክስ አመልካች አንድ የእህል ወፍጮ ሊተክልልኝ ሐምሌ 16 ቀን 1988 ዓ.ም ባደረግነው ስምምነት መሠረት ከሠላም ሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል ድርጅት ገዝቶ ካስቀመጣቸው አንዱን ተረክቤ ነበረ፡፡ ሆኖም አገልግሎት ሣይሰጥ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ችግር እየፈጠረ ባለመሥራቱ ይህንኑ ባሣውቅም መፍትሄ አላገኘሁም ከዚህም በኋላ በተበላሸው ወፍጮ ምትክ ሌላ ወፍጮ ገዝቶ ሊተካልኝ መጋቢት 25 ቀን 1992 ዓ.ም ተዋውለናል፡፡ ይሁን እንጂ ተከሣሹ ሁለቱንም ውሎች ተግባራዊ ባለማድረጉና ውሉንም ለህሊና ተቃራኒ እና ተንኮል ባለው ሁኔታ ያስፈረመኝ ስለሆነ ውሎቹ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2287፣ 2290፤ 1823፣ 1824 እና 1808 መሠረት ሊፈርሱ ይገባል የሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካችም ከሣሽ የተበደረው ወፍጮ ሣይሆን የብር 40,000.00 /አርባ ሺህ ብር/ የገንዘብ ብድር ስለመሆኑ በውሉ ላይ ተመልክቷል፡፡

የወፍጮው መግዣ ገንዘብ ለአስመጭው ኩባንያ በከሣሽ ስም ወጭ ሆኖ እንደሚከፈል በተስማማው መሠረት ይኸው የብድር ገንዘብ ለአስመጭው ኩባንያ ተከፍሎላቸዋል፡፡ ከሣሽ ውሉን አውቆና ተገንዝቦ ከፈረመ በኋላ ወፍጮውን ከኩባንያው ተረክቧል፡፡ ወፍጮው የሚፈለግበትን ግልጋሎት ሊሰጥ አልቻለም በሚል ምክንያት የብድሩ ውል ይፍረስልኝ ማለታቸው ተቀባይነት የለውም፤ በብድሩ ገንዘብ የተገዛው ወፍጮ መሥራት ካልቻለ የብድር ስምምነቱ ይፈርሣል የሚልም ግዴታ አልነበረንም፤ አመልካች የፈፀማቸው የተንኮል ተግባራት ምን እንደሆነም አላብራሩም፤ በቁጥር ዋሥአ/031/2000 መጋቢት 12 ቀን 1992 ዓ.ም የተፃፈውም ደብዳቤ ከሣሽ በጠየቁት መሠረት የወፍጮ



መግዣ ብድር እንዲሰጣቸው የሚል እንጂ ምትክ ወፍጮ ለመስጠት አይደለም፡፡ ይህንንም በገዛ ፈቃዳቸው ትተውታል በማለት መልስ ሰጥቶበታል፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ፣

በአንድ በኩል ተደርጓል የተባለው ስምምነት የከሣሽን ግልጽ የሆነ የኑሮ ልማድ ዕውቀት ማጣትን በመጠቀም እንዲሁም ተከሣሽ የመንግሥት የልማት ድርጅት በመሆኑ በውሉ ላይ የተመለከተውን ቃል እንደማያጥፍ በማመን እና ብልሽት ያለበት መሆኑን ቢያውቅ ኖሮ የማይቀበለውን ግዴታ እንዲቀበል መደረጉ ሆን ተብሎ የማታለል ወይም ሁለተኛ የማግባቢያ ዘዴ በመጠቀም በተንኮል የተደረገ መሆኑን በመጥቀስ ውሉ መፍረስ እንደሚገባው በውሣኔው መሠረት ያደረገ ሲሆን፣

በሌላም በኩል ግራ ቀኙ ቀጥተኛ የወፍጮ ሽያጭ ውል ባያደርጉም በተዘዋዋሪ መንገድ የወፍጮ ብድር መሆኑን ስለሚያመለክትና በብድር የተሰጠውም ወፍጮ ጉድለት ያለበት በመሆኑ የውል ስምምነቱ ፈራሽ ነው ስለሆነም የውል ስምምነቱ ሙሉ በሙሉ ፈርሶ ውል ከመደረጉ በፊት ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ጉዳይ ይግባኝ የቀረበለትም የፌዴራል ከፈተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ መዝገቡን ከመረመረ በኋላ፣

የብድር ገንዘቡ በእጅ የሚሰጥ ሣይሆን ለወፍጮ መግዣ ባንኩ ለአስመጭው ወጭ አድርጎ የሚከፍለው እንደሆነ ውሉ የሚናገር መሆኑን ጠቅሶ ግዥው የተፈፀመው በማን ነው የሚለውን በሚመለከት ውሉ መልስ አይሰጥም፡፡ እንዲህም በሆነ ጊዜ ከውሉ በኋላ የነበረውን ሁኔታ በማመዛዘን የተዋዋዮቹ ሀሣብ ምን ነበር? የሚለውን መሠረት በማድረግ መታየት አለበት የብድሩ ውል ከተፈረመ በኋላ በወፍጮው ርክክብ ሰነድ ላይ ባንኩ ገዢ መሆኑና ከርክክብ በኋላ በታየው ጉድለት ሣቢያ በሻጭ ላይ ክስ መመስረቱን ስለገለፀ ገዢው ባንኩ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ተበዳሪው ከመጀመሪያውኑ ባንኩ በብድሩ ገንዘብ ገዝቶ የሚያቀርብለት ወፍጮ እንደማይሰራ ቢያውቅ ኖሮ የብድር ውሉን ባልፈረመ ነበር የሚለውን ተንተርሶ የሥር ፍ/ቤት ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት የሰጠውን ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የቅሬታ ነጥቦችም፣ ለክሱ መነሻ የሆነው አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት ስምምነት ይዘት የገንዘብ ብድር ሆኖ እያለ የሥር ፍ/ቤቶች በትርጉም ሰበብ ከውል በኋላ የነበረውን ሁኔታ ማመዛዘን ያስፈልጋል የሚለውን በመያዝ የወፍጮ ሽያጭ ስምምነት ባንክ እንደፈፀመ በመቁጠር የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ፣

ሽያጭ ተከናውኗል እንኳ ቢባል በሽያጭ ምክንያት ጉድለት ያለበት ነው በማለት የሚቀርብ ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2298 በአንድ ዓመት መቅረብ ሲገባው

ከዚህ ጊዜ በኋላ ክስ በማቅረቡ በይርጋ ቀሪ ሆኖ እያለ ባንኩ የማጭበርበር ተግባር ፈጽሟል በማለት መታለፉ ሕግን መሠረት ያደረገ ባለመሆኑ፣

አመልካች የተንኮል ተግባር መፈፀሙ ሣይረጋገጥ የማታለል ወይም ሐሰተኛ የማግባቢያ ዘዴ በመጠቀም በተንኮል የተፈፀመ ስምምነት ነው፡፡ ተበዳሪው ወፍጮው የማይሠራ መሆኑን ቢያውቅ ኖሮ የብድሩን ውል ባልፈረመ ነበር በማለት እንደ ውል ማፍረሻ ምክንያት መወሰዱ ሕጋዊ መሠረት የለውም የሚሉት ናቸው፡፡

በዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ መልስ ሰጭ እንዲቀርብ ተደርጎ በሥር ፍ/ቤቶች በየደረጃው ያቀረባቸውን የመከራከሪያ ነጥቦች በማጠናከር በሥር ፍ/ቤቶች የተፈፀመ የሕግ ስህተት የለም በማለት ዝርዝር መልስ ሰጥቶበታል፡፡ የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ለዚህ ጉዳይ መነሻ የሆነው ግራ ቀኙ ሐምሌ 16 ቀን 1988 ዓ.ም ያደረጉት ስምምነት ነው፡፡ የዚህ ስምምነት ርዕስ እንደሚያመለክተውና ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በውሣኔው ላይ እንደገለፀው ስምምነቱ የገንዘብ ብድር ስለመሆኑ አከራካሪ አይደለም እንዲሁም የብድሩ ገንዘብ ለወፍጮ ግዢ እንደሚውልና ገንዘቡም በቀጥታ በተበዳሪው የሚከፈል ሣይሆን ለወፍጮ አስመጪው ኩባንያ ስለመሆኑ ይኸው ውል ያስረዳል፡፡ ይህ ስለመሆኑ ውሉ ግልጽ ነው፡፡ ለትርጉም በር የከፈተም አይደለም፡፡ ከየትኛው አስመጪ ኩባንያ የሚለውን በሚመለከት በውሉ ላይ በግልጽ ባይመለከትም«... የወፍጮው መግዣ ገንዘብ በአስመጪው ኩባንያ ወጭ ሆኖ ይከፈላል፡፡» በሚል መጠቀሱ የአስመጪውን ኩባንያ ማንነት ምርጫ ለአበዳሪው የተተወ ስለመሆኑ ተበዳሪው አስቀድሞ የተስማማ፤ (መሆኑን) ፈቃድ የሰጠበት መሆኑን ከሚያመለክት በቀር የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው አይደለም፡፡ ተጠሪ ከሠላም ሙያና ቴክኒክ ማሰልጠኛ የተባለውን ወፍጮ መረከቡም ይህንኑ አባባል የሚያጠናክር ነው፡፡ ይህም የውል ይዘት ባንኩ የወፍጮ ሻጭ መሆኑን አያመለክትም፡፡ ሻጭ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ለተሸጠው ነገር ጉድለት ኃላፊ ለማድረግ የሚያስችል ሕጋዊ መሠረት የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ለውሣኔያቸው መሠረት ያደረጉት ተበዳሪው የተሸጠው ወፍጮ ጉድለት የሚኖርበት መሆኑን ቢያውቅ ኖሮ ስምምነቱን አይፈጽምም ነበር የሚለውን በመያዝ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከላይ እንደተገለፀው የብድሩ ገንዘብ ለወፍጮ መግዣ እንደሚውልና ይህም ገንዘብ በቀጥታ ለተበዳሪው የሚከፈል ሣይሆን ወፍጮውን ለሚያቀርብ አስመጪ ኩባንያ በተበዳሪው ስም ወጭ ሆኖ እንደሚከፈል የሚያረጋግጥ በመሆኑ ውሉ ግልጽ ነው፡፡ ወፍጮውን ማን ገዛው የሚለው በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተያዘው ጭብጥ ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት የለውም እንጂ አለው እንኳ ቢባል ተጠሪው እንደስምምነቱ ወፍጮውን ከአስመጪው ኩባንያ መረከቡ ነው፡፡ ከተረከበው በኋላ ለሚታየው ጉድለት ንጥጥሩን ወፍጮውን ከአስረከበው ኩባንያ ጋር ከሚያደርግ በቀር በውሉ ባልተመለከተው አበዳሪውን እንደ ሻጭ በመቁጠር የተሸጠው ነገር ጉድለት ተገኝቶበታልና ለጉድለቱ እንደማካካሻ የብድር ስምምነቱ ሊፈርስ ይገባል በማለት ለመጠየቅ



የሚያስችለውን መብት አይሰጠውም፡፡ የአበዳሪን ግዴታ በሚመለከት ውሉ ግልጽ ሆኖ እያለም ወፍጮውን ማን ገዛው? የሚለውን በሚመለከት ውሉ ግልጽነት ይጐድለዋል፤ ግልጽ ካልሆነ ደግሞ ከውል በኋላ የተፈፀመውን ተግባር በመንተራስ የተዋዋዮች ሀሣብ ምን ነበረ? የሚለውን በመያዝ መተርጐም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1733 "ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ግልጽ ሆኖ ከሚሰማው በመራቅ የተዋዋዮቹ ፈቃድ ምን እንደነበረ ዳኞች ለመተርጎም አይችሉም" የሚለውን ክልከላ መተላለፍ ነው፡፡

በሌላ በኩል የፈቃድ ጉድለት አለበት በሚል እንደ ውል ማፍረሻ ምክንያት የተወሰደው ተዋዋይ በኑሮ ልማድ ዕውቀት ማነስ የተነሣና አበዳሪውም የመንግሥት ተቋም በመሆኑ ኃላፊነቱን ይወጣል የሚል እምነት በመጣል ምክንያት የተፈፀመ ውል በመሆኑ የማታለል ወይም የተንኮል ተግባር የተፈፀመ መሆኑን ያሳያል በሚል የቀረበው የፍሬ ነገር ክርክር /ማስረጃ በተባለው አኳኋን የፈቃድ ጉድለት የነበረ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አይደሉም፡፡ ተቀባይነትም የላቸውም፡፡

በሌላ በኩል አመልካች የተሸጠውን ነገር ገዢ በእጁ ከአደረገ በኋላ ለሚደርሰው አደጋ ኃላፊነቱ በማን ላይ እንደሚወድቅና ጉድለት መኖሩ ከታወቀ ለምን ያህል ጊዜ ክስ ሊቀርብ ይገባዋል የሚለውን በመጥቀስ በአማራጭ ያቀረበው ክርክር ንብረቱን በሸጠው ወገን በኩል የሚቀርቡ መከራከሪያዎች ናቸው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው በዚህ ጉዳይ አመልካች ሻጭ አይደለም ሻጭ ሣይሆን ያነሣው ክርክር በመሆኑ ይህንኑ የመከራከሪያ ነጥብ መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ለማጠቃለል ያህል አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት ስምምነት ግልጽና ትርጉም የማያስፈልገው መሆኑ እየታወቀ በትርጉም ሽፋን የሥር ፍ/ቤቶች አመልካችና ተጠሪ ሐምሌ 16 ቀን 1988 ዓ.ም ያደረጉት የገንዘብ ብድር ውል ፈርሶ ከውሉ በፊት ወደ ነበሩበት ቦታ ሊመለሱ ይገባል ሲሉ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

የልዩ ወረዳው ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንን ጉዳይ በማስመልከት በፍ/ብ/መ/ቁ. 3195 በ18/02/96 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 26638 በ4/06/96 ዓ.ም ይግባኝ የተባለበት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በሚል የተሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡

በዚህ ክርክር ምክንያት የደረሰውን ወጭና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የሰበር መ/ቁ. 19081

መጋቢት 18 ቀን 1999

ዳኞች፦ አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፦ ዓሊ ቃሌብ አህመድ

መልስ ሰጪ፦ እነ አቶ ሚሊዬን ተፈራ

*ይርጋ - ይርጋን የማንሳት ኃላፊነት የተከሳሽ መሆኑ - የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1677፣ 1901።*

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት በተጠሪዎች ላይ የቀረበው ክስ በይርጋ ታግዷል ሲል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ ነው።

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል።

1. የይርጋ አፈፃፀም ትርጉም ሊሰጠው የሚገባው በሚቀርበው የክስ ባህሪ አንጻር ነው።
2. በመርህ ደረጃ የይርጋ ጥያቄ በተከራካሪዎች ካልተነሳ ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት ሊያነሳው አይችልም።
3. ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የተገናኙ ተከሣሾች በአንድ ላይ በተከሰሱ ጊዜ አንዱ ተከሳሽ የሚያነሳውን የይርጋ መቃወሚያ መሰረት በማድረግ ክሱን መዝጋት ከህጉ ጋር የሚጋጭ አይደለም።



የሰበር መ/ቁ. 19081

መጋቢት 18 ቀን 1999

ዳኞች፦ 1. መንበረፀሐይ ታደሰ
2. አሰግድ ጋሻው
3. መስፍን ዕቁበዮናስ
4. ሂሩት መለሠ
5. ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፦ ዓሊ ቃሌብ አህመድ - አልቀረበም

መልስ ሰጪ፦ 1ኛ/ አቶ ሚሊዮን ተፈራ - አልቀረበም

2ኛ/ ኮሜት ትራንስፖርት - ነገረፈጅ - ላቀው ክብረት ቀረቡ

3ኛ/ ኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ - አልቀረበም

በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ሦስተኛ መልስ ሰጭ ያቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ መሠረት በማድረግ አመልካች በ1ኛና በ2ኛ ተከሣሾች ላይ ያቀረበውን ክስ ጭምር ውድቅ ማድረጉ የሕግ ስህተት ነው በሚል ነው። መዝገቡን መርምረን እንደተረዳነው አመልካች በሦስቱም መልስ ሰጪዎች ላይ ያቀረበው ክስ በ2ኛ ተከሣሽ ትእዛዝ፣ በአንደኛ ተከሣሽ አሽከርካሪነት ሲንቀሣቀስ የነበረው የሦስተኛ ተከሣሽ ንብረት የሆነው መኪና በከሣሽ መኪና ላይ ጉዳት በማድረሱ ለደረሰው ጉዳት ሦስቱም ተከሣሾች ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ተጠያቂ ናቸው ይባልልኝ የሚል ነው። አንደኛው ተከሣሽ ክሱ ደርሶት ያልቀረበ በመሆኑ ጉዳዩ በሌለበት ሲቀጥል 2ኛና 3ኛ መልስ ሰጪዎች ግን ቀርበው ተከራክረዋል። የይርጋን ጥያቄ ያቀረበው ግን 3ኛ ተከሣሽ ብቻ ነው። 2ኛ ተከሣሽ ለክሱ መቃወሚያዎችንና መልሱን ያቀረበ ቢሆንም የይርጋ ጥያቄ ግን አላነሣም።

አመልካች ለሰበር ያቀረቡት አቤቱታ 1ኛና 2ኛ መልስ ሰጪዎች ባላነሱትና ባላቀረቡት የይርጋ ጥያቄ ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረጉ አግባብ አይደለም የሚል ሲሆን 2ኛ መልስ ሰጪ 3ኛ ተከሣሽ ባቀረበው የይርጋ ጥያቄ መነሻነት የአመልካች ክስ በይርጋ መዘጋቱ አግባብ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል።

የቀረበው አቤቱታ የይርጋን ሕግ አፈፃፀም የሚመለከት ሲሆን ይህ ችሎት ትርጉም ሊሰጠው የሚገባው አመልካች ካቀረበው የክስ ባህርይ አንፃር መሆን እንዳለበት አምኖበታል። በመርህ ደረጃ የይርጋ ጥያቄ በተከራካሪዎች ካልተነሣ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሣሽነት ሊያነሣው እንደማይችል በፍትሀ ብሄር ሕጉ በግልጽ ሰፍሮ የሚገኝ ነው። በዚህ ሕግ መሠረት የይርጋን ጉዳይ የማንሣት ወይም ያለማንሣት ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ የተከሣሽ ወገን ነው። ይህ አጠቃላይ

መሠረተ ሃሣብ ግን በፍትሐብሔር ሕጉ ሌሎች ክፍሎች ከተጠቀሱትና አሁን ከያዝነው ጉዳይ ጋር አግባብነት ካላቸው ሌሎች ድንጋጌዎች ጋር አብሮ መታየት ይኖርበታል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው የአሁን አመልካች በሦስቱም መልስ ሰጪዎች ላይ ያቀረበው ክስ ለደረሰው ጉዳት ባልተነጣጠለ ኃላፊነት ይወሰንባቸው የሚል ነው፡፡ በመሆኑም ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የተገናኙ ተከሣሾች ስለሚያቀርቡዋቸው መከላከያዎች ሕጉ የሚለውን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ የያዝነው ጉዳይ ከውል ውጪ የደረሰ ጉዳይን የሚመለከት ቢሆንም የውል ሕግ መሠረተ ሃሣቦችም ተፈፃሚ እንደሚሆኑ በሕጉ አንቀጽ 1677 ሰፍሯል፡፡ በዚህ መሠረት ያልተነጣጠለ ኃላፊነት ያለባቸው ባለእዳዎችን የሚመለከተው የውል ሕግ ክፍል ለያዝነውም ጉዳይ ቢሆን አግባብነት አለው፡፡ የውል ሕግ አንቀጽ 1901 "ባለእዳ የሆኑት ሁሉ እዳው በሙሉ ወይም በከፊል ተከፍሏል ወይም በይርጋ ታግዷል በማለት ባለገንዘቡን ለመከራከር ይችላሉ" በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ በግልጽ እንደሰፈረው ከተከሣሾች አንዱ የይርጋ ጥያቄ ማንሣት እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት የሦስተኛውን ተከሣሽ የይርጋ መቃወሚያ መሠረት በማድረግ ክሱን መዝጋቱ ከሕጉ ጋር የሚጋጭ አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ሰበር ችሎት የሚታረም የሕግ ስህተት የለም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 145/93 የሰጠው ውሣኔና ከፍተኛው ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 1457/97 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡



የሰበር መ/ቁ. 23320

መጋቢት 20 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
” ፍስሐ ወርቅነህ
” ዓብዱልቃድር መሐመድ
” መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ት ሂሩት መለሠ

አመልካች፡- አቶ ገብሩ አብሴ

ተጠሪዎች፡- እነ የአቶ ሁሴን አብዱራህማን ወራሾች

የኪራይ ውል - የኪራይ ውል በአከራይና በተከራይ መካከል የሚደረግ ስለመሆኑ - የዳኝነት አከፋፈል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ለ1ኛው ተጠሪ ኪራይ ሊከፍሉ ይገባል ሲል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

ውሣኔ፡ - የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. ኪራይ በአከራይና በተከራይ መካከል የሚደረግ ውል ነው፡፡
2. ይዞታን ያስረክቡኝ ተብሎ ለቀረበ ክስ የቤቱ ዋጋ ተገምቶ የዳኝነት ማስከፈል ስህተት ነው፡፡

የሰበር መ/ቁ. 23320

መጋቢት 20 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. ” ፍስሐ ወርቅነህ
3. ” ዓብዱልቃድር መሐመድ
4. ” መስፍን ዕቁበዮናስ
5. ወ/ት ሂሩት መለሠ

አመልካች፡- አቶ ገብሩ ኦብሴ - ከጠበቃ ወንድአወክ አየለ ጋር ቀረበ

ተጠሪ፡- 1. የአቶ ሁሴን አብዳራህማን ወራሾች - ወኪል ቀረበ
2. የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት - ነገረፈጅ ቀረበ
3. የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ተተኪ የመሠረተ ልማት ሚኒስቴር

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል - ነ/ፈጅ ቀረበ

## ፍ ር ድ

በሥር ፍ/ቤት የአሁኖቹ አንደኛ ተጠሪዎች በአሁኑ አመልካችና በሁለተኛና ሦስተኛ መልስ ሰጭዎች ላይ በመሠረቱት ክስ፣ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 22 ቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 13-15 የጉንደር ቡና ቤት ያለበት ሕንፃ ምርጫ ቤታቸው መሆኑንና በአዋጅም ያልተወረሰ መሆኑ ተረጋግጦ የቤት ቁጥር 013 የጉንደር ቡና ቤትና ምድር ቤቱ ለአሁኑ 1ኛተጠሪዎች በንብረትነት መፈቀዱን ገልፀው የአሁኑ አመልካች በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቤቱን ስላላስረከቡ ከሰኔ 1 ቀን 1986 ዓ.ም ጀምሮ ቀደም ሲል በወር 1300 (አንድ ሺ ሦስት መቶ ብር) የነበረው የቤት ኪራይ የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ባወጣው አዲስ ተመን መሠረት ለባለንብረቱ በስድስት ተባዝቶ ማለትም 1300X6= 7,800 (ሰባት ሺ ስምንት መቶ ብር/ ለከሣሽ መክፈል ስላለበት ከሰኔ 1 ቀን 1986 እስከ ጥቅምት ወር 1987 የ5 ወር ሂሣብ ብር 39,000 (ሰላሣ ዘጠኝ ሺ)ብር 1ኛ ተከሣሽ እንዲከፍል፤ ሁለተኛ ተከሣሽ ከአንደኛ ተከሣሽ ጋር ያለው ኪራይ በመቋረጡ ከሰኔ 1986 ጀምሮ ኪራይ መቀበሉን እንዲያቋርጥ እስከ ጥቅምት ወር 1987 የተቀበለውን ብር 6,500 (ስድስት ሺ አምስት መቶ) ለከሣሽ እንዲከፍል፣ ሦስተኛ ተከሣሽ ለከሣሽ የባለቤትነት ደብተር እንዲሰጥ ጠይቀዋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ፣ አንደኛ ተከሣሽ (የአሁኑ አመልካች) ቀደም ሲል በወር በብር 1300 ከኪራይ ቤቶች ተከራይቶት የነበረውን ቤት ለከሣሾች እንዲያስረክቡ ለአሁኑ ሁለተኛ መልስ ሰጭ የከፈሉት የኪራይ መጠን ታሣቢ ሆኖ በአዲሱ ተመን (የሚኒስቴር መ/ቤቱ ባወጣው)መሠረት የቤቱ ኪራይ በስድስት ተባዝቶ ከሰኔ 1 ቀን 1986 እስከ ጥቅምት ወር 1987 ያለው ብር 39,000(ሰላሣ ዘጠኝ ሺ) እንዲከፍሉ፤ የአሁኑ ሁለተኛ መልስ ሰጭ ከንብረቱ መመለስ በኋላ የተቀበለውን የኪራይ ልዩነት ለከሣሾች እንዲመልስ፤ በመጨረሻም የባለቤትነት ማረጋገጫ ሠነድ የሦስተኛ ተከሣሽ የነበረውን ኃላፊነት የወሰደው ክፍል እንዲሰጣቸው ተወስኗል፡፡

ይህ የሰበር ቅሬታ የቀረበው የአሁኑ አመልካች የካቲት 14 ቀን 1998 ጽፎ ባቀረበው የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ መነሻነት ነው የአሁኑ አመልካች በሰበር ቅሬታ ማመልከቻው ለአሁኑ 1ኛ ተጠሪዎች ይመለስ የተባለውን ድርጅት ከታህሣሥ 29 ቀን 1959 ጀምሮ በድርጅትነት ሲገለገሉበት የቆዩ መሆኑንና ተገቢውንም የቤት ኪራይ ያለማቋረጥ ቀደም ሲል የቤቱ ባለቤት ለነበረው አከራይ ሲከፍሉ መቆየታቸውን ገልፀው፣



የቤቱ ኪራይ በስድስት ተባዝቶ በወር 7800 ብር ሂሣብ ከሰኔ 1 ቀን 1986 ጀምሮ ያለው ለ1ኛ መልስ ሰጭዎች ይክፈሉ መባሉ ሕግና ሥርዓትን የተከተለ አይደለም፣ የሚኒስቴር መ/ቤቱ አወጣው የተባለውም መመሪያ ከ10 ዓመት በፊት በሥራ ላይ እንዳይውል ተብሎ የታገደና ከአዋጁ ጋር የሚቃረን ነው በማለት ነው፤ ይህ ችሎት ታህሣሥ 5 ቀን 1999 በዋለው ችሎት የግራ ቀኙን የቃል ክርክር አድምጧል፡፡

በዚህ ጉዳይ የአሁኑ አመልካች ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ሲገለገሉበት የቆየው የድርጅት ቤት ለአሁኖቹ አንደኛ ተጠሪዎች ተከለከለ በሚል ኪራዩ በስድስት ተባዝቶ ያለው ውዝፍ ይክፈል መባሉ በአግቡ መሆን አለመሆኑን ይህ ችሎት መርምሯል፡፡

ይህ ችሎት ከጉዳዩ- አጠቃላይ ሁኔታ መረዳት የቻለው ነገር ቢኖር፣ የአሁኑ አመልካች የተጠቀሰውን የድርጅት ቤት ለረጅም ዘመናት የቤቱ ባለቤት ከነበረውና ቤቱን በኪራይ ውል አከራይቷቸው ከነበረው ከ2ኛ ተጠሪ ተከራይተው የኪራይ ውሉ ፀንቶ እስከቆየበት ጊዜ ድረስ ተገቢውን የኪራይ ገንዘብ ለ2ኛ ተጠሪ ሲከፍሉ መቆየታቸው ተረጋግጧል፡፡

የአሁኑ አመልካች የውል ግዴታቸውን በዚህ ሁኔታ ሲወጡ ከመቆየታቸው ውጭ ቤቱ ተመልሶላቸው ከተባሉት ከአሁኖቹ አንደኛ ተጠሪዎች ጋርም ያደረጉት የኪራይ ውል የሌለ መሆኑን ከሥር ክርክሩ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ከሁሉም በላይ የአሁኑ አመልካች የገበያ ዋጋን ለማረጋጋት በሦስትኛ አካል ማለትም በሚኒስቴር መ/ቤት ወጣ ተብሎ በተነገረው መመሪያ ለመገዛት ወደውና ፈቅደው ስለመስማማታቸው የተረጋገጠ አንዳችም ነገር ሣይኖር የሥር ፍ/ቤት የውሉችን መሠረታዊ ጽንሰሐሣብ በሚንድ ሁኔታ የአሁኑ አመልካች በቤቱ ላይ የባለቤትነት መብት በሌለው አካል በተወሰነው መመሪያ መሠረት አመልካች የድርጅት ኪራዩን በስድስት ተባዝቶ ይክፈል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፤ በተጨማሪ ይዞታውን ያስረክቡኝ ተብሎ ለቀረበ ክስ የቤቱ ዋጋ ተገምቶ የዳኝነት ይክፈል መባሉ ስህተት ነው ብለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጥር 26 ቀን 1996 በመ/ቁ. 02631 የአሁኑ አመልካች በአዲስ ተመን መሠረት የመረከብ ግዴታ ያለባቸውን ልዩነት ከሰኔ 1 ቀን 1986 እስከ ጥቅምት ወር 1987 ብር 39,000 (ሰላሣ ዘጠኝ ሺ) እንዲከፍሉ በማለት የሰጠውም በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 29090 በ25/4/98 ያፀናው የውሣኔ ክፍል ተሽሯል፣

- የአሁኑ አመልካች ረቺ በመሆናቸው በሥር ፍ/ቤት ከፍ ብሎ በተገለፀው የመ/ቁጥር እና ቀን እንዲከፍሉ የተወሰነው የዳኝነትና የጠበቃ አበል ተሽሯል፡፡
- የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፣
- መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሰበር መ/ቁ. 14493

መጋቢት 13 ቀን 1999 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** የኢት/የ ልማት ባንክ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሚደቅሳ ቱሉማ

*የውል ክርክር - የብድር ውል - የሽያጭ ውል - ስለ ውል ትርጉም - በተንኮል የተፈጸመ ውል - የፍ/ብ/ህግ ቁ. 2298፣ 1733 - የሰ. 14493*

አመልካችና ተጠሪ ያደረጉት የብድር ውል ፈርሶ ከውሉ በፊት ወደነበሩበት ቦታ ሊመለሱ ይገባል ሲሉ የአዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ በመቃወም የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የአዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ግልጽ ሆኖ ከሚሰማው በመራቅ የተዋዋዮች ፍቃድ ምን እንደነበር ዳኞች ለመተርጐም አይችሉም፡፡



ሰበር መ/ቁ. 14493

መጋቢት 13 ቀን 1999 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** የኢት/የ ልማት ባንክ ነገረፈጅ አቶ አክሊሉ ተስፋዬ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሚደቅሳ ቱሉማ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

መዝገቡን መርምረን እንደተረዳነው አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት ግራ ቀኙ ሐምሌ 15 ቀን 1988 ዓ.ም ያደረጉት ስምምነት ይዘት የገንዘብ ብድርን የሚያመለክት ነው ወይስ የወፍጮ ሽያጭን? በሚለው ነጥብ ላይ ነው የሥር ፍ/ቤቶችም ለዚህ ጭብጥ የእራሣቸውን ትንታኔ በመስጠት በዚህ ጉዳይ አመልካች የኢት/የ ልማት ባንክ የብድሩን ገንዘብ አበዳሪ ሣልሆን የወፍጮው ሽያጭ ነው የሚለውን በመያዝና በተሸጠው ወፍጮ ለታየው ጉድለት ሻጩ ኃላፊ ነው በማለት ውል ሊፈርስ ይገባል በማለት ውሣኔ የሰጠበት መሆኑን ነው፡፡

ይሁን እንጂ በአመልካች በኢት/የ ልማት ባንክ እና በሌላ ግለሰብ መካከል በተነሣው ክርክር ይኸው ጉዳይ ተነስቶ ይኸው ሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መ/ቁ.15662 ለክርክሩ መነሻ የሆነው ተመሣሣይ ስምምነት ለአመልካች የብድር ገንዘብን የሰጠ መሆኑን የሚያመለክት እንጂ የወፍጮ ሽያጭ መሆኑን የማያመለክት መሆኑን ገልፆ ዳኝነት የሰጠበት በመሆኑ ይህም ጉዳይ በዚያው አንፃር ታይቶ ተፈርዷል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

በዚህ ጉዳይ የአዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ. 449/91 ግንቦት 04 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠውና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትም የቀረበለትን ይግባኝ ተመልክቶ የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት በመ/ቁ. 2415/95 ህዳር 10 ቀን 1996 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) ተሽሯል፡፡

ይህ ጉዳይ ስላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰ/መ/ቁ. 18768

*ሚያዚያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም*

**ዳኞች፡-** *አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ*

*አቶ አሰግድ ጋሻው*

*አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ*

*ወ/ት ሂሩት መሰሠ*

*አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ*

**አመልካች** ፡- ወ/ሮ ዓለሚቱ አግዛቸው

**ተጠሪ** ፡- እነ ወ/ሮ ዝናሽ ኃይሌ

*የውል ክርክር - የውል መፍረስ፣ የቤት ሽያጭ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1771(1)፣ 1785(2)፣ 1789*

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያደረጉት ውል አመልካች ስም እንዲዛወር ፈቃደኛ ስላልነበሩ ውሉ ፈርሶ ተዋዋይ ወገኖች ወደ ነበሩበት ሊመለሱ ይገባል ሲል የሰጠውን ውሣኔ በማጽናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

**<u>ውሣኔ፡ -</u>** የፌዴራል መጀመሪያና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. ተዋዋይ ወገኖች መሰረታዊ ያልሆኑና ጥቃቅን የሆኑ ምክንያቶችን ብቻ በመስጠት ውል ማፍረስ እንዳይችሉ ዳኞች ውሉ እንዲፈርስ ሊያደርጉ የሚችሉት ውሉ ባይፈርስ ከፍ ያለ ችግር የሚያስከትል ከሆነ ብቻ ነው፡፡
2. የውል አብዛኛው ግዴታ በተፈፀመ ጊዜ የተወሰነ ቀሪ ገንዘብ አለመከፈሉ ውሉን ለማፍረስ የሚያበቃ መሠረታዊ የሆነ የግዴታ መጣስ የሚያሰኝ ምክንያት አይደለም፡፡



የሰ/መ/ቁ. 18768

*ሚያዚያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም*

**ዳኞች፡-** 1. *አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ*

2. *አቶ አሰግድ ጋሻው*

3. *አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ*

4. *ወ/ት ሂሩት መሰሠ*

5. *አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ*

**አመልካች** ፡- ወ/ሮ ዓለሚቱ አግዛቸው - ወኪል አቶ አግዛቸው ገ/ሚካኤል ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ** ፡- እነ ወ/ሮ ዝናሽ ኃይሌ - ቀረቡ፡፡

*መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡*

**<u>ፍ ር ድ</u>**

በዚህ መዝገብ የቀረበው የውል መፍረስን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪዎች በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ በወረዳ 15 ቀበሌ 26 የሚገኘውን ቁጥር 495 የሆነውን ቤት አሁኗ አመልካች ብር 9.000/ዘጠኝ ሺ.ህ/ ሽጠው ብር 6.000/ ስድስት ሺ.ህ/ ከተከፈላቸው በኋላ ቀሪውን ገንዘብ አመልካች ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ውሉ ቀሪ ሆኖ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ጠይቀዋል፡፡

አመልካችም ቀሪ ገንዘባቸው ያልተከፈላቸው በውሉ ላይ የተመለከተውን ግዴታዎች ባለመወጣታቸው በመሆኑ ውሉ ሊፈርስ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በውሉ መሠረት ስም እንዲዛወር ፈቃደኛ ያልነበሩት አመልካች ካልሆኑ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት አመልካች የገዙትን ቤት እንዲያስረክቡና ተጠሪዎች የተቀበሉትን ብር 6.000 /ስድስት ሺ.ህ/ እንዲመልሱ በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በድምፅ ብልጫ መዝገቡን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337 መሠረት ዘግቶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም ውሉ ሊፈርስ ይገባል ወይስ አይገባም የሚለውን በመመርመር አቤቱታው ለሠበር እንዲቀርብ በማድረግ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች ለአመልካች ቤት መሸጣቸውን፣ ቤቱንም ማስረከባቸውን ከተዋዋሉት ብር 9.000 /ዘጠኝ ሺህ/ ውስጥ ብር 6.000 /ስድስት ሺህ/ መቀበላቸውን አምነዋል፡፡ ውሉ እንዲፈርስ የጠየቁት ከሺያጩ ዋጋ ቀሪው ብር 3.000 /ሦስት ሺህ/ ባለመከፈሉ ነው፡፡

ውልን ስላለመፈፀም በሚመለከተው የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1771/1/ ከተዋዋዮቹ አንዱ የውሉን ግዴታ ያልፈፀመ እንደሆነ ውሉ ያልተፈፀመለት ወገን የውሉን መፍረስ ሊጠይቅ እንደሚችል ይገልፃል፡፡ እንዲሁም የዚሁ ክፍል አንቀጽ 1789 ውሉ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ያልተፈፀመ ከሆነ ዳኞች በአንደኛው ወገን ጠያቂነት ውሉን ሊያስቀሩት እንደሚችሉም ተመልክቷል፡፡ በአንድ በኩል ህጉ ውል አልተፈፀመልኝም የሚለው ወገን ውሉ እንዲፈርስለት ለመጠየቅ እንዲችል መብት ሰጥቶታል በሌላ በኩል ግን ዳኞች በውሉ ላይ አይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ካልሆነ በቀር ውሉ እንዳያፈርሱ ህጉ ግዴታ ይጥልባቸዋል /የፍ/ህ/ቁ.1785/2/ ይመለከቷል/፡፡ ተዋዋይ ወገኖች መሠረታዊ ባልሆኑና ጥቃቅን የሆኑ ምክንያቶችን ብቻ በመስጠት ውል ማፍረስ እንዳይችሉ ዳኞች ውሉ እንዲፈርስ ሊያደርጉ የሚችሉት ውሉ ባይፈርስ ከፍ ያለ ችግር የሚያስከትል ከሆነ ብቻ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የከፍተኛው ፍ/ቤት አነስተኛ ድምጽ እንዳሠፈረው የውሉ አመዛኙ ግዴታ ተፈጽሟል፡፡ ገዥ /አመልካች/ የሽያጩን አብዛኛውን ክፍያ ፈጽመው ቤቱንም ተረክበዋል፡፡ አልተፈፀመም የሚባለው ቀሪው የብር 3,000 /ሦስት ሺህ/ ክፍያ ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ውሉን ለማፍረስ የሚያበቃ መሠረታዊ የሆነ የግዴታ መጣስ የሚያሠኝ ምክንያት አይደለም፡፡

በዚህም መሠረት ቀሪው ገንዘብ አልተከፈለም በማለት ውሉ እንዲፈርስ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 29696 ሰኔ 4/1996 የሰጠው ውሳኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 32497 ጥር 30/1997 በአብላጫ ድምጽ የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የቤት ሽያጭ ውል ሊፈርስ አይገባም፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡



የሰ/መ/ቁ/ 21448
ሚያዚያ 30/1999

ዳኞች፡- አቶ መንበረጸሐይ ታደሰ
አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ት ሂሩት መለሰ
አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ ኀርፌ ወርቅነህ
መ/ሰጭዎች፡- እነ ወ/ሮ አበራሽ ደባርጌ

*የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል - የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል አፃፃፍ ፎርም - የሽያጭ ውልን ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው ወይም በፍርድ ቤት ፊት ስለማድረግ - የሽያጭ ውልን በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ መመዝገብ - የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1723፣ 1727፣ 2877፣ 2878፡፡*

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመልስ ሰጭዎችና በአመልካች አውራሽ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል በህጉ ተቀባይነት ያለው ነው ሲል የሰጠውን ውሳኔ በማፅናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሳኔ</u>፡- የፌዴራል መጀመሪያና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡

1. የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከቱ ውሎች በህግ ፊት የሚፀኑ እንዲሆኑ ሁለት መስፈርቶችን ሚሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የመጀመሪያው መስፈርት ውሉ በፁሁፍ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ውሉ በአዋዋይ ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ፊት መከናወኑ ነው፡፡
2. የፍ/ብ/ህግ ቁ.1723(1) የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በአዋዋይ ወይም በፍርድ ቤት ፊት እንዲደረግ የሚጠይቀው በተዋዋዮች መካከል በሕግ ፊት የሚፀና ውል እንዲኖር ለማድረግ ነው፡፡
3. የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2878 የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ምዝገባ እንዲከናወን የሚጠይቀው ውሉ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረው ለማድረግ ነው፡፡
4. ልዩ ህግ ከአጠቃላይ ህግ ቅድሚያ ይሰጠዋል (the special prevails over the general) የሚለው የተለመደው የህግ አተረጓገም ስልት ተግባራዊ የሚሆነው ሁለት የህግ ድንጋጌዎችን አንድ ላይ ተግባራዊ ማድረግ ሳይቻል ሲቀር ብቻ ነው፡፡
5. “ስለ ውሎች በጠቅላላው” ምዕራፍ ስር የሚገኘው የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1723 እና “ስለማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ” ስር የሚገኘው የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2877 ድንጋጌዎች መካከል ልዩነት ቢኖርም በመካከላቸው ግልፅ የሆነ ግጭት የሌለ በመሆኑና የማይንቀሳቀስ ንብረትን ባለቤትነት ለማስተላለፍ ከሌሎች ውሎች የበለጠ ጥንቃቄና ጥበቃ ስለሚሻ አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት የሽያጭ ውልን የአፃፃፍ ፎርም በሚመለከት ገዥ ድንጋጌ መሆን ያለበት የተለየና ጥብቅ መስፈረት የሚያስቀምጠው የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1723 ነው፡፡

የመ.ቁ. 21448

ዳኞች፡ - አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሃመድ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ሪት ሂሩት መለሰ

አመልካች፡ - ወ/ሮ ጐርፌ ገ/ሕይወት

መልስ ሰጪ፡ - 1) ወ/ሮ አበራሽ ዱባርጌ 2) አቶ ጌታቸው ነጋ

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የማይንቀሳቀስ ሀብት (ቤት) ሽያጭን የሚመለከት ነው፡፡ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች አቅርበውት በነበረው ከወራሽነት ጋር የተያያዘ የንብረት ክፍፍል ክስ ነው፡፡ አመልካች አባታቸው አጋዝ ገ/ሕይወት ወልደየስ ከአንደኛዋ መልስ ሰጪ ጋር በጋብቻ አብረው ሲኖሩ ያፈሩትና በወረዳ 24 ቀበሌ 09 የሚገኝና ቁጥሩ 011 የሆነ ቤት የጋራ መሆኑን በመግለጽ የሚቹን የአባታቸውን ድርሻ ያካፍሉኝ የሚል ክስ ለፍርድ ቤት አቀረቡ፡፡ ፍርድ ቤቱም ተጠቃሹ ቤት የጋራ ነው በማለት አመልካች በቤቱ ላይ ግማሽ ባለድርሻ ናቸው በማለት ውሳኔ ሰጠ፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁኑ 2ኛ መልስ ሰጪ አቶ ጌታቸው ነጋ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ይኸው ውሳኔ የኔን ይዞታ የሚያጠቃልል በመሆኑ ውሳኔው ይለወጥልኝ በማለት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁ. 358 መሠረት የመቃወም ማመልከቻ አቀረቡ፡፡ 2ኛ መልስ ሰጪ ለዚህ ማመልከቻ መሠረት ያደረጉት በ1985 ፈፀምኩ የሚሉት የሽያጭ ውል ነው፡፡ 2ኛ መልስ ሰጪ ባቀረቡት ማመልከቻ 1ኛ መልስ ሰጪና ባለቤታቸው አጋዝ ገ/ሕይወት ወልደየስ በ23/03/85 በተፃፈ የሽያጭ ውል አንድ ጅምር ቤትና 400 ካሬ ሜትር ቦታ በብር 16,500.00 (አስራ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ብር) የሸጡላቸው መሆኑን በመግለጽ ፍርድ ቤቱ ቀደም ሲል የሰጠውን ውሳኔ እንዲለውጥ ጥያቄ አቅርበዋል፡፡

የአሁን አመልካች 2ኛ መልስ ሰጪ ባቀረቡት መቃወሚያ ላይ መልስ እንዲያቀርቡ ተደርገው 2ኛ መልስ ሰጪ ገዛሁ የሚሉት ቤት የቤት ቁጥር ካልተገለፀና ደብተር ከሌለው ገዝቻለሁ ሊሉ እንደማይችሉ፣ ክርክር በተነሳበት ቤት ላይ በ1985 ዓ.ም ጅምር ቤት ያልነበረ መሆኑን፣ ሟች ውሉ በተፈፀመበት ወቅት በእድሜ የገፉና ሕመምተኛ ስለነበሩ ውሉ ተቀባይነት እንደሌለው፣ ተፈረመ በተባለው ውል ላይ ያለው የጣት ፊርማ የሟች አለመሆኑን፣ የፍርድ አፈጻጸም መምሪያ መሃንዲስ በ1992 ክርክር የተነሳበትን ቤት ማህደር በማስቀረብ የ2ኛ መልስ ሰጪ መሆኑን የሚያመለክት ሰነድ አለማግኘቱን መግለጹን በመዘርዘር ውሉ ተቀባይነት የለውም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ የአሁንዋ አንደኛ መልስ ሰጪ በሌላ በኩል ከባለቤታቸው ጋር በመሆን ውሳኔ ያረፈበትን ቤት በከፊል ለአሁን 2ኛ መልስ ሰጪ ሸጠው በውሉ መሠረት ለ2ኛ መልስ ሰጪ ያስረከቡ መሆናቸውን በመግለጽ ወደ ክርክሩ ቢገቡ ተቃውሞ እንደሌላቸው ገልጸዋል፡፡



ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት በ2ኛ መልስ ሰጪ በቀረበው የሽያጭ ውል ላይ ያለው ፊርማ የሟች የአጋዝ ገ/ሕይወት መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ጉዳዩን ለፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ ከላከ በኋላ ተመርማሪው የጣት ፊርማ በውስጡ በቂ ዝርዝር ማስረጃ የለውም በማለት ለመለየት መቸገሩን እንደገለፀለት በፍርዱ መዝግቧል፡፡ ይህ ሪፖርት ከቀረበለት በኋላ በግራ ቀኙ የቀረቡትን ምስክሮች ሠምቶ በ2ኛ መልስ ሰጪ የቀረበው የሽያጭ ውል ተቀባይነት ያለው ነው በማለት ቀደም ሲል የሰጠውን ውሳኔ በከፊል አሻሽሏል፡፡

የአሁን አመልካች በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ፍርድ ቤቱ ይግባኙን ውድቅ አድርጐታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤት የሽያጭ ውሉ ይፀናል ሲል የሰጠው ውሳኔ እንዲሻርላቸው ጠይቀዋል፡፡

መልስ ሰጪዎች የአመልካች የሰበር አቤቱታ እንዲደርሳቸው ከተደረገ በኋላ በዚህ ችሎት ፊት የቃል ክርክር ተካሂዷል፡፡

በዚህ በቀረበልን ጉዳይ መፍትሄ የሚፈልገው ዋነኛ ጥያቄ የማይንቀሳቀስ ሀብት ሽያጭ ሊከተለው የሚገባው የውል አጻጻፍ ፎርም ምን ዓይነት ነው የሚለው ነው፡፡ በዚህም መሠረት ይህ ችሎት የቤት ሽያጭን በሚመለከት በኢትዮጵያ ሕግ ማዕቀፍ አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች ዳስሷል፡፡ የማይንቀሳቀስ ሀብትን የሚመለከቱ የአጻጻፍ ፎርም ድንጋጌዎች በፍትሐብሔር ሕጉ የተለያዩ ክፍሎች የሚገኙ በመሆናቸው የነዚህን ድንጋጌዎች ግንኙነትና ልዩነትም ተመልክቷል፡፡

ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ውሳኔ የተሰጠው የቤት ሽያጭ ውል በጽሑፍ መሆኑን በቂ ነው ከሚል አጠቃላይ መንደርደሪያ የተነሳ መሆኑ ከውሳኔው አጠቃላይ ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሉ በእርግጥ ተፈጽሟል ወይስ አልተፈጸመም የሚለውን ጥያቄ ለማጣራት ማስረጃ እንዲቀርብ ከማድረጉ በስተቀር ውሉ በእርግጥ ሕጉ የሚጠይቀውን መስፈርት አሟልቷል ወይስ አላሟላም የሚለውን የሕግ ነጥብ አልተመለከተም፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ የቤቱን ሽያጭ በሚመለከት በሁለቱ ወገኖች መካከል መስማማት ነበር ወይስ አልነበረም የሚለውን የፍሬ ነገር ጉዳይ ከማጣራት አልፎ በመካከላቸው መስማማት አለ እንኳን ቢባል ሕጉ የሚፈቅደውን ሥርአት ተከትሎ የተፈጸመ ውል ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ዋነኛ ነጥብ አልተመለከተም፡፡ ይህ የሰበር ችሎት ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ የነበረውን የጣልቃ ገብነት ጥያቄ ለማስተናገድ ጣልቃ ልግባ ብሎ የጠየቀው 2ኛ መልስ ሰጪ በሕግ የሚፀና የሽያጭ ውል ነበረው ወይስ አልነበረውም የሚለው የሕግ ነጥብ ይበልጥ አግባብነት የነበረው መሆኑን ተገንዝቧል፡፡ ይህን የሕግ ነጥብ ለመፍታት ደግሞ ውሉ ላይ የነበሩ ምስክሮችን አስቀርቦ ከመስማት

ይልቅ ሕጉ የሚያስቀምጠው መስፈርት መሟላት አለመሟላቱን ማጣራት ትክክለኛው አካሄድ ነው፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ በ2ኛ መልስ ሰጪ በአንድ በኩል በ1ኛ መልስ ሰጪ እና በሟቹ ባለቤታቸው በሌላ በኩል ተፈፀመ የተባለውን የቤት ሽያጭ ውል ሕልውና ለማረጋገጥ ምስክሮችን ከመስማቱ በፊት የቀረበውን ሰነድ ሕጋዊ ጠቀሜታ መመርመር ነበረበት፡፡ በዚህ ረገድ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተከተለው አሰራር ትክክለኛ አልነበረም፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በ2ኛ መልስ ሰጪ የቀረበውን መቃወሚያ መሠረት በማድረግ ቀድሞ የሰጠውን የአመልካች የወራሽነት ጥያቄ ያሻሻለው ህዳር 23 ቀን 1985 ዓ.ም ተፈፀመ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል የሚፀና ነው በማለት ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ ቀጥሎ የቤት ሽያጭ ውል የሚፀናው ምን ምን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ ነው የሚለውን ጥያቄ እንመለከታለን፡፡

ለመቃወሚያው መሠረት የሆነው የቤት ሽያጭ ውል በመሆኑ በቅድሚያ የፍትሐ ብሔር ሕጉ የቤትን የሽያጭ ውል በማስመልከት ያሰፈረውን ድንጋጌ እንመለከታለን ቀጥሎ ደግሞ በሽያጭ ህጉ ያለው መስፈርት ከአጠቃላይ የውል ሕግ ካለው መስፈርት ጋር ያለውን ግንኙነት እንመለከታለን፡፡ የቤት ሽያጭን አስመልክቶ የሚቀርቡ ክርክሮችን በአግባቡ ለማስተናገድ አግባብነት ያላቸውን የሕጉ ድንጋጌዎች እንደነገሩ ሁኔታ የአማርኛም የእንግሊዝኛም ትርጉም እንጠቅሳለን፡፡ የማይንቀሳቀስ ሀብት ሽያጭን በሚመለከተው የፍትሐብሔር ሕግ ክፍል የሚገኙት አንቀጽ 2877 እና አንቀጽ 2878 እንደሚከተለው ይደነግጋሉ፡፡

**2877 የውሉ ፎርም**

የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በጽሑፍ ሳይደረግ የቀረ እንደሆነ ፈራሽ ነው፡፡

**2877 form of contract**

A contract of sale of an immovable shall be of no effect unless it is made in writing.

**2878 በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ስለ መፃፍ**

ያንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ንብረቱ ባለበት አገር በሚገኘው በማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ ካልተፃፈ በቀር በሦስተኛ ወገኖች ዘንድ ውጤትን ሊያስገኝ አይችልም፡፡

**2878 Registration in registers of unmovable property**

The sale of immovable shall not affect third parties unless it has been registered in the registrars of immovable property in the place where the immovable sold is situate.

ከድንጋጌዎቹ ይዘት ለመገንዘብ እንደሚቻለው አንቀፅ 2877 በተዋዋዮቹ መካከል በሕግ የሚፀና ውል እንዲኖር መሟላት የሚገባውን መስፈርት የሚመለከት ሲሆን አንቀፅ 2878 በሌላ በኩል ይኸው ውል ሦስተኛ ወገኖችን በሚመለከት ውጤት እንዲኖረው መሟላት ያለበትን መስፈርት የሚመለከት ነው፡፡ በአንቀፅ 2877 መሰረት



የሚፀና ውል አለ ለማለት በሻጩና በገዢው መካከል የጽሑፍ ውል መኖሩ በቂ ነው፡፡ ይህ መስፈርት ከውል ሕግ አጠቃላይ ድንጋጌዎች ጋር ተያይዞ ሲታይ በሻጭና በገዢ መካከል የተከናወነው የሽያጭ ውል በጽሑፍ እንዲሆንና ግዴታ ያለባቸው ተዋዋዮች እንዲፈርሙበትና ሁለት ምስክሮች እንዲያረጋግጡት የሚጠይቅ ነው (አንቀጽ 1727)፡፡ በተዋዋይ ወገኖች መካከል የፀና ውል እንዲኖር የዚሁ መስፈርት መሟላት አስፈላጊነት እንደተበጠቀ ሆኖ አንቀጽ 2878 3ኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረው ለማድረግ ተጨማሪ የምዝገባ ሥርአት መከናወን እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ ይህ የምዝገባ ሂደት መከናወን ያለበት ንብረቱ በሚገኝበት የማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ መሆኑንም ድንጋጌው ይገልጻል፡፡

የማይንቀሳቀስ ሀብት ሽያጭን በሚመለከተው የፍትሐብሔር ሕጉ ክፍል ያለው የውል አፃፃፍ ፎርምን እና ምዝገባን የሚመለከት መሰረታዊ የሕግ ማዕቀፍ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን በውል ሕግ በጠቅላላ የሚገኘው መስፈርት ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ አግባብነት ያለው የሕጉ አንቀጽ 1723 ድንጋጌ የሚከተለው ይዘት ያለው ነው፡፡

**1723 የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን የሚመለከቱ ውሎች**

(1) የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ባለቤትነት ወይም ባንድ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የአላባ ጥቅም መብት ወይም የመያዣ መብት ወይም የሌላ አገልግሎት መብት ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የሚደረጉት ውሎች ሁሉ በጽሑፍና በሚገባ አኳኋን በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው ፊት መሆን አለባቸው፡፡

(2) እንዲሁም የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከቱ የክፍያ ወይም የማዛወር ስምምነቶች ሁሉ በጽሑፍና በሚገባ አኳኋን በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው ፊት መሆን አለባቸው፡፡

**1723 Contracts relating to immovable**

(1) A contract creating or assigning rights in ownership or bare ownership on an immovable or an usufruct, servitude or mortgage of an immovable shall be in writing and registered with a court or notary

(2) Any contract by which an immovable is divided and any compromise relating to an immovable shall be in writing and registered with a court or notary.

ከአንቀጽ 1723 (1) ይዘት ለመገንዘብ እንደሚቻለው የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከቱ በርካታ ውሎች በሕግ ፊት የሚፀኑ ለመሆን ሁለት መስፈርቶችን ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የመጀመሪያው መስፈርት ውሉ በጽሑፍ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው መስፈርት ውሉ በአዋዋይ ወይም በፍርድ

ቤት መዝገብ ፊት መከናወን ነው። እነዚህ ሁለት መስፈርቶች የማይንቀሳቀስ ሀብት ባለቤትነትን ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የሚደረጉ ውሎችንም የሚመለከቱ ናቸው። የሽያጭ ውል የንብረት ባለቤትነት ከሚተላለፉባቸው መንገዶች አንዱ በመሆኑ በዚሁ ድንጋጌ ውስጥ የሚጠቃለል ነው። በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ መሠረት ቤትን የሚመለከት የሽያጭ ውል በህግ ፊት የፀና የሚሆነው በጽሑፍ ሲደረግ ብቻ ሳይሆን ይኸው የጽሑፍ ውል ሥልጣን በተሰጠው አዋዋይ ክፍል ወይም በፍርድ ቤት የተከናወነ ሲሆን ነው። የአንቀጽ 1723 ድንጋጌ አንቀጽ 2778 ካስቀመጠው መስፈርት የተለየ ተጨማሪ መስፈርት ያካተተ መሆኑ ድንጋጌዎቹን በማነፃፀር መገንዘብ የሚቻል ነው። የሽያጭ ሕጉን በተለይ የሚመለከተው ድንጋጌ የሚጠይቀው የውሉን በጽሑፍ መከናወን ብቻ ሲሆን የውል ሕግ በጠቅላላው ግን የጽሑፍን መስፈርት እንደ አንድ አስፈላጊ መስፈርት እንጂ እንደ ብቸኛ መስፈርት አይወስደውም። በመሆኑም በሽያጭ ሕግ የሚፀና የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ለማከናወን የሚጠየቀው መስፈርት በውል ሕግ ከሚጠየቀው መስፈርት የተለየ ነው። ይህ ልዩነት አንድ የሽያጭ ውል በሕግ ፊት የሚፀና መሆን አለመሆኑን ለመወሰን ገዥው ድንጋጌ መሆን ያለበት የትኛው ነው የሚለው ጥያቄ እንዲነሳ ያደርጋል። ይህን ጥያቄ ከመመልከታችን በፊት በአንቀጽ 1723 የሰፈረው ተጨማሪ መስፈርት በአንቀጽ 2878 ከሚገኘው የምዝገባ መስፈርት ጋር ያለውን ግንኙነት፣ ተመሳሳይነትና ልዩነት በአጭሩም ቢሆን መመልከት አስፈላጊ ነው። የአንቀጽ 1723 (1) የእንግሊዝኛው ትርጉም "registration" የሚለውን ቃል ከመጠቀሙ በስተቀር በሁለቱም ድንጋጌዎች መካከል ያለው ይዘት ሰፊ ልዩነት ያለው ነው። በመጀመሪያ ደረጃ አንቀጽ 2878 ምዝገባ እንዲከናወን የሚጠይቀው ውሉ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረው ለማድረግ ሲሆን አንቀጽ 1723 (1) አዋዋይ ወይም ፍርድ ቤት ፊት መቅረብን የሚጠይቀው በተዋዋዮች መካከል በሕግ ፊት የሚፀና ውል እንዲኖር ለማድረግ ነው። በመሆኑም የአንቀጽ 1723 (1) መስፈርት መሟላት ወይም አለመሟላት ሦስተኛ ወገኖችን የሚመለከት ሲሆን የኋለኛው መስፈርት መሟላት አለመሟላት ግን በተዋዋዮች በራሳቸውም ላይ የውል መኖር ወይም አለመኖር ውጤት የሚያስከትል ነው። በሁለተኛ ደረጃ በአንቀጽ 1723 (1) የሚከናወነው ተግባር የሚፈፀመው አዋዋይ ወይም ፍርድ ቤት ፊት በመቅረብ ሲሆን በአንቀጽ 2878 ያለው የምዝገባ ተግባር የሚከናወነው ንብረቱ በሚገኝበት ቦታ ነው። በአንቀጽ 1723 (1) የሚከናወነው ሂደት ተዋዋዮች አዋዋይ ፊት ቀርበው መዋዋላቸውን የሚያረጋግጡበት (authentication) ሂደት ሲሆን በ2878 የሚከናወነው ምዝገባ ሌሎች ሰዎች አንድን የማይንቀሳቀስ ንብረት በማስመልከት የተከናወኑ ሕጋውያን ተግባራት (juridical acts) ማወቅ እንዲችሉ ተግባራቱ ንብረቱ ባለበት ማህደር እንዲያያዝ በማድረግ የሚከናወን ነው። አዋዋይ ፊት ቀርቦ የመዋዋሉ መስፈርት ውሉ በተፈፀመበት ቦታ በሚገኝ አዋዋይ/ፍርድ ቤት በመቅረብ መከናወን የሚችል ሲሆን በ2878 መሠረት የሚከናወን ምዝገባ ግን የግድ ቤቱ በሚገኝበት ቦታ ባለ መዝገብ በማስገባት የሚከናወን ነው።



ከዚህ ቀጥሎ የምንመለከተው የአንድን የማይንቀሳቀስ ንብረት የሽያጭ ውል በሚመለከት ገዢው ድንጋጌ የትኛው ነው የሚለውን ነው። አሁን ከቀረበልን ጉዳይ አንፃር ዋናው ጥያቄ የአንቀጽ 2877ን የጽሑፍ መስፈርት ያሟላ ሰነ[illegible] 1723 (1) መሠረት አዋዋይ ወይም ፍርድ ቤት ፊት ካልተደረገ እንደሚፀና ውል ይቆጠራል ወይስ አይቆጠርም የሚለው ነው። በዚህ [illegible] የሚመለከተው የሽያጭ ሕግ ድንጋጌ አንድ መስፈርት ብቻ በቂ ነው ሲል ጠቅላላ የውል ሕግ ሁለት መስፈርት አስፈላጊ ነው ስለሚል በሁለቱ ድንጋጌዎች መካከል ያለውን አለመጣጣም ለመፍታት የሽያጭ ሕግ ልዩ ሕግ ስለሆነ አጠቃላይ ጉዳዮችን በሚመለከተው የውል ሕግ ላይ የበላይነት ተሰጥቶት ጉዳዩ የሽያጭ ሕግ በሚያስቀምጠው መለኪያ መሠረት መዳኘት አለበት የሚለውን አማራጭ እንደ መጀመሪያ መውሰድ ይቻላል። ይህ አማራጭ የተለመደውን ልዩ ሕግ ከአጠቃላይ ሕግ ቅድሚያ ይሰጠዋል (the special prevails over the general) የሚለውን የሕግ ትርጉም መርህ የሚከተል ነው። ይህን መርህ በመከተል ጉዳዩን ካስተናገድን የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ በጽሑፍ እስከተከናወነ ድረስ የጽሑፍ ውሉ አዋዋይ ፊት ወይም ፍርድ ቤት ፊት ባይቀርብም ተዋዋዮቹን በሚመለከት የፀና የሽያጭ ውል ለመመስረት በቂ ነው ወደሚለው መደምደሚያ እንደርሳለን።

በሌላ በኩል ይህ የአተረጓጎም ስልት ተግባራዊ የሚሆነው ሁለት የህግ ድንጋጌዎች የሚጋጩ ሲሆንና ሁለቱም ድንጋጌዎች አንድ ላይ ተግባራዊ ማድረግ ሳይቻል ሲቀር ብቻ ተፈፃሚነት የሚኖረው የአተረጓጎም ዘይቤ በመሆኑ ይህን ዘይቤ ለመምረጥ በቅድሚያ በሁለቱም ሊታረቅ የማይችል ቅራኔ መኖሩን ማረጋገጥ ይጠይቃል። የሽያጭ ሕግ በሚፀና የሽያጭ ውል ጽሑፍ ያስፈልጋል ማለቱ፣ የውል ሕግ ለሚፀና የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ከጽሑፍ በተጨማሪ አዋዋይ ፊት መከናወኑ አስፈላጊ መሆኑን ከሚገልፀው ጋር ይጋጫል? ሁለቱንም ማጣጣምስ አይቻልም? የሕጉ አንቀጽ 2877 የሽያጭ ውል በጽሑፍ ካልሆነ በቀር አይፀናም ከማለት ሌላ በአዋዋይ ፊት መከናወን አያስፈልግም የሚል ድንጋጌ የለውም። በመሆኑም የሽያጭ ሕግ በውልም ሕግ ለተጠቀሰው የጽሑፍ አስፈላጊነት አፅንኦት ከመስጠቱ ሌላ የመረጋገጥን (authentication) አስፈላጊነት አላስቀረም በማለት የሁለቱን ድንጋጌዎች ላይ ላዩን የሚታይ ቅራኔ (apparent contradiction) ማስታረቅ ይቻላል።

ከዚህ በተጨማሪ የፍትሐ ብሔር ሕጉን አደረጃጀት፣ ዓላማና ወጥነት ግምት ውስጥ ማስገባት አሁን ለተያዘው ጉዳይ የሚበጅ ነው። የፍትሐ ብሔር ሕጉ አደረጃጀት በተለያዩ መጽሐፎች የተከፋፈሉት ርእስ ጉዳዮች አንድን ዓላማ የሚያሳኩ፣ ከተመሳሳይ መሠረተ ሃሳብ የሚንደረደሩና እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው። ይህ አደረጃጀት ሕጎቻቸውን በኮድ መልክ በሚያደራጁ አገሮች (codified systems) የተለመደና የሕግ ሥርዓቱ

መገለጫ ባህርይ ነው፡፡ በመሆኑም በተለያዩ የሕጉ ክፍሎች በሚገኙ ድንጋጌዎች መካከል ቅራኔ ከማፈላለግ ይልቅ ተደጋጋፊ ሆነው የጋራ ዓላማ የሚያሳኩበትን የሕግ ትርጉም መሻት የሕግ ባለሙያዎች ሊመርጡት የሚገባ የሕግ አተረጓጎም ዘይቤ ነው፡፡ ስለዚህ ልዩ ሕግ ጠቅላላ ዓላማ ካለው ሕግ ቅድሚያ ይሰጠዋል የሚለውን ዘይቤ ተከትሎ ውሳኔ ላይ ከመድረስ በፊት በእርግጥ የማይታረቅ፣ ምክንያታዊ የሆነ፣ በላቀ የሕግ አውጪው ፍላጐት የተደገፈ ግጭት መኖሩን ማረጋገጥ ያስፈጋል፡፡

ይህ ችሎት ለማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ የውል ሕግ አንቀጽ 1723 (1) የተለየና ጥብቅ መስፈርት ያስቀመጠበት ምክንያት ለአተረጓጎሙ መነሻ መሆን ይገባዋል ከሚል መንደርደሪያ ይነሳል፡፡ የፍትሐ ብሔር ሕጉ መነሻ መሰረተ ሀሳብ በመርህ ደረጃ ለውል መመስረት የተዋዋዮች ስምምነት ብቻ በቂ ነው የሚል ሆኖ ሳለ (አንቀጽ 1719) የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በሚመለከት ግን ጠበቅ ያለ ፎርም እንዲከተሉ ይደነግጋል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሚመለከት ተዋዋይ ወገኖች ስምምነታቸውን በጽሑፍ ከማስፈራቸው በተጨማሪ አዋዋይ ፊት ወይም ፍርድ ቤት ፊት ቀርበው እንዲፈጽሙ መደንገጉ ሕጉ ለማይንቀሳቀስ ንብረት ልዩ ትኩረት መስጠት መፈለጉን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ የሕግ አውጪው ፍላጐት የማይንቀሳቀስ ንብረት ለአንድ አገር በአጠቃላይም ሆነ ለአንድ ግለሰብ በተለይ ካለው ጠቀሜታ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት ካለው ማህበራዊ ጠቀሜታ አንፃር ውሎቹ ስልጣን ባለው አካል እንዲረጋገጡ በመጠየቅ ረገድ የኢትዮጵያ ሕግ የተከተለው ሥርአት ከሞላ ጐደል ሁሉም የሕግ ሥርአት የተቀበለው ነው፡፡ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን በማስመልከት የሚፈፀሙ ውሎች ከሌሎች ውሎች ለየት ባለ ሁኔታ ሥልጣን በተሰጠው አካል ቀርበው እንዲረጋገጡ ማድረግ በአብዛኞቹ የሕግ ሥርዓቶች የሚፈፀም አካሄድ ነው፡፡ የማረጋገጡ (authentication) ሂደት ተዋዋዮቹ ትልቅ ጠቀሜታ ባለው ንብረት ላይ የሚፈጽሙት ውል ፈቅደው የሚፈጽሙት መሆኑን ከማረጋገጥ ባሻገር፣ የሚሸጠው ሰው ባለንብረት መሆኑን ለማጣራት፣ ውሉ የተፈፀመበትን ትክክለኛ ቀን ለማረጋገጥ እድል በመስጠት የንብረት መብትን ለመጠበቅ፣ የውሎች ዋስትና (security of legal transactions)ለማረጋገጥ ትልቅ ጠቀሜታ ያለው ነው፡፡ የፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1723 (1) በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚከናወኑ ዓበይት ህጋውያን ተግባራት በተለይም የባለሀብትነትን (ownership) ዓላባን (usufruct) እና የአገልግሎትን መብት (servitude) ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የሚደረጉ ውሎች የተጠቀሰውን ፎርም እንዲከተሉ የግድ ይላል፡፡ በዚህ አንቀጽ ውስጥ ከተጠቀሱት መብቶች ባለቤትነት ከሁሉም የሰፋ መብት ነው፡፡ ባለቤትነትን ማቋቋምም ሆነ ማስተላለፍም ዓላባን ወይም የአገልግሎት መብትን ከማቋቋም የበለጠ ጠቀሜታ እና ጥንቃቄ እንደሚያስፈልገው እሙን ነው፡፡ ባለቤትነትን ማስተላለፍ ከሌሎች በአንቀጽ 1723 (1) ከተጠቀሱት ሕጋውያን ተግባራት የበለጠ ጥንቃቄና ጥበቃ የሚሻና የሚገባው እንደመሆኑ ሕግ አውጪው የባለቤትነት መብትን ለሚያስተላልፍ የሽያጭ ውል አላባን ወይም የአገልግሎት መብትን ለማቋቋም ከሚደረጉ ውሎች ያነሰ ጥበቃ ያደርጋል ተብሎ አይገመትም፡፡ የሕጉን አንቀጽ 2877 በተናጠል በመመልከት የሽያጭ ውል በጽሑፍ ብቻ መደረጉ በቂ ነው፣ አዋዋይ ወይም



ፍርድ ቤት ፊት መከናወን አያስፈልገውም ወደሚል መደምደሚያ መድረስ ከሁሉም በላይ ጥንቃቄ

የሚያስፈልገው የባለቤትነት ማስተላለፍ ጉዳይ ልል በሆነ ፎርም እንዲከናወን ማድረግን የሚያስከትል በመሆኑ ከሕጉ አጠቃላይ ዓላማ ጋር የሚጣጣም ነው አንልም፡፡ በመሆኑም የማይንቀሳቀስ ንብረትን በሚመለከት የሚደረጉ የሽያጭ ውሎች በጽሑፍ ብቻ ሳይሆን አንቀጽ 1723 (1) በሚጠይቀው መሠረት አዋዋይ ወይም ፍርድ ቤት ፊት መከናወን ይገባቸዋል፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው በአንቀጽ 1723 (1) የሰፈረው የማረጋገጥ (authentication) መስፈርት ውሉ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረው ብቻ መከናወን ያለበት ሳይሆን ውሉ በተዋዋይ ወገኖች መካከል ውጤት እንዲኖረውም ጭምር መከናወን ያለበት ነው፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከት የሽያጭ ውል የአንቀጽ 1723(1)ን መስፈርት የማያሟላ ከሆነ በሕጉ አንቀጽ 1720 (1) መሠረት ውሉ እንደረቂቅ ብቻ ሆኖ ከሚቆጠር በስተቀር የሚፀና ውይ አይሆንም፡፡

አሁን በቀረበልን ጉዳይ 2ኛ መልስ ሰጪ አለኝ የሚሉት የሽያጭ ውል በጽሑፍ መሆኑ ተገጋግጦአል፡፡ ሆኖም የሽያጭ ውሉ በአዋዋይ ፊት ያልተከናወነ በመሆኑ ውሉ መፈፀሙ ራሱ አከራካሪ ሆኖአል፡፡ ሕግ አውጪው ቤትን የሚመለከቱ መሠረታዊ ውሎች በ1723 (1) የተጠቀሱ ውሎች አዋዋይ ፊት እንዲከናወኑ የሚፈልገውም የኋላ ኋላ የሚነሱትን የዚህ አይነት አለመግባባቶች ቀድሞውኑ ለማስወገድ ነው፡፡ ውሉ በአዋዋይ ፊት ወይም በፍርድ ቤት ቀርቦ ያልተረጋገጠ መሆኑን ሲገነዘብ ፍርድ ቤቱ ውሉ እንደረቂቅ እንደመቁጠር ነበሩ የተባሉትን ምስክሮች በመስማት በሕግ ሕልውና የሌለው ውል ተቀባይነት እንዲያገኝ ማድረጉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡

የአሁን ተቃዋሚ በፍትሐ ብሔር ሕግ አንቀጽ 1723 (1) መሠረት አዋዋይ ፊት ወይም ፍርድ ቤት የተረጋገጠ የቤት ሽያጭ ውል ባለማቅረቡ ፍርድ ቤቱ ቀደም ሲል የሰጠውን ውሳኔ ለመቃወም የሚያበቃ ህጋዊ መብት የለውም፡፡ ፍርድ ቤቱም ይህን መሠረት በማድረግ የቀረበለትን ኑዛዜ በከፊል ማሻሻሉ ትክክለኛ አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ሊሻር የሚገባው ነው፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይህን ስህተት ማረም ሲገባው የቀረበለትን ይግባኝ አያስቀርብም በማለት መዝጋቱ ትክክል አልነበረም፡፡

**<u>ውሳኔ</u>**

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 09823 ሐምሌ 14 ቀን 1986 የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 33751 ሰኔ 14 ቀን 1997 የሰጠው ውሳኔ ተሽረዋል፡፡
2. የአሁንዋ አመልካች በወረዳ 24 ቀበሌ 09 በቤት ቁጥር 011 ላይ እኩል ባለድርሻ ናቸው በማለት በ16/3/92 ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ በ23/3/85

የአሁን 2ኛ መልስ ሰጪ ፈፀምኩ በሚለው የሽያጭ ውል ምክንያት ሊሻሻል አይገባም ብለናል፡፡



የሰበር መ/ቁ 15557

መጋቢት 18 ቀን 1999 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

ወ/ት ሂሩት መለሰ

አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አልማዝ ዓለማየሁ

**ተጠሪ፡-** አቶ ብርሃኑ ተሊላ

*የአፈጻጸም ክርክር - የጋራ ሀብት በፍርድ አፈጻጸም የሚከበርበትና በሐራጅ የሚሸጥበት ሁኔታ - የከተማ ቦታ ይዞታ - የባልና ሚስት የጋራ ሃብት*

የአፋር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪው በአፈጻጸም ከአዋሽ ማዘጋጃ ቤት የተረከበው ቦታ የፍርድ ባለዕዳው ከነበረው ቦታ የበለጠ ቢሆንም በአፈጻጸሙ አጋጣሚ ቅድሚያ የተመራ ስለሆነ ለእሱ ሊደለደል ይገባዋል እንዲሁም በፍርድ ቤቱ ተይዞ የንብረቱ ግምት ግማሽ ገንዘብ ለተጠሪው ሊመለስ ይገባል ሲል የወሰነውን ውሣኔ በመቃወም የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

**<u>ውሣኔ፡ -</u>** የአፋር ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሮ የዞን 3 ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ትእዛዝ ጸንቷል፡፡

> ማዘጋጃ ቤት በፍርድ ቤት በታዘዘ የአፈጻጸም ጉዳይ በስህተት ቦታ ለክቶ አስረክቦኛል ግብርና የስም ማዛወሪያ ከፍዬበታለሁ የሚለው መከራከሪያ ነጥብ የቦታ ባለይዞታ ለማድረግ የሚያበቃ አይደለም፡፡

የሰበር መ/ቁ 15557

መጋቢት 18 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

አሰግድ ጋሻው

መስፍን ዕቁበዮናስ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ ዓለማየሁ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ብርሃነ ተሊላ አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍርድ

ይህ የሰበር ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው የአፋር ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ጉዳይ በይግባኝ ተመልክቶ በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 15/94 የካቲት 18 ቀን 1996 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ አመልካች ቅር ተሰኝተው የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩም ባጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

ተጠሪ አቶ ብርሃነ ተሊላ በአሁን አመልካች ባለቤት በአቶ ዮሐንስ ገ/ስላሴ ላይ ብር 18,794.15 አስፈርደዋል፡፡ ሆኖም ይህ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በክርክር ላይ እያለ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ በሚል የዕግድ ትዕዛዝ የተላለፈበት ንብረት የአቶ ዮሐንስ ገ/ስላሴ ብቻ ሳይሆን ከእኔ ከአመልካች ጋር በትዳር እያለን የተፈራ፤ የተገኘ በመሆኑ የእኔ ድርሻ ሊነካብኝ አይገባም በሚል ጣልቃ ገብታ አመልካች በመከራከሯ እንደ አቤቱታዋ ዕግድ ከተሰጠበት ንብረት ግማሹ የአመልካች መሆኑ የተጠበቀ ነው በሚል ፍርድ አርፎበታል፡፡

እንዲሁም ይኸው ንብረት በአፈፃፀም ተይዞ በብር 25,000.00 ግምት መነሻ እንዲሸጥ በተባለ ጊዜ ግማሹ የአመልካች መሆኑ ተጠብቆ ንብረቱ በሐራጅ እንዲሸጥ ተደርጎ ገዥ ባለመቅረቡ ምክንያት እንደ መጨረሻ አማራጭ የፍርድ ባለመብት የአሁን ተጠሪ ከግምቱ ብር 25,000.00 የሆነበትን /የአመልካችን ግማሽ ድርሻ ብር 12,500.00/አስራ ሁለት ሺህ ከፍሎ ንብረቱን እንዲረከብ ታዟል፡፡



ተጠሪም ይህንኑ ገንዘብ በሞዴል 85 አስይዤ ቦታውንም የአዋሽ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ለክቶ አስረክቦኝ አስፈላጊውን የመንግስት ውዝፍ ግብር ከከፈልኩ በኋላ ካርታ እንዲሰጠኝ ሳመለክት እንድረከብ ከተወሰነው ቦታ ተከፍሎ ለአሁን አመልካች እንዲሰጥ ታዝዣለሁ በማለት ማዘጋጃ ቤቱ እንደ ውሳኔው ሊያስፈፅምልኝ ስላልቻለ፡-

1. በሞዴል 85 የተያዘው ገንዘብ ለአመልካች እንዳይከፈልብኝ
2. እንድረከብ ለተደረገው ንብረት ተቀርሶ ለአመልካች እንዳይሰጥብኝም የማገጃ ትዕዛዝ ለማዘጋጃ ቤቱ እንዲተላለፍልኝና
3. የፍርድ ባለዕዳው የአቶ ዮሐንስ ገ/ስላሴ የቦታ ይዞታ ፋይል ቀርቦ ታይቶ ንብረቱን እንድረከብ ይደረግልኝ በማለት በት/ፋ/መ/ቁ 11/94 ለዞን 3 ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርቧል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤትም በዚህ ጉዳይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የአሁን ተጠሪ በአፈፃፀም ይረከብ የተባለው ይዞታ የፍርድ ባለዕዳውን የአቶ ዮሐንስ ገ/ስላሴን ነው፡፡ የፍርድ ባለዕዳው ይዞታ ስፋት ደግሞ 600 ካሬ ሜትር እንደሆነ በማዘጋጃ ቤት ተረጋግጧል፡፡ ይሁን እንጂ የፍርድ ባለመብቱ ከዚህ ወጭ የፍርድ ባለዕዳውን ወንድም የአቶ ገ/እግዚአብሔር ገ/ስላሴን 200 ካሬ ሜትር እና በትርፍነት የሚገኘውን 355 ካሬ ሜትር ጭምር በስህተት ደርቦ እንዲረከብ የተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ስለሆነም አመልካች የባለቤቷ ወንድም በግንባር ተገኝቶ እስከሚረከብ ድረስ ይህንኑ 200 ካሬ ሜትር በአደራ እንድትይዝ በትርፍነት የሚገኘውንም 358 ካሬ ሜትር ማዘጋጃ ቤቱ በስሟ እንዲያዘዋውርላት ከዚህ በቀር ተጠሪው ሊረከብ የሚገባው የፍርድ ባለዕዳውን ይዞታ 600 ካሬ ሜትር ሊሆን ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርቧል፡፡

የጠ/ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙ በተገኙበት ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በትርፍነት ተገኝቷል የተባለውን ቦታ በሚመለከት ትርፍ እስከሆነ ድረስ ማዘጋጃ ቤቱ ለፈለገው ሰው መደልደል /መስጠት/ ይችላል፡፡ሆኖም ይህንኑ ቦታ ማዘጋጃ ቤቱ በመጀመሪያ ተጠሪው /እንዲረከብ/ ለክቶ እንዲረከብ ካደረገ በኋላ ከአምስት ወር ቆይታ በኋላ ደግሞ ለአመልካች እንዲሰጥ አድርጓል፡፡አንድን ቦታ ለሁለት ሰዎች በአንድ ጊዜ መስጠት አይቻልም፡፡ ስለሆነም ለማን ይሰጥ የሚለው ጉዳይ በቅድሚያ

ለማን ተስጥቶ ነበረ ከሚለው አንፃር መታየት ስላለበት ይኸው 358 ካሬ ሜትር ቦታ ለተጠሪ ይገባል እንዲሁም በሞዴል 85 ተይዞ የነበረው ገንዘብ ለአመልካች መስጠቱ ቀርቶ ለተጠሪው ይመለስ በማለት ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል የተባለው የቅሬታ ነጥብም ክርክር ባስነሳው ትርፍ ቦታ ላይ ከተጠሪ በፊት በቦታው ላይ የቆየሁበት በመሆኑ በመሬት ወይም በምሪት አሰጣጥ ላይ የቀዳሚነት መብት የእኔ ሆኖ እያለ ለተጠሪ ይሰጥ በማለት የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት መወሰኑ የህግ አግባብን የተከተለ አይደለም፡፡

እንዲሁም በሞዴል 85 የተያዘው ብር 12,500.00 የእኔ የሚስት ድርሻ ሆኖ እንዲከፈል የተወሰነው ለጠ/ፍ/ቤቱ ይግባኝ ምክንያት በሆነው የትዕዛዝ ፋይል መዝገብ በአለመሆኑ በይግባኝ መዝገቡ ላይ በዚህ አኳኋን መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ፈፅሟልና ይሻርልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪም ቀርቦ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በይግባኝ አይቶ የሰጠው ውሳኔ የህግ ግድፈት የለበትም የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር መልስ ሰጥቷል፡፡

እኛም ጉዳዩን ተመልክተናል፡፡

እንደተመለከትነውም ለዚህ ክርክር መነሻ የሆነው የአሁን ተጠሪ ከሳሽ የአመልካች ባለቤት አቶ ዮሐንስ ገ/ስላሴ ደግሞ ተከሳሽ ሆነው በፍ/ብ/መ/ቁ 8/90 በከፍተኛው ፍ/ቤት በመከራከር ላይ እያሉ የአሁን አመልካች ባለቤቴ አመጣው በተባለው ዕዳ ምክንያት የእኔ የጋራ ሀብት በሆነው ቤት ላይ የዕግድ ትዕዛዝ መተላለፉ ተገቢ አይደለም፡፡ ስለሆነም ጣልቃ ገብቼ ልከራከር በማለት ባቀረበቺው ጥያቄ የክርክሩ ተካፋይ ከሆነች በኋላ የከፍተኛው ፍ/ቤት የአመልካች ባለቤት በሥራው ምክንያት ላጐደለው ብር 18,794.15 ባለዕዳ ነው፡፡ የዕግድ ትዕዛዝ የተላለፈበትን ቤት አመልካች በሚስትነታቸው አብረው የሰሩት መሆኑን በማስረጃ ስላረጋገጠ ድርሻቸው ሊነካባቸው አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ መሠረት እንዲፈፀም በአፈፃፀም መ/ቁ 3/93 የአፈፃፀም ክሱ ቀጥሎ በብር 25,000.00 ግምት መነሻ ይህንኑ የጋራ ቤት የሚገዛ ገዥ ባለመገኘቱ አመልካች ግማሹን መክፈል ከቻለች ቤቱን እንድታስቀር ተብሎ ቢታዘዝም ይህንን መፈፀም ባለመቻሏ ተጠሪው ብር 12,500.00 የአመልካችን ድርሻ በሞዴል 85 አስይዞ ንብረቱን ስለዕዳው እንዲረከብ በሚል የታዘዘ ስለመሆኑ ከመዝገቡ ግልባጭ ተገንዝበናል፡፡

ይህም ከሆነ የፍርድ ባለመብቱ የአሁን ተጠሪ ስለዕዳው ሊረከበው የሚገባው ቤትና ይዞታው ይህንኑ በአፈፃፀም ምክንያት ይሸጥ የተባለውንና በባለዕዳው በአቶ ዮሐንስ ገ/ስላሴ ስም ተመዝግቦ የሚገኘውን ነው፡፡ ይህ ቦታ እና ይዞታ ደግሞ በፊቱ 650 ሜትር ካሬ ብቻ እንጂ ከዚያ ያልዘለለ ስለመሆኑ በባለሙያ በማዘጋጃ ቤቱ ተረጋግጧል፡፡ ይህንኑ ቤት ከእነ ትክክለኛ ይዞታው ተለክቶ እንዲረከብ ማድረግ ሲገባ በዕዳ ከተያዘው ንብረት ውጭ መሰራቱ እና እንዲረከብ ጥረት መደረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘውም፡፡ የማዘጋጃ ቤቱ ይህንኑ 600 ሜትር ካሬ፣ የአቶ ገ/እግዚአብሔር ገ/ስላሴን ይዞታ 200 ሜትር ካሬ እና ክርክር ያስነሳውን ትርፍ ቦታ እንድረከብ ለክቶልኛል፡፡ ግብር ና የስም ማዛወሪያ ከፍዬበታለሁ የሚለው መከራከሪያ ነጥብ የዚህ ሁሉ ቦታ ባለይዞታ ለማድረግ የሚያበቃ አይደለም፡፡ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ፍርዱን በአፈፃፀም ተከካሹ ወይም በፍርድ ባለዕዳው ንብረት ላይ ብቻ ማስፈፀም ሲገባው የማዘጋጃ ቤቱ የፈፀመውን ስህተት እንደ መነሻ በመውሰድ ይህንኑ ትርፍ ቦታ በቅድሚያ የተመራው የፍርድ ባለመብቱ የአሁን ተጠሪ ነው፡፡ ስለሆነም ለእርሱ ሊደለደል ይገባል ሲል የሰጠው ውሳኔ የአፈፃፀም ሥርዓቱን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል የአመልካች ባለቤት በተከሰሰበት ጉዳይ አመልካች ጣልቃ ገብታ ተከራክራ በክሱ ምክንያት ቦታ በታገደው ንብረት ላይ ያላት ድርሻ የተጠበቀ ነው በሚል ፍርድ አርፎበታል፡፡ የጣልቃ አግባብ ሥርዓቱ ተገቢ አይደለም በሚል የይግባኝ አቤቱታ ቀርቦ የታረመ ስለመሆኑም አልተመለከተም፡፡ ከዚህ በላይ በአፈፃፀም መ/ቁ 3/93 ከንብረቱ ሽያጭ ግማሹ ብር 12,500.00 የሚስት/የአመልካች ድርሻ ሆኖ በሞዴል 85 እንዲያዝ ተደርጓል፡፡ ይህ መሆኑ እየታወቀ በአፈፃፀም ምክንያት ልረከብ የሚገባው ይዞታ ምን ያህል ሊሆን ይገባል የሚለውን በሚመለከት ክስ ላይ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይኸው በአደራ ተይዞ የነበረው ገንዘብ ወጭ ሆኖ ለተጠሪው ይመለስ ሲል የሰጠው ዳኝነት ህጋዊ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ ለምን ቢባል ይሸጥ ከተባለው ንብረት ላይ ግማሹ የአመልካች ድርሻ መሆኑ ለአፈፃፀሙ ምክንያት በሆነው በዋናው ጉዳይ በመ/ቁ 8/90 ውሳኔ ያረፈበት ከመሆኑም በላይ ጠ/ፍ/ቤቱ በይግባኝ ለተመለከተው ጉዳይ መነሻ በሆነው በመ/ቁ 11/94

በሞዴል 85 የተያዘው ገንዘብ የይዞታው መጠን ታይቶ ውሳኔ እስኪሰጠው ድረስ ይህ ገንዘብ ሳይከፈል ታግዶ ይቆይልኝ በሚል እንጂ ይመለስልኝ በሚል ዳኝነት አልተጠየቀበትም፡፡ ይህን ሳይረዳ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት በሞዴል 85 የተያዘው ገንዘብ ይመለስ ሲል መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡

## ውሳኔ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 15/94 ታህሳስ 28 ቀን 1996 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ የተሻረ ሲሆን በአንፃሩ የዞን ሦስት ከፍተኛ ፍ/ቤት በት/ፋ/መ/ቁ 11/94 የካቲት 19 ቀን 1994 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ የፀና ስለሆነ፡

1. ተጠሪ ገዥ ባለመገኘቱ ምክንያት በአፈፃፀም ሊረከበው የሚገባው ንብረት የፍርድ ባለዕዳውን የአቶ ዮሐንስ ገ/ስላሴን እና የአመልካችን ቦታና ይዞታ ብቻ በመሆኑ በማዘጋጃ ቤቱ እንደተረጋገጠው 600 ሜትር ካሬ ብቻ ሊረከብ ይገባል፡፡
2. ይህም ይሸጥ የተባለው ቤትና ቦታ የፍርድ ባለዕዳውና የአመልካች የጋራ ሀብት መሆኑ ታይቶ ለአፈፃፀሙ መነሻ በሆነው ውሳኔ ላይ ዳኝነት የተሰጠበት በመሆኑና ይህም በይግባኝ ያልተሻረ ስለሆነ እንዲሁም በአፈፃፀም መዝገቡም ላይ ቢሆን ይኸው መብት የተጠበቀ በመሆኑ በሞዴል 85 ተይዞ የሚገኘው ብር 12,500.00 /አስራ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ብር/ የአመልካች ድርሻ በመሆኑ ለአመልካች ሊከፈል ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

ይህ ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡



የሰበር መ/ቁ. 22260

መጋቢት 20 ቀን 1999

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

” አሠግድ ጋሻው

” መስፍን እቁበዮናስ

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** የጎንደር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት

**ተጠሪዎች፡-** እነ ወ/ሮ ገደሪፍ ውብነህ

*የወጪና ኪሣራ ክርክር - የወጪና ኪሣራ አወሳሰን - የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 463*

የአማራ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪዎች ወጪና ኪሣራ እንዲከፍል የወሰነውን በመቃወም የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

**<u>ውሣኔ፡ -</u>** የአማራ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ በከፊል ተሽሯል፡፡

1. የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 462 በክስ ምክንያት ስለሚከፈለው ማናቸውም ወጪና ኪሣራ፣ የሚከፍለውን ወገን፣ የወጪውንና የኪሣራውን ልክ፣ የሚከፈልበትን የሃብት ምንጭ፣ የአከፋፈሉን ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ትክክል መስሎ በሚገምተው ሁኔታ እንዲወስን መብት (discretion) ይሰጠዋል፡፡
2. የወጪና ኪሣራ ክፍያ አላማ ረቺው ወገን በክርክሩ ምክንያት ያወጣውን ወጪ ተረቺ እንዲሸፍን እንጂ ተረቺውን ለመቅጣት አይደለም፡፡
3. ፍርድ ቤት የወጪና ኪሣራን መጠን ሲወስን ምክንያታዊ ባልሆነና በተጋነነ መንገድ እንዳይሆን ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፡፡
4. የወጪና ኪሣራ ዝርዝር ባልቀረበ ጊዜ ፍርድ ቤት የኪሳራውን መጠን የተጋነነ እንዳይሆን ክርክሩ የወሰደው ጊዜ፣ የክርክሩ ውስብስብነትና አስፈላጊውን ዳኝነት ለመከታተል ተገቢ ናቸው የሚላቸውን ወጪዎች አመዛዝኖ ተመጣጣኝ መጠን ያለው ኪሣራ ሊወስን ይገባል፡፡

የሰበር መ/ቁ. 22260

መጋቢት 20 ቀን 1999

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. " አሠግድ ጋሻው

3. " መስፍን እቁበዮናስ

4. ወ/ት ሂሩት መለሠ

5. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- የጎንደር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት - ነገረፈጅ በረደድ

ተጠሪዎች፡- 1.ወ/ሮ ገደሪፍ ውብነህ የአባ ሣሙኤል ከብት እርባታ ድርጅት

ባለንብረት ጠበቃ አብዱል ተካበ

2. የወተት ሃብት ልማት ድርጅት

3. የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የወጪና ኪሣራ አከፋፈልን የሚመለከት ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች 1ኛ ተጠሪ ለሚጠቀሙበት ቦታ ብር 1,479,996.60 የቦታ ግብር እንዲከፍሉ የመሠረተውን የአፈፃፀም ክስ የሰ/ጎንደር መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተቀብሎ እንዲከፍሉ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ 1ኛ ተጠሪ ቅር በመሠኘታቸው ይግባኙን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ የሻረው ሲሆን አመልካች በአሁኖቹ ተጠሪዎች ላይ ተገቢ ያልሆነ ክስ በማቅረብ ለደረሰው መጉላላትና ለተከሰተው ወጪ ኃላፊ ነው በማለት ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው ብር 2,000 (ሁለት ሺህ) ለ1ኛ ተጠሪ ደግሞ 500.00 (አምስት መቶ ብር) እና የጠበቃ አባል ክስ የቀረበበትን ብር 5% እንዲከፈል ወስኖበታል፡፡

የአሁኑ አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ ማይኖር ወጪና ኪሣራ እንዲከፈላቸው እንዲሁም ለ1ኛ ተጠሪ ብር 500 እና የጠበቃ አበል ክስ የቀረበበትን ገንዘብ 5% እንዲከፈል የተሰጠውን ውሣኔ ሕጋዊነት የወጪና ኪሣራ አከፋፈልን አስመልክቶ ከተቀመጡት የፍ/ብሔር ሥነ- ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌ አኳያ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረግ የግራ ቀኙን ክርክር ሠምቷል፡፡



ስለወጪና ኪሣራ የሚመለከተው የፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ አንቀፅ 462 በክስ ምክንያት ስለሚከፈለው ማናቸውም ወጪና ኪሣራ የሚከፍለውን ወገን፣ የወጪውንና የኪሣራውን ልክ፣ የሚከፈልበትን የሃብት ምንጭ፣ የአከፋፈሉን ሁኔታ ፍ/ቤቱ ትክክል መስሎ በሚገምተው ሁኔታ እንዲሰጥ መብት (discretion) ይሠጠዋል፡፡ የወጪና ኪሣራ ክፍያ አላማም ረቺው ወገን በክርክሩ ምክንያት ያወጣውን ወጪ ተረቺ እንዲሸፍን እንጂ ተረቺውን ለመቅጣት ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ የወጪና ኪሣራውን መጠን ለመወሰን መብት (discretion) ቢኖረውም ውሣኔውን በሚሠጥበት ጊዜ ይህንኑ የህጉን አላማ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

ፍ/ቤቱ ተገቢ ግምት ነው ያለውን ወጪና ኪሣራ ለመወሠን ይረዳው ዘንድም ወጪው ወይም ኪሣራው ሊከፈለው የሚገባው ወገን የወጪውን ዝርዝር እንዲያቀርብ ሊያዘው እንደሚችል የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 463(1) ያመለክታል፡፡ ዝርዝሩ ቢቀርብለትም ግን የቀረበውን ዝርዝር እንዳለ ለመቀበል ማይገደድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 464 መሠረት መርምሮ በቂ ባልሆነ ምክንያት ከፍ ብሎ የሚታየውን በመቀነስ ወይም ተገቢ ያልሆነውን በመቀነስ ወይም ጭርሱንም በመሠረዝ መጠኑን መወሰን እንደሚገባው ይኸው የሥነ ሥርዓት ድንጋጌ ያመለክታል፡፡

ከፍ ሲል የተመለከቱት የሥነ ሥርዓቱ ድንጋጌዎች በሙሉ፤ ምንም እንኳን ፍ/ቤቱ የወጪና ኪሣራውን መጠን ለመወሰን መብት (discretion) ቢኖረውም፤ መጠኑን ሲወስን ምክንያታዊ ባልሆነና በተጋነነ መንገድ እንዳይሆን ጥንቃቄ ሊያደርግ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ፡፡

ከዚህ ተነስተን ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የሰ/ጎንደር መ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ያቀረቡት ይግባኝ የለም ይህም በመሆኑ አመልካችን ሲሞግቱ ያወጡት ወጪም ሆነ በደረሰባቸው ኪሣራ አልነበረም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ሊተካላቸው የሚገባ ወጪም ሆነ ኪሣራ ስለሌለ አመልካቹ ለእያንዳቸው ብር 2.000 (ሁለት ሺህ ብር) እንዲከፍል የተሰጠው ውሣኔ የሕግ መሠረት የለውም፡፡

በሌላ በኩል ግን 1ኛ ተጠሪ በከፍተኛ ፍ/ቤቱ ውሣኔ ላይ ይግባኝ አቅርበው አመልካቹን መርታታቸውን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ክርክራቸውን ለመከታተል ያወጡትን ወጪና ኪሣራ አመልካቹ ሊተካላቸው ይገባል፡፡ ነገር ግን ከፍ ሲል እንደተመለከተው የወጪና ኪሣራ ክፍያ ተከራካሪው ያወጣውን ወጪ ወይም የደረሰበትን ኪሣራ ከመተካት ያለፈ አላማ ስለሌለው የፍ/ቤቱ ውሣኔ ከወጣው ወጪ ጋር ተመጣጣኝ መሆን ይገባዋል፡፡ በእርግጥ ፍ/ቤቱ ትክክለኛ ነው ያለውን ግምት ለመወሰን እንዲያመቻቸው የወጪና ኪሣራ ዝርዝር እንዲቅርብ ማዘዝ የሚችል ቢሆንም ዝርዝር ባልቀረበለት ጊዜም ተገቢ መጠን

ያለው ኪሣራ በግምት ሊወሰን የሚችልበት አጋጣሚ እንዳለ ከፍ/ሥ/ሕ/ ቁ.464(3) መመልከት ይቻላል። በመሆኑም ዝርዝር ባልቀረበ ጊዜ የኪሣራው መጠን የተጋነነ እንዳይሆን ክርክሩ የወሰደው ጊዜ የክርክሩ ውስብስብነት አስፈላጊውን ዳኝነት ለመከታተል ተገቢ ናቸው የሚላቸውን ወጪዎች አመዛዝኖ ተመጣጣኝ መጠን ያለው ኪሣራ ሊወስን ይገባል።

በተያዘው ጉዳይ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ለጠበቃ አበል ክስ የቀረበበትን ገንዘብ 5% የሆነውን ከፍተኛ መጠን ያለው ኪሣራ ወይም ወጪ ሲወስን ለኪሣራው አወሣሡን መሠረት ያደረገው ነገር ግልፅ አይደለም። በእርግጥ 1ኛ ተጠሪ በጠበቃ ክርክሩን መምራታቸው አላከራከረም። ይሁን እንጂ ጠበቃው ለሰጡት አገልግሎት ሊከፍሉ የተስማሙት የገንዘብ መጠን ስለመኖሩ የቀረበ ውል ካለመኖሩም ሌላ ጉዳዩ የቦታ ኪራይ እንዲከፈል የቀረበ የግብር ውሣኔ አፈፃፀም ክርክር እንጂ መደበኛ ክርክር አለመሆኑ ክርክሩ ውስብስብነት ያለው ነው ለማለት የሚያስችል ሆኖ አላገኘነውም። ጠበቃውም ዳኝነቱን ለመከታተል የተለየ ወጪ ሊያስወጣቸው የሚችል ነገር ስለመኖሩ መዝገቡ አያመለክትም። በአጠቃላይ ጠቅላይ ፍ/ቤት የወሰነው የኪሣራ መጠን የወጪና ኪሣራ አከፋፈልን አላማ ያልተከተለና በዚህም ምክንያት እጅጉን የተጋነነ መሆኑን ተረድተናል። ይህም 1ኛ ተጠሪ ያወጡትን ወጪ ከመተካት አልፎ አመልካቹን የመቅጣትና ጠበቃውንም ያላግባብ እንዲበለፅግ የሚያደርግ ውሣኔ በመሆኑ ውሣኔው የሕግ ስህተት ያለበት ነው።

በሌላ በኩል ግን 1ኛ ተጠሪ ዋናው ባለጉዳይ በመሆናቸው ዳኝነቱን ለመከታተል ወደ ፍ/ቤት መመላለስ ያለባቸው በመሆኑም ሌሎችም አስፈላጊ ወጪዎች የሚያወጡ በመሆኑ ብር 500 (አምስት መቶ) እንዲከፈላቸው መወሰኑ ስህተት ነው ማለት አልቻልንም።

## ው ሣ ኔ

1. የአማራ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 04509 በ01/02/1998 ለ2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ለእያንዳንዳቸው ብር 2.000 (ሁለት ሺህ) እንዲሁም ለ1ኛ ተጠሪ የጠበቃ አበል ክስ የቀረበበትን ገንዘብ 5% እንዲከፈል የሰጠው የውሣኔ ክፍል ተሽሯል።
2. ለ1ኛ ተጠሪ ብር 500 (አምስት መቶ)እንዲከፈል የተሰጠው የውሣኔ ክፍል ፀንቷል።
3. 1ኛ ተጠሪ ክርክራቸውን በጠበቃ የተከታተሉ በመሆኑ የክርክሩን ርዝመትና የክርክሩን ውስብስብነት ከግምት በማስገባት የጠበቃ አበል ብር 3,000 (ሦስት ሺህ) አመልካች እንዲከፍል ተወስኗል።



4. በዚህ ፍ/ቤት ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ። መዝገቡ ተዘግቷል።

የሰበር መ/ቁ. 17984

መጋቢት 20 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
" ፍስሐ ወርቅነህ
" ዓብዱልቃድር መሐመድ
" አሰግድ ጋሻው
" ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** የጌዲዮ ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ አስናቀች ታደሰ

*የሐራጅ ሽያጭ - ጉድለት ያለበት ሃራጅ - ጉድለት ያለበት ሃራጅ ቀሪ ሲደረግ ሻጭና ገዥን ወደነበሩበት ስለመመለስ - የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1817(1)ና(2)*

የደቡብ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሀራጅ ሽያጩ ፈርሶ ንብረቱ ወደ ነበረበትና የግገርው ገንዘብ እንዲመለስ በመወሰኑ የቀረበ አቤቱታ ነው።

<u>**ውሣኔ፡ -**</u> የደቡብ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሸሯል።

1. ንብረት በሐራጅ ከተሸጠ በኂላ የሐራጅ ሽያጩ በጉድለት ምክንያት ቀሪ እንዲሆን በተወሰነ ጊዜ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ህ/ቁ 1817(1) የተደነገገውን ሊከተል ይገባል።
2. የሐራጁን ሽያጭ በማፍረስ ገገሮችን ወደ ነበሩበት መመለስ ባልተቻለ ጊዜ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1817(2) መሠረት ለደረሰው መዛባት ኪሣራ ይከፈል ለማለት ጉዳዩ የመነጨው በፍርድ ቤት አማካይነት በተደረገ ሽያጭ በመሆኑ ይህን ድንጋጌ ተፈፃሚ ማድረግ የሚቻል አይደለም።

የሰበር መ/ቁ. 17984

መጋቢት 20 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

" ፍስሐ ወርቅነህ

" ዓብዱልቃድር መሐመድ

" አሰግድ ጋሻው

" ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** የጌዲዮ ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት አልቀረበም

**መልስ ሰጭ፡-** ወ/ሮ አስናቀች ታደሰ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

መዝገቡን መርምረናል እንደመረመርነውም በዚህ ጉዳይ መነሻ የሆነው የደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ ተመልክቶ በሁለተኛው የሐራጅ አሻሻጥ ሥርዓት አፈፃፀም ላይ ጉድለት ታይቶበታል፡፡ ስለሆነም ሁለተኛው የሐራጅ ሽያጭ ሊደረግ የሚገባው በግምቱ መነሻ ሲሆን በዚህ ግምት መነሻ ገገር ካልተገኘ ግምቱን መሠረት በማድረግ ከላይ ወደታች ጥሪ በማድረግ ነው በዚህ አኳኋን ይፈፀም በማለት ወስኖ ወደ ሥር ፍ/ቤት መልሶታል፡፡

የሥር ፍ/ቤትም በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት ለማስፈፀም ቢታሰብ በተካሄደው ሁለተኛ ጨረታ ጊዜ አሸናፊ ናቸው የተባሉት ገገርዎች ንብረቱን ተረክበው በቦታው ላይ የሚገኘውንም ንብረት አንስተው ወስደውታል፡፡ የሚገኘው ነገር ቢኖር ባዶ ቦታ ብቻ ነው ስለሆነም እንደ ውሣኔው ለማስፈፀም እንዴት እንደሚቻል ማብራሪያ ይሰጥበት በማለት በአቀረበው ጥያቄ መነሻ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ የተሰጠው ውሣኔ ይሸጥ የተባለው ንብረት ወደ ሦስተኛ ወገኖች ማለት ወደ ገገርዎች የተላለፈ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት አይደለም፤ እነዚህ ገገርዎችም ሕግን የተላለፈ ተግባር የፈፀሙ ስለመሆኑም አልተገለፀም ስለሆነም ከዚህ በፊት ሥርዓቱን በተከተለ እኳኋን ሁለተኛ የሐራጅ ሽያጭ ሊከናወን ይገባል በማለት የተሰጠው ውሣኔ ቀሪ ነው በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት የአሁን መልስ ሰጭ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርባለች፡፡



የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም ምንም እንኳ ይሸጥ የተባለው ንብረት በገገርዎች እጅ የገባ መሆኑ ቢረጋገጥም ይኸው ግገር የተፈፀመበት ሐራጅ በይግባኝ እስከተሻረ ድረስ ግገርው እንዳልተደረገ ሊቆጠር ስለሚገባ ግገርው ፈርሶ ገገርዎች ንብረቱን በነበረበት ሁኔታ ሊመልሱ ይገባል፤ የገገርው ገንዘብ ለእነርሱ ይመለስ በማለት ወስኗል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የክልል ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡

እኛም ጉዳዩን ተመልክተናል፡፡ እንደተመለከትነውም ሁለተኛ የሐራጅ ሽያጭ የተደረገበት አካሄድ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጉዳይ በይግባኝ ታይቶ ከመወሰን በፊት እንደ ከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ በሁለተኛው ሐራጅ ገገር መሆናቸው የተረጋገጠው ገገርዎች ባሸነፉበት ዋጋ መሠረት እንደ ሥርዓቱ ንብረቱን እንዲረከቡ ተደርጓል፡፡

እንዲረከቡ ከተደረገ በኋላም በገገርነታቸው እምነት የቆዳና ሌጦ መጋዘኑንም ሆነ በወፍጮው የሚገኘውን ንብረት ነቃቅለው የወሰዱት ለመሆኑና እንደ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ውሣኔ ሊሸጥ የሚቻል ንብረት በቦታው የማይገኝ መሆኑን አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት በሚገባ አረጋግጧል፡፡ እንደ ፍ/ቤቱ ማረጋገጫ ከሆነም ንብረቱን በነበረበት አኳኋን ለመመለስ የሚቻል አይደለም ይህ መሆኑን እንደተረዳ የሰበር ሰሚው ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1817/1/ የተመለከተውን ድንጋጌ ሊከተል ይገባ ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ የሐራጅ ሽያጩን በማፍረስ ገገርዎችን ወደ ነበሩበት ቦታ መመለስ ባልተቻለ ጊዜ ከላይ እንደተመለከተው ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 2 መሠረት ለደረሰው መዛባት ኪሣራ ይከፈል እንዳይባል ጉዳዩ የመነጨው በፍ/ቤት አማካኝነት በተደረገ ሽያጭ መሠረት በመሆኑም ይህንኑ ድንጋጌ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሁኔታውን እንደነበረ ለማድረግ የማይቻል መሆኑን እየተረዳ በማይፈፀም አኳኋን የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## ው ሣ ኔ

የደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ጠ/ፍ/ቤት በሰበር መ/ቁ. 4867 ጥቅምት 17 ቀን 1997 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡ ይህንኑ እንዲያውቀው በክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በኩል አፈፃፀሙን ይዞ ለነበረው ፍ/ቤት ይተላለፍ፡፡

ወጭና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የሰበር መ/ቁ. 19205

መጋቢት 25/1999

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** አቶ ሽኩር ሲራጅ

**መልስ ሰጪ፡-** አቶ ሙላት ካሣ

*የአፈጻጸም ክርክር - ለአፈጻጸም በፍርድ ቤት የሚያዝ ገንዘብ - ፍርድ ተፈፀመ ስለሚባልበት ጊዜ - የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 395*

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍርድ ባለዕዳው ፍርድ ያረፈበትን ገንዘብ በፍርድ ቤት ውሣኔ በመሻሩ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሮ የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

> አንድ ፍርድ ተፈጸመ ሊባል የሚገባው ለፍርድ ቤቱ ገቢ የተደረገ ገንዘብ ለፍርድ ባለመብቱ ሲደርሰው ነው፡፡



የሰበር መ/ቁ. 19205

መጋቢት 25/1999

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** አቶ ሽኩር ሲራጅ ጠበቃ ሙላት ፈለቀ

**መልስ ሰጪ፡-** አቶ ሙላት ካሣ - ቀርበዋል

በዚህ መዝገብ የቀረበልንን የፀቡ አቤቱታ መርምረን ቀጥሎ ያለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## <u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ የቀረበልን ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን አመልካች የፍርድ ባለመብት ሲሆን መልስ ሰጪ የፍርድ ባለእዳ ነው፡፡ የአሁን አመልካች የተፈረደለትን የገንዘብ መጠን ብር 24,227 (ሃያ አራት ሺ ሁለት መቶ ሃያ ሰባት ብር) ለማስከፈል የአፈፃፀም መዝገብ አስከፍቶ የአሁን መልስ ሰጭ ቤት ተሸጦ እዳው እንዲከፈል ትእዛዝ ተሰጠ፡፡ ከዚህ ትእዛዝ በኋላ የአሁን መልስ ሰጪ በፍርድ ቤት ፈቃድ ብር 20,000 በሞዴል በማስያዙ የአሁን አመልካች ገንዘቡ እንዲለቀቅለት አመለከተ፡፡ ሆኖም የአፈፀፀም መዝገቡ ጠፋ በመባሉ በፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቱ ትእዛዝ ሌላ የአፈፃፀም መዝገብ እንዲከፈት ከተደረገ በኋላ የፍርድ ባለመብቱ (የአሁን አመልካች) በሞዴል 85 የተያዘው ገንዘብ እንዲከፈለው በጠየቀው መሠረት ፍ/ቤቱ ወጭ ሆኖ እንዲከፈለው አዘዘ፡፡ ትእዛዙ የደረሰው የፋይናንስ ቢሮ በሞዴል 85 ተይዞ የነበረው ገንዘብ ፍርድ ቤቱ በ15/5/89 በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ገንዘቡን አቶ ኤልያስ አርአያ ለተባለ ሰው መከፈሉን ስለገለፀ ጉዳዩን የያዘው ፍ/ቤት የፍርድ ባለእዳ ገንዘቡን በሞዴል 85 ካስያዘ በፍርድ ቤት እንደተቀመጠ ስለሚቆጠር የፍርድ ባለመብት ጉዳዩን ተከታትሎ ገንዘቡ ለሌላ 3ኛ ወገን እንዲከፈል ምክንያት የሆነውን አካል ጠይቆ ገንዘቡን ከሚቀበል በቀር ከፍርድ ባለእዳ ድጋሚ መጠየቅ አይችልም በማለት ወሰነ፡፡ ይህ ውሣኔ በከፍተኛ ፍ/ቤት የተሻረ ቢሆንም የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መልሶ በመሻሩ የፍርድ ባለመብት ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

የጠቅላይ ፍ/ቤቱ የፍትሐብሔር ችሎት የፍርድ ባለእዳ በሞዴል 85 ያስያዘውን ገንዘብ በፍትሀብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁ. 395 መሠረት እንደተከፈለ ይቆጠራል በማለት ነው የአሁን መልስ ሰጪን ይግባኝ በመቀበል የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ የሻረው፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች በአቤቱታው ያቀረበው ቅሬታ በሞዴል 85 የተያዘው ገንዘብ በአመልካቹ ስም ለመሆኑ አልተረጋገጠም፣ አመልካች ያስፈረደው በመልስ ሰጪ ላይ በመሆኑ ከሦስተኛ ወገን ገንዘቡን እንዲያስመልስ መታዘዙ አግባብ አይደለም፣ ገንዘቡ ለሦስተኛ ከተከፈለ ገንዘቡን ማስመለስ ያለበት በስሙ ያስያዘው መልስ ሰጪ መሆን አለበት የሚሉት ናቸው፡፡

መልስ ሰጪ የጽሑፍ መልሱን አቅርቧል፡፡ የመልስ ሰጪ ፍሬ ሀሣብ አመልካች ገንዘቡ በስሜ አልተያዘም ማለቱ ትክክል አይደለም፣ ገንዘቡ በሞዴል 85 በፍርድ ቤት በኩል እንዲያዝ ሲታዘዝ እዳው እንደተከፈለ ስለሚቆጠር ዳግመኛ ልጠይቅ አይገባኝም የሚሉ ናቸው፡፡

ይህ ችሎት ጉዳዩን በስር ፍርድ ቤቶች ከተደረጉ ክርክሮች አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማነፃፀር መርምሯል፡፡ መልስ የሚሻው ዋነኛ ነጥብ በሞልል 85 ተይዞ የነበረው ገንዘብ ለሌላ ሦስተኛ ወገን ቢከፈልም ለአሁን አመልካች እንደተከፈለ መቆጠሩ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በመዝገቡ ለመገንዘብ እንደቻልነው የአሁኑ አመልካችን የአፈፃፀም ክስ መሠረት በማድረግ ብር 20,000 በሞዴል 85 በፋይናንስ ቢሮ እንዲያዝ መደረጉ አላከራከረም፡፡ ይህ ተይዞ የነበረው ገንዘብ ለአሁን አመልካች ሣይሆን ለሌላ ሰው በፍርድ ቤት ትእዛዝ መከፈሉም ተረጋግጦአል፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይህ መሆኑ እየታወቀ መልስ ሰጪ እዳውን እንደከፈለ ይቆጠራል ለማት የበቃው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ.395 (1(ሀ)) ያስቀመጠውን ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ የዚህ ቁጥር አግባብነት ያለው ክፍል" በፍርድ ወይም በውሣኔ መሠረት የሚከፈል ገንዘብ ሁሉ ከዚህ ቀጥሎ በተመለከተው ሁኔታ መከፈል አለበት፡፡ ፍርዱን እንዲያስፈጽም በታዘዘው ፍርድ ቤት በማስያዝ" በማለት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ለመገንዘብ የሚቻለው አንድ ሰው የተፈረደበትን ገንዘብ ለፍርድ ቤት ገቢ ለማድረግ ግዴታውን የሚወጣበት አንድ አማራጭ መንገድ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ግን እንዲህ በተናጠል ሣይሆን ከድንጋጌው ዓላማ ጋር ተጣምሮ መታየት ይኖርበታል፡፡ ባለእዳው ገንዘቡን ለፍርድ ቤት ገቢ የሚያደርገው የፍርድ ባለመብት የሚጠይቀውን ገንዘብ እንዲያገኝ ለመርዳት ነው፡፡ የሂደቱ ዋናው ተጠቃሚ የፍርድ ባለገንዘቡ እንጂ ፍርድ ቤቱ እንደሆነ ተደርጎ ሊቆጠር አይገባውም፡፡ ለአንድ ፍርድ ባለመብት በፍርዱ መሠረት



ተፈፀመለት ሊባል የሚገባውም ለፍርድ ቤቱ ገቢ የሆነው ገንዘብ ሲደርሰው ነው፡፡ በፍርድ ቤቱ የተያዘው ገንዘብ የፍርድ ባለመብቱ የሚያዝበት ገንዘብ አይደለም፡፡ ወደ ፍርድ ባለመብቱ ገቢ እንዲሆን የፍርድ ቤት ትእዛዝ የሚፈልገውም የፍርድ ባለመብቱ የሚያዝበት ሀብት ባለመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም በፍርድ ቤት ገንዘብ ገቢ በማድረግ እዳ መከፈል አንድ አማራጭ መንገድ ቢሆንም የፍርድ ባለእዳው እዳውን ጨርሷል መባል ያለበት ይህ ሂደት ተጠናቅቆ የፍርድ ባለመብቱ ገንዘቡን ሲረከብ ሊሆን ይገባል፡፡

አሁን በቀረበልን ጉዳይ የፍርድ ባለእዳው ብር 20,000 በሞዴል 85 ማስያዙ ቢታወቅም ይኸው ገንዘብ በፍርድ ቤት ትእዛዝ ለሌላ ሰው ተከፍሏል፡፡ የፍርድ ባለመብት የሆነው አመልካች ይኸው ገንዘብ እንዲከፈለው የጠየቀ ቢሆንም ገንዘቡን ይዞ የነበረው የፋይናንስ ቢሮ ገንዘቡን ለሌላ ሰው መከፈሉን በመግለፁ ሊከፈለው አልቻለም፡፡ ገንዘቡ ወሰደ የተባለው ሰው በምን ምክንያት እንደወሰደው የተገለፀ ነገር ባይኖርም በፍርድ ቤት ትእዛዝ እንደተለቀቀለት ግን ከፍርድ ቤቶቹ መዝገብ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ይህ ገንዘብ ለአሁን መልስ ሰጪ እዳ መክፈያ ውሎ ሊሆን እንደሚችልም ይገመታል፡፡ በመሆኑም የፍርድ ባለመብቱ ገንዘቡን ባልተረከበበት ሁኔታ የፍርድ ባለእዳው እንደከፈለ መቁጠሩ አግባብ አይደለም፡፡ የፍርድ ባለእዳው ያስያዘው ገንዘብ ፍርዱ ከመፈፀሙ በፊት ተመልሶ በፍርድ ቤት ትእዛዝ ከተከፈለ ባለእዳው ገንዘብ እንዳስያዘ ሊቆጠርም አይገባውም፡፡ ያስያዘው ገንዘብ ሣይኖር በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 395(2) መሠረት ፍርዱ እንደተፈፀመ የሚቆጠርበት ምክንያት የለም፡፡

በዚህ ምክንያት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ገንዘቡ መጀመሪያ በሞዴል 85 መያዙን ብቻ ግምት ውስጥ በማስገባት የአሁን መልስ ሰጭ እዳውን እንደከፈለ ይቆጠራል በማለት የሰጠው ውሣኔ ትክክል ስላልሆነ ሊሻር ይገባዋል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን መልስ ሰጪ ያስያዘው ገንዘብ ለሌላ ሰው መከፈሉን መሠረት በማድረግ ለብር 20,000 ተጠያቂ ነው በማለት የሰጠው ፍርድ ሊፀና የሚገባው ነው፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ.ቁ. 17544 የካቲት 14 ቀን 1997 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 08423 በ17/02/97 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. የዚሁ ውሣኔ ግልባጭ ለሁለቱም ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡

4. ወጪና ኪሣራ መልስ ሰጪ ለአመልካቹ ብር 500 (አምስት መቶ ብር) ይክፈል፣ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያስከፍል፡፡



የሰበር መዝገብ ቁ. 19479

መጋቢት 20 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አቶ መንበረ ፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሀ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃደር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

**አመልካች፡-** የወ/ሮ አመለወርቅ ገለቴ ወራሾች

**መ/ሰጪዎች፡-** እነ አቶ ቢሻው አሻሜ

*ውርስ - የጋራ ሃብት - የቤት ክፍፍል - የቦታ ይዞታ መብት - የአዋጅ ቁ. 47/67*

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ለውርስ ክፍፍል ክርክር የቀረበበት ቤት የጋራ ነው ሆኖም የቦታ ይዞታው የግል ነው ሲል የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናቱ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. አከራካሪ የሆነው ቤት የግልም ሆነ የጋራ ቤቱ ያረፈበት ቦታ የመንግሥት በመሆኑ ከቤቱ ተነጥሎ እንዲገመትና አስፈላጊም ከሆነ እንዲሸጥ የሚያደርግ ውሣኔ መሬት የመንግሥት ለማድረግ የወጣውን ህግ የሚፃረር ነው፡፡
2. ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ተከራካሪዎች በስር ፍርድ ቤት ክርክር ያላደረጉበትን መሠረት አድርጎ መወሰን አይችልም፡፡

የሰበር መዝገብ ቁ. 19479

መጋቢት 20 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች:- አቶ መንበረ ፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሀ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃደር መሐመድ
አቶ አሰግድ ጋሻው
አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

**አመልካች:-** የወ/ሮ አመለወርቅ ገለቴ ወራሾች -ወኪል ቀርባለች

**መልስ ሰጪ:-** 1ኛ. አቶ ቢሻው አሻሜ -ቀረቡ
2ኛ. አቶ አዳነ አሻሜ
3ኛ. አቶ ማነው አሻሜ
4ኛ. ወ/ሮ እመቤት አሻሜ
(2ኛ–4ኛ) - ወኪላቸው ቀርበዋል

በዘህ መዝገብ የቀረበልንን ጉዳይ መርምረን ቀጥሎ ያለውን ፍርድ ሰጥተናል::

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ ቤትን አስመልክቶ የቀረበ የክፍፍል ጥያቄን የሚመለከት ነው:: የአሁን መልስ ሰጪዎች መጀመሪያ ያቀረቡት ክስ የአውራሻችን የግል ቤት በስር ተከሣሾች በአሁን አመልከቾች እጅ ስለሚገኝ ድርሻችን ብር 111,111.08 /አንድ መቶ አስራ አንድ ሺህ አንድ መቶ አስራ አንድ ብር ከዜሮ ስምንት ሣንቲም/ እንዲሰጠን በማለት ክስ አቀረቡ፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት የአሁን መልስ ሰጪዎች ቤቱ የጋራ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ስላቀረቡ ቤቱ የግል ሳይሆን የጋራ ነው በማለት ወሰነ:: ፍርድ ቤቱ ቤቱ የጋራ ነው የሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰው ጥያቄ የቀረበበት ቤት ጋብቻ ከተመሰረ በኋላ እንደአዲስ ተሰርቷል በማለት ነው:: ይኸው ፍርድ ቤት ቤቱ የጋራ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ቤቱ የተሰራበት ቦታ ግን የግል ነው በማለት ከየቦታው ግምትና የቤቱ ግምት ለየብቻ በባለሙያ በፍርድ አፈፃፀም ተገምቶ ተከሣሾች የቤቱን ግምት ብቻ ግማሹን ለተከሣሽ ሰጥተው ከተከሣሽ እንዲረከቡ ይህ ካልተቻለ ተከሣሽ የቦታውን ግምት እና የቤቱን ግምት ግማሽ ለከሣሾች ሰጥተው ቤቱን እንዲያስቀሩ ይህ ካልሆነ ቤቱና ቦታው በሐራጅ ተሽጦ የቦታው ግምት በውሉ የቤቱ ግምት ግማሽ ለከሣሾች እንዲከፍል እና የቀረው የቤቱ ግምት ለተከሣሽ እንዲከፍል ታዟል በማለት ሐምሌ 8 ቀን 1996 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ወሰነ::

ይህን ውሣኔ በመቃወም ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ በአሁን አመልካቾች ቢቀርብም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 33964 ጉዳዩ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ዘግቶታል::



የሰበር አቤቱታ የቀረበው የፌዴራል መጀመሪያና ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት ካለበት ይታረምልን በማለት ነው:: በአቤቱታው የተገለፁት ዋና ዋና ቅሬታዎች:-

1. ቤቱን በሚመለከት እንጂ ቤቱ የተሰራበትን ቦታ በሚመለከት ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበ አቤቱታም ሆነ በፍርድ ቤቱ የተደረገ ክርክር አልነበረም:: ክርክር ባልተደረገበት ጉዳይ ፍርድ ቤቱ ውሣኔ መስጠቱ ሥርዓቱን የተከተለ ሂደት አይደለም::
2. ቦታው የግል ነው በማለት የተሰጠው ውሣኔ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤትን የመንግስት ያደረገውን አዋጅ 47/1967 እና የሕገ መንግስቱን ድንጋጌዎች የሚጥስ ነው፣
3. ፍርድ ቤቱ ያስቀመጠው የክፍፍል ቀመር ተጠሪዎች ከጠየቁት ውጪ የተደረገ ነው፣ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ.2/3/1992 ድንጋጌዎችም ያገናዘበ አይደለም የሚል ነው::

መልስ ሰጪዎች አመልካቾች ላቀረቡት አቤቱታ ሰኔ 8 ቀን 1997 የተፃፈ መልስ አቅርበዋል:: በመልሳቸው ላይም :-

1. አዋጅ ቁጥር 47/ 67 አንቀፅ 7/1/ አዋጁ ከመፅናቱ በፊት የከተማ ቦታ ያለው ቤተሰብ ወይም ግለሰብ ሌላ የመኖሪያ ቤት ከሌለው በአንቀፅ 4/1/ በተመለከተው የይዞታ መጠን በቦታው ላይ የይዞታ መብት ይኖረዋል ስለሚል የቀረበው የአመልካች ቅሬታ የሕግ መሠረት የለውም፣
2. አመልካች የከተማ ቦታ የመንግስት ብቻ ነው ቢሉም ይህን የሚደግፍ አንቀፅ አልጠቀሱም፣
3. የስር ፍ/ቤቶች የሰጡዋቸው ውሣኔዎች የቤተሰብ ሕግን ድንጋጌዎች የሚፃረሩ አይደሉም፣
4. የቤቱ ግምት የተሰላው ፍርድ ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የቀረበውን የ275, 000 ብር/ሁለት መቶ ሰባ አምስት ሺ ብር/ ግምት በመንተራስ በመሆኑ የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል::

ይህ ችሎት በግራ ቀኙ ያለው ክርክር ዋነኛ ነጥብ ክርክር ያስነሣው ቤትና ቤቱ የተሰራበት ቦታ ለየብቻ በመመልከት ቤቱ የጋራ ነው ቦታው ግን የግል ነው በማለት የተሰጠው ውሣኔ የሕግ መሰረት ያለው ነው ወይም አይደለም የሚለው ነው::

በመሰረቱ ከማህደሩና ተያይዘው ከቀረቡት ሰነዶች ለመገንዘብ የቻልነው በአመልካችና በመልስ ሰጪ የነበረው ሙግት ቤትን የሚመለከት ብቻ ነው:: ቤቱ ያረፈበት ቦታን የሚመለከት ሙግት በመጀመሪያ ፍርድ ቤት አልተካሄደም ስለዚህ ፍርድ ቤቱ መጨረሻ ላይ ቤቱ ያረፈበትን አስመልክቶ የሰጠው ውሣኔ ባለጉዳዩቹ ያደረጉትን ክርክር መሠረት ያደረገ አይደለም::

ከዚህ በተጨማሪ የከተማ /ቦታና ትርፍ ቤት የመንግስት ለማድረግ የወጣው አዋጅ ቁ. 47/67 በከተማ ቦታ ላይ የግል ባለሀብትነት ማስቀረቱን ግንዛቤ የወሰደ ውሣኔ ሆኖ አላገኘነውም:: አከራካሪ የሆነው ቤት የግልም ይሁን የጋራ ቤቱ ያረፈበት ቦታ የመንግስት በመሆኑ ከቤቱ ተነጥሎ እንዲገመትና አስፈላጊም ከሆነ እንዲሸጥ የሚያደርገው ውሣኔ መሬት የመንግስት ለማድረግ የወጣውን ህግ የሚፃረር ነው:: የከፍተኛ ፍርድ ቤቱም የተሰራውን ስህተት ማረም ሲገባው ይግባኙን በ337 አያስቀርብም ማለቱ አግባብ አልነበረም:: በመሆኑም የፌዴራል መጀመሪያ ፍርድ ቤትም ሆነ የከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ጉዳይ ላይ የሰጡት ወሣኔ ሊለወጥ የሚገባው ነው::

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. ቤቱ ያረፈበት ቦታ የመልስ ሰጪዎች አውራሽ የግል ሀብት ነው የሚለው የመጀሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ. 01416 ሐምሌ 8 ቀን 1996 የተሰጠው ውሣኔ ተሰርዟል::
2. አከራካሪው ቤትና ቦታ በግራ ቀኙ ስምምነት ይከፋፈል :: በስምምነት መከፋፈል ካልቻሉ በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡን እኩል ይካፈሉ::
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ::



የሰበር መ/ቁ. 16109

ሚያዝያ 12 ቀን 1999 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ አሰግድ ጋሻው
አቶ መስፍን እቁበዮናስ

**አመልካች፡-** አቶ ከበደ አርጋው

**መልስ ሰጪ፡-** እነ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

*የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ - የእግድ ትዕዛዝ፣ የእግድ ትእዛዝ እንዲነሳ ስለመጠየቅ፣ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭን በማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ ማስመዝገብ፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1587-1620፣ 1613፣ 1614 2878*

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የማይንቀሳቀስ ሽያጭ ውል በማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ ላይ እስካልተመዘገበ ድረስ በሦስተኛ ወገን ላይ ወቃወሚያ ሊሆን አይችልም ሲል የሰጠውን ውሣኔ በማፅናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው::

<u>**ውሣኔ፡ -**</u> የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል::

1. አንድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭን የሚመለከት ውል በመዝገብ የሚጻፍበት ቀንና የንብረቱ የባለቤትነት ስም የሚዛወርበት ቀን ልዩነት ሊኖረው ይችላል::
2. ውሉ በመዝገቡ እስከተፃፈ ድረስ ሶስተኛ ወገኖች የስሙን አለመዛወር መሰረት በማድረግ ሊከራከሩ እንዲችሉ ሕጉ አይፈቅድላቸውም::
3. የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2878 የሽያጭ ውል በሶስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረው በተዋዋዮች ላይ ውላቸውን በመዝገቡ እንዲፃፍ ከማድረግ የዘለለ ግዴታ አይጥልባቸውም::
4. ሽያጭ በመዝገብ ውስጥ ማስፃፍ ማለት በሚመለከተው ማህደር ውስጥ ውሉን በማያያዝ የሚጠቃለል ነው::

የሰበር መ/ቁ. 16109

ሚያዝያ 12 ቀን 1999 ዓ.ም.

ዳኞች፡- 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. ፍስሐ ወርቅነህ

3. አብዱልቃድር መሐመድ

4. አሰግድ ጋሻው

5. መስፍን እቁበዮናስ

**አመልካች፡-** አቶ ከበደ አርጋው ከጠበቃው ጋር ቀርቧል፡፡

**መልስ ሰጪ፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነ/ፈጅ ቀርቧል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ለዚሁ የሰበር ጉዳይ መነሻ የሆነው አመልካች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 158ን በመጥቀስ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ሰኔ 20 ቀን 1994 ዓ.ም. ወረዳ 23 ቀበሌ 12 የቤት ቁጥሩ 153 በሆነ ቤት ላይ የሰጠው የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሳላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ በመድረጉ ነው፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤት ይህን የእግድ ትእዛዝ የሰጠው በአሁን መልስ ሰጪ ንግድ ባንክና በአቶ ቦጋለ ቲጋ መካከል በነበረ ክርክር ምክንያት ሲሆን ቤቱ የታገደው አቶ ቦጋለ ቲጋ በነበረባቸው የባንክ እዳ ምክንያት ነው፡፡ የአሁን አመልካች በቤቱ ላይ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ እንዲነሳ ሲጠይቁ ለማመልከቻቸው መነሻ ያደረጉት ቤቱን በ1987 ዓ.ም. ከተከሰሰ ከአቶ ቦጋለ ቲጋ የገዙት መሆኑን፣ ውሉ በውል አዋዋይ ፊት የተፈፀመ መሆኑንና የቤቱን ካርታ የተረከቡ መሆኑን ቤቱን ሲገዙ ቤቱ እዳና እገዳ ያልነበረበት መሆኑ ከየዞኑ ፋይናንስ ቢሮና ከባንክ የተጣራ መሆኑን ነው፡፡

ከፍተኛው ፍርድ ቤት የመልስ ሰጪን መቃወሚያ ከተቀበለ በኂላ የአመልካችን ጥያቄ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ መልስ ሰጪ ያቀረበው ተቃውሞ በዋናነት አመልካች አደረግኩት የሚሉት የሽያጭ ውል የፍትሐብሔር ሕግ ቁ. 2878 በሚያዘው መሠረት በማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ ስላልተመዘገበ እግዱ የተሰጠው በአቶ ቦጋላ ቲጋ ስም በተመዘገበ ቤት ላይ እንጂ በአመልካች ቤት ላይ አይደለም፣ የአዲስ አበባ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ሰኔ 19 ቀን 1994 የተሰጠውን የእግድ ትዕዛዝ ተግባራዊ ያደረገው ቤቱ በአሁን አመልካች ባለመመዝገቡ ነው የሚል ነው፡፡ ጥያቄው የቀረበለት የከፍተኛው ፍ/ቤትም ቤቱ ላይ የእግድ ትእዛዝ የተሰጠው በሥር ተከሣሽ በአቶ ቦጋለ ቲጋ ስም የተመዘገበ መሆኑ ከተረጋገጠ በኂላ መሆኑን የአመልካች የሽያጭ ውል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2878 መሠረት በማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ ላይ እስካልተመዘገበ ድረስ በ3ኛ ወገን



ላይ መቃወሚያ ሊሆን እንደማይችል በመግለጽ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ በሥር ተከሣሽ በአቶ ቦጋለ ቲጋ ሥም ተመዝግቦ በሚገኝ ቤት እንጂ በአሁን አመልካች በአቶ ከበደ አርጋው ስም በተመዘገበ ቤት ላይ ባለመሆኑ እግዱ የሚነሳበት ምክንያት የለም በማለት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አደረገ፡፡ አመልካች ይግባኝ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም ይግባኙም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ከሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ትእዛዝ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአቤቱታው መሠረታዊ ሀሣብ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ የሚጠቃለል ነው፡፡

1. ዕግድ የተሰጠበት ቤት ግንቦት 9 ቀን 1987 ዓ.ም. በተደረገና በውልና ማስረጃ በተመዘበ የሽያጭ ውል ለአሁን አመልካች የተሸጠ መሆኑን ይህም ውል ለሥራና ከተማ ልማት ቀርቦ ከማኀደሩ ጋር የተያያዘ መሆኑ የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ሐምሌ 18 ቀን 1994 ዓ.ም. በተ.ቁ. 2/በ-1277/125 በፃፈው ደብዳቤ ለፍርድ ቤቱ ያሳወቀ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 154 መሠረት በቤቱ ላይ የእግድ ትእዛዝ መስጠት ትክክል አልነበረም፡፡
2. ከፍተኛው ፍ/ቤት የተጠቀሰው ቤት ለአመልካች ግንቦት 9 ቀን 87 ዓ.ም. የተሸጠ መሆኑን በመግለጽ የአ/አ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ያቀረበለትን ማረጋገጫ ወደጎን የተወው ያለአግባብ ነው፡፡
3. ቤቱ የተሸጠ መሆኑ ከሚመለከተው ክፍል ቀርቦለት እያለ አመልካች የሽያጭ ውሉን አላቀረበም ማለቱ ትክክል አይደለም፡፡
4. የሽያጭ ውሉ በውልና ማስረጃ ከመረጋገጡም በላይ ለሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ቀርቦ ከማህደሩ ጋር በመያያዙ የፍ/ሕግ/ቁ. 2878 መስፈርት አልተሟላም መባሉ አግባብ አይደለም፡፡
5. የከተማ ልማት ቢሮ የፃፈው ደብዳቤ የለም፤ ዝውውሩ አለመፈፀሙ እንጂ ውሉ በማይንቀሳቀስ ንብረት አለመመዝገቡን አልገለፀም የሚሉ ናቸው፡፡

መልስ ሰጪ በጉዳዩ ላይ የጽሁፍ መልስ አቅርቧል ዋና ዋና ነጥቦቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የእግድ ትእዛዝ የተሰጠው ተጠቃሹ ቤት በአቶ ቦጋለ ቲጋ ስም የተመዘገበ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፡፡
2. የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ፃፈ የተባለውን ደብዳቤ በማስመልከት በሥር ፍ/ቤት ክርክር ስላልተደረገ በአሁን ደረጃ ክርክር መቅረብ አይችልም፡፡
3. አመልካች አለኝ የሚሉትን የሽያጭ ውል ለከፍተኛውም ሆነ ለጠቅላይ ፍ/ቤት አለማቅረባቸው የሽያጭ ውሉ በእርግጥ አለመፈፀሙ የሚያመለክት ነው፡፡
4. ጉዳዩ የሚመለከተው የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በሥር ተከሣሽ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ በማረጋገጡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2878 መስፈርት ተሟልቷል ሊባል አይችልም፡፡
5. ተደረገ የተባለው የሽያጭ ውል በውልና ማስረጃ መረጋገጡም ሆነ የውሉ ቅጂ ከሚመለከተው ማኅደር ቀርቧል መባሉ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2878 በሚያዘው መሠረት ምዝገባው በአሁን አመልካች ስም መፈፀሙን የሚያመለክት አይደለም፡፡
6. ቤቱ በሥር ተከሣሽ ስም የተመዘገበ በመሆኑ እግዱ ተገቢ ነው ሊነሳም አይገባውም፡፡

አመልካቹ በመልስ ሰጪ ለቀረበው መልስ በጽሁፍ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡ ይህ ችሎት የቀረበውን ክርክር አግባብ ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮአል፡፡ በቀረበው ጉዳይ ላይ ውሣኔ ለመስጠት አመልካች ውሉን በሚመለከተው አካል የሽያጭን ውል ካስመዘገበ የቤቱ ስም ባለመዛወሩ ብቻ ባለቤትነት የለውም ሊባል ይችላል? የሚለውን ከተጓዳኝ ሌሎች ነጥቦች ጋር መመልከት ያስፈጋል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት መዝገብ አስቀርበን እንተመለከትነው የአዲስ አበባ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ሐምሌ 18 ቀን 1994 ዓ.ም. ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በላከው ደብዳቤ ስሙ በአሁን አመልካች የተዛወረ ባይሆንም አመልካችና አቶ ቦጋለ ቲጋ የሽያጭ ውል መፈጸማቸው፣ ይኸው ውል በውልና ማስረጃ የተመዘገበ መሆኑ፣ ይኸው ውል ቤቱን በሚመለከት ማኅደር ውስጥ መያዙን ገልጿል፡፡ አግባብነት ያለው የደብዳቤው ክፍል፡-

> “ፍ/ቤቱ በሰጠው ትእዛዝ መሠረት በመሥሪያ ቤታችን የሚገኘውን የአቶ ቦጋለ ቲጋ ማኅደር አውጥተን እንዳየነው በወረዳ 23 ቀበሌ 12 የቤት ቁጥር 153 በግለሰቡ ስም የተመዘገበ ሲሆን ግለሰቡ ከላይ በተጠቀሰው ወረዳና ቀበሌ የሚገኘውን መኖሪያ ቤት ግንቦት 9 ቀን 1987 በውልና ማስረጃ ምዝገባ መምሪያ ባደረጉት ውል ለአቶ ከበደ አርጋው ሸጠው ውሉ በማኅደሩ ውስጥ ተያይዞ የሚገኝ እና የስም ዝውውሩ ያልተፈፀመ መሆኑን ለተከበረው ፍ/ቤት እየገለጽን ፍ/ቤቱ በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ይዞታውን በነበረበት ሁኔታ በማስከበሪያ መዝገብ ላይ መዝግበን ያገድን መሆኑን እንገልፃለን” የሚል ነው፡፡



ከዚህ ደብዳቤ ይዘት ለመገንዘብ እንደሚቻለው የአሁን አመልካች የሽያጭ ውሉን አዋዋይ ፊት ከመፈፀም ባሻገር የሽያጭ ውሉ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል አቅርበው ከማኅደሩ ጋር እንዲያያዝ አድርገዋል፡፡ የሽያጭ ውሉ ከማኅደሩ ጋር የተያያዘው መቼ እንደሆነ በደብዳቤው ላይ ባይገለጽም ፍ/ቤት የእግድ ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት መያያዙ ግን ከደብዳቤ ይዘት መገንዘብ ይሻላል፡፡ ውሉ በውልና ማስረጃ ፊት ቀርቦ የተፈፀመውም ግንቦት 9 ቀን 1987 ዓ.ም. መሆኑም ከዚሁ ደብዳቤ ይዘት መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ ያም ሆኖ ጉዳዩ የቀረበለት መስሪያ ቤት የስም ዝውውሩን በአመልካች ስም አላደረገም፡፡ በዚህም ምክንያት ደብዳቤው በተፃፈበት በሐምሌ 18 ቀን 1994 ዓ.ም. የቤቱ ስም የተመዘገበው በሻጩ በአቶ ቦጋለ ቲጋ እንጂ በአሁኑ አመልካች አይደለም፡፡ የከፍተኛውም ፍርድ ቤት ለውሣኔው መሠረት ያደረገው ማኅደሩ ውስጥ የሚገኘውን አጠቃላይ ይዞታ ሳይሆን ቤቱ ትአዛዙ በተሰጠበት ወቅት በማን ስም ነበር የሚለውን ነጥብ ብቻ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ የጠቀሰው የፍትሐብርሄር ሕግ ቁ. 2878 “ያንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ንብረቱ ባለበት አገር በሚገኘው በማይንቀሣቀስ ሀብት መዝገብ ካልተፃፈ በቀር በሦስተኛ ወገኖች ዘንድ ውጤትን ሊያስገኝ አይችልም” በማለት ይደነግጋል፡፡ በመሠረቱ ይህ ድንጋጌ የሚጠይቀው የሽያጭ ውሉ በመዝገብ ውስጥ መፃፍ እንዳለበት ነው፡፡ ስለዚህ የሦስተኛ ወገኖችን በሚመለከት ተዋዋዮቹ ጥበቃ የሚያገኙት ውሉ በመዝገቡ ከተፃፈበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡ ውሉ በመዝገብ በተፃፈበት ቀንና ስሙ ወደገዢው በተዛወረበት ቀን ልዩነት ሊያሰጥም እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ የስም ዝውውር ውሉን ከማቅረብ በተጨማሪ ሌሎች ጉዳዮችን ሟሟላት የሚጠይቅ በመሆኑ ውሉ በቀረበበትና በተፃፈበት ቀን ላይጠይቁት ይችላል፡፡ ውሉ በመዝገቡ እስከተፃፈ ድረስ ግን ሦስተኛ ወገኖች የስሙን አለመዛወር መሠረት በማድረግ ሊከራከሩ እንዲችሉ ይህ ድንጋጌ አይፈቅድላቸውም፡፡ የሕጉ መሠረታዊ ዓላማ ሦስተኛ ወገኖች የማይነቀሣቀሰው ሀብት በማስመልከት የተፈፀሙ ሕጋውያን ተግባራት እንዲውቁ ማስቻል ነው፡፡ ይህ ዓላማ የሽያጭ ውሉ በመዝገቡ ውስጥ እንዲፃፍ በማድረግ ማሳካት ይችላል ከሚል መንደርደሪያ የተነሣው የፍትሐብሔር ሕጉ 2878 የሽያጭ ውሉ በሦስተኛ ወገን ላይ ውጤት እንዲኖረው በተዋዋዮቹ ላይ ውላቸውን በመዝገቡ እንዲፃፍ ከማድረግ የዘለለ ግዴታ አይጥልባቸውም፡፡ ውሉ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረው ከውሉ መመዝገብ በተጨማሪ የማይንቀሣቀሰው ንብረት ሀብትነት በገዢው ስም መዛወር አለበት የሚል ድንጋጌ የለውም፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች የፈፀመው የሽያጭ ውል በሦስተኛው ወገን ላይ ውጤት ይኖረዋል ወይም አየኖረውም ለማለት ማጣራት የነበረበት ውሉ በማይንቀሣቀስ ንብረት መዝገብ ውስጥ

መፃፍ አለመፃፉን እንጂ ስሙ በአመልካች መዛወር አለመዛወሩን መሆን አልነበረበትም፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ጉዳዩ የሚመለከተው የአዲስ አበባ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በአመልካችና በአቶ ቦጋለ ቲጋ ተጠቃሹን ቤት በማስመልከት የተፈፀመው ውል በማህደሩ ውስጥ መያያዙን ለፍርድ ቤቱ አስታውቋል፡፡ ሽያጭ በመዝገብ ውስጥ መፃፍ ማለት በሚመለከተው ማህደር ውስጥ ውሉን ማያያዝ የሚያጠቃልል መሆኑ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1613 እና 1614 ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከፍትሐብሔር ሕግ 1587-1620 ያሉት የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች እንደሚያመለክቱት ምዝገባ የሚከናወነው መዝጋቢው አካል የሚያቀርበውን ፎርም በመጠቀም አስፈላጊ ዝርዝር ጉዳዮችን ማህደሩ ውስጥ እንዲካተት በማድረግ ነው፡፡ አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካች እነዚህ ፎርሞች በሚመለከተው አካል ቀርበውለት አለመሙላቱን የሚገልጽ ነገር ለፍርድ ቤቱ አልቀረበም፡፡ ይልቁንም የሽያጩን ዝርዝር የሚያመለክት የሽያጭ ውል ለሚመለከተው አካል አቅርቦና ተቀባይነት አግኝቶ ከማህደሩ ጋር ለማያያዙ ተገልፆአል፡፡

ይህ መሆኑ ሲረዳ ፍ/ቤቱ ባንክ እንደሸጥለት ጥያቄ ያቀረበበት ቤት የአሁን አመልካች መሆኑን በመገንዘብ የእግድ ጥያቄው ውድቅ ማድረግ ነበረበት፣ በወቅቱ እግዱን ቢሰጥ እንኳን አመልካቹ እግዱ ይነሣልኝ ብሎ ሲጠይቅ ጥያቄውን ተቀብሎ የሰጠው እግድ ማንሣት ነበረበት የአመልካችና የአቶ ቦጋለን የሽያጭ ውል በሚመለከት መልስ ሰጪ ባንክ ሦስተኛ ወገን ነው፡፡ ስለዚህ የሽያጭ ውሉ በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 2878 አባባል በማይንቀሣቀስ ሀብት መዝገብ ሲፃፍ በባንኩ ላይ ውጤት ይኖረዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ ቤቱ አሁንም በአቶ ቦጋለ ቲጋ ስም የሚገኝ ነው በማለት የሰጠው የፍርድ ትእዛዝ የዚህን ሕግ ግልጽ ድንጋጌ የሚጥስ የአንድ ሰው ሀብት ለሌላ ሰው እዳ ማስፈጸሚያ እንዲውል የሚያደርግ በመሆኑ ትክክል አይደለም፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 14428 ሰኔ 19 ቀን 1994 ዓ.ም በወረዳ 23 ቀበሌ 12 በቤት ቁጥር 153 የሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡
2. ከላይ የተጠቀሰው ቤት አመልካች የገዙትና በማይንቀሣቀስ ሀብት ሽያጭ ውሉ እንዲመዘገብ ያደረጉ በመሆኑ በመልስ ሰጪ እና በአቶ ቦጋለ ቲጋ መካከል ለነበረው የአፈፃፀም ክስ ማስፈፀሚያ ሊሆኑ አይገባም፡፡
3. ከላይ በተራ ቁጥር 1 የተጠቀሰውን በሚመለከት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 14428 የተሰጠው ትእዛዝ ተሻሽሏል፡፡
4. መዝገቡ ስለተወሰነ ከከፍተኛ ፍ/ቤት የመጣው መዝገብ ይመለስ፡፡



የሰበር መ/ቁ. 14094

ሚያዝያ 18/1999

**ዳኞች**፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አሠግድ ጋሻው

አቶ መስፍን እቁበዮናስ

ወ/ት ሒሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች**፡- የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት

**ተጠሪ**፡- የአቶ ሰለሞን ወረደ ወራሽ ሕፃን አብይ ክብሩ

*የንብረት ክርክር - ኪራይ የተወረሰ ንብረት - ክስ የማቅረብ መብት የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1195፣ አዋጅ ቁ. 47/67፣ የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 33/2/*

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ክርክር የተነሳበትን ቤት ለተጠሪ ሊለቅ ይገባል ሲል የሰጠውን ውሣኔ በማጽናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>**ውሣኔ፡ -**</u> የፌዴራል መጀመሪያና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. ለረጅም አመታት በመንግሥት እጅ የነበረ ቤትን በተመለከተ ባለቤት ነኝ የሚል ወገን ቤቱ በአዋጅ ቁ. 47/67 የተፈቀደለት መሆኑን ወይም ያለአግባብ ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል ጥያቄውን አቅርቦ ውሣኔ አግኝቶ ባለመብት ስለመሆኑ ማስረዳት አለበት፡፡
2. አንድ ከሳሽ ለክሱ መነሻ በሆነው ነገር ወይም ክሱ በተመሰረተበት ሃብት ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው መሆኑን ካላረጋገጠ ክስ እንዲያቀርብ አይፈቀድለትም፡፡

የሰበር መ/ቁ. 14094

ሚያዝያ 18/1999

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አቶ አሠግድ ጋሻው

3. አቶ መስፍን እቁበዮናስ

4. ወ/ት ሒሩት መለሠ

5. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት - ነገረፈጅ አቶ አንበርብር አባይነህ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአቶ ሰለሞን ወረደ ወራሽ ሕፃን አብይ ክብሩ ሰለሞን የሚች ሚስትና ሞግዚት ወ/ሮ መሠረት ከበደ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ፍ ር ድ</u>

ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ አውራሽ አቶ ሰለሞን ወረደ በሥር ተከሣሽ ላይ ባቀረቡት ክስ ተከሣሹ በውርስ ያገኙትን ቤት በሕገወጥ መንገድ የያዙባቸው ስለሆነ እንዲለቀቅላቸው ጠይቀዋል፡፡ ተከሣሹም ቤቱን ከአመልካች የተከራዩላቸው አገር መከላከያ ሚ/ር በመሆኑ ሊከሠሡ እንደማይገባ ተከራክረዋል ፍ/ቤቱም አመልካቹና የአገር መከላከያ ሚ/ር እንዲገቡ በማድረግ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ተከሣሹንና የአገር መከላከያ ሚ/ርን በነፃ ከክሱ በማሰናበት ክርክር የተነሣበት ቤት የከሣሽ አባት ቤት መሆኑና ከሣሹም የሣቸው ወራሽ መሆኑ ስለተረጋገጠ አመልካች ቤቱን ለከሣሽ እንዲያስረክብና የ6 ወር ኪራይ ብር 12.000 /አስራ ሁለት ሺህ/ እንዲከፍል ወስኗል፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ መልስ ሰጪን ሣይጠራ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የቅሬታ ነጥቡም ክርክር የተነሣበትን ቤት ባለቤትነት ለማሥረዳት የቀረበው ካርታና የቤት ስራ ፈቃድ ባለቤትነትን አያስረዳም፣ በፍ/ሕ/ቁ. 1195 መሠረት ከተገቢው የመንግሥት አካል የተሰጣቸው የባለቤትነት ምስክር ወረቀት አልቀረበም፣ ከአ/ቁ. 47/67 መሠረት ከታህሣሥ 11/1967 ጀምሮ የከተማ ቤት በንብረትነት የያዘ ግለሰብ ወይም ድርጅት መብቱ በሚኒስትሩ ካልፀደቀ በቀር ንብረትነቱ አይፀናለትም የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም ቤቱ እንዲመለስም ሆነ ኪራይ እንዲከፈል የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም



ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም በቃል ባደረገው ማጣራት ቤቱን ያስተዳድረው የነበረው የአሁኑ አመልካች እንደሆነና የሥር ከሣሽ ቤቱን የያዙት በ1983 መሆኑን ተረድቷል፡፡ መዝገቡንም እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከመዝገቡ የተጠሪው አውራሽ ክስ ያቀረቡት ከአባቴ በውርስ ያገኘሁትን ቤት የሥር 1ኛ ተከሣሽ ያላግባብ ስለያዙብኝ ይልቀቁልኝ፣ ኪራዩንም ይክፈሉኝ የሚል ነው፡፡ ከሥር ፍ/ቤት ከተደረገው ክርክርና በዚህ ችሎትም በተደረገው ማጣራት ክርክር የተነሣበትን ቤት 1ኛ ተከሣሽ የያዙት በኪራይ መሆኑን፣ ቤቱን ያከራየውም አመልካች መሆኑን፣ ቤቱ በ1983 በሥር ከሣሽ ከመያዙ በፊት ያስተዳድረው የነበረው አመልካች መሆኑን፣ አሁንም ቤቱ በአመልካች የሚተዳደር መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እንግዲህ ይህ ቤት ለረዥም አመታት በመንግሥት እጅ የነበረ ሲሆን የተጠሪ አውራሽ ቤቱ በአ/ቁ 47/67 የተፈቀደላቸው እና ባለንብረት በመሆናቸው ወይንም ደግሞ ያላግባብ ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚሉም ከሆነ ለሚመለከተው አካል ጥያቄአቸውን አቅርበው ውሣኔ አግኝተው ባለመብት ስለመሆናቸው ያስረዱት ነገር የለም፡፡ የተጠሪ አውራሽ ቤቱን በ1983 መያዛቸውን ቢገልፁም በምን ሁኔታ እንደያዙት ያቀረቡት ነገር የለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ቤቱ እንዲመለስላቸው ክስ ሲያቀርቡ በቤቱ ላይ ያላቸውን መብት አላረጋገጡም፡፡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/ አንድ ከሣሽ ለክሱ መነሻ በሆነው ነገር ወይም ክሱ በተመሠረተበት ሀብት ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው መሆኑን ካላረጋገጠ ክስ እንዲያቀርብ አይፈቀድለትም፡፡

ባመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች በሥር ከሣሹ አባት ስም የቀረበውን ካርታና የቤት ሥራ ፈቃድ መሠረት አድርገው ከሣሹ ክሱን ባቀረቡ ጊዜ በቤቱ ላይ የነበራቸውን መብት ሣያረጋግጥ ቤቱን እንዲረከቡና ኪራይ እንዲከፈላቸው በመወሰኑ የሕግ ሥህተት መፈፀሙን ተረድተናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 3269 ሚያዚያ 6/1995 የሰጠው ውሣኔና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 21007 ታህሣሥ 19/1996 የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የተጠሪ አውራሽ ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ያላቸው መሆኑን ስላላረጋገጡ ክሱ ተቀባይነት የለውም፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የሰበር መዝገብ ቁ. 17937

መጋቢት 20 ቀን 1999

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ አሰግድ ጋሻው
አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ድንቄ ተድላ

**ተጠሪዎች፡-** እነ አቶ አባተ ጫኔ

*ውርስ - ይርጋ - የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1000 አፈጻጸም - ጋብቻ በአንደኛው ተጋቢ ሞት መፍረስ - ጋብቻ በሞት በፈረሰ ጊዜ የግል ንብረት የሚወሰድበት ጊዜ - የውል ህግ ድንጋጌዎች በሌሎች ግዴታዎች ላይ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ - የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 17፣ 684፣ 1000፣ 1677፣ 1845*

የአማራ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረቡትን የይርጋ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ በመስጠቱ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

**<u>ውሣኔ፡ -</u>** የአማራ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሸሮ የጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

1. በፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1000/1/ ና /2/ ላይ የሰፈረው የይርጋ ጊዜ ተፈጻሚ የሚሆነው አንድ ወራሽ በሌላ በወራሽነት የውርስ ሀብት በያዘ ሰው ላይ ክስ ሲያቀርብ ነው፡፡
2. ተከራካሪዎች የይርጋ ጥያቄ እስካቀረቡ ድረስ ጥያቄውን በትክክለኛው አንቀጽ መሰረት እንዲመራ ማድረጉ የፍርድ ቤት ሃላፊነት ነው፡፡
3. ጋብቻ በአንደኛው ተገቢ ሞት ምክንያት በፈረሰ ጊዜ የጋራም ሆነ የግል ንብረት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መጠየቅ እንዳለበት ባይመለከትም በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677 መሠረት በቁ. 1845 ላይ የተቀመጠው ይርጋ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡



የሰበር መዝገብ ቁ. 17937

መጋቢት 20 ቀን 1999

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ አሰግድ ጋሻው
አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ድንቄ ተድላ - ጠበቃ ማሞ ስበር ቀርበዋል

**መልስ ሰጪ፡-** (1) አቶ አባተ ጫኔ - ወኪሉ ቀርበዋል
(2) አቶ ፍስሀ መልካሙ - ቀርበዋል

በዚህ መዝገብ የቀረበው የሰበር ጉዳይ መርምረን ቀጥሎ የተመለከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የውርስ ሕግን በርካታ ድንጋጌዎች የሚመለከት ሲሆን በዋናነት በሰበር ፍርድ ቤት የቀረበን የይርጋ ጥያቄ የሚያስተናግድ ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጪዎች በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ አውራሻችን ደጃዝማች ጫኔ የመረጡ ከቀድሞው ንጉሴ ኃ/ሥላሴ በስጦታ ያገኙትን የግል ቤት የሟች ሚስት የሆኑት የአሁን አመልካች የሌላቸውን የወራሽነት መብት አለኝ በማለት ቤትና ቦታው አለአግባብ በስማቸው እንዲዞር ጠይቀዋል፡፡ በመሆኑም አመልካችዋ ያለአግባብ የያዙብንን የአውራሻችንን ቦታ ያስረክቡ የሚል ነበር የአሁን መልስ ሰጪዎች ያቀረቡት ክስ የቤቱን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ለአሁን አመልካች በሕገወጥ መንገድ ሰጥቷል በማለት የጉንደር ከተማ ማዘጋጃ ቤትን 2ኛ ተከሣሽ በማድረግ ከሰዋል፡፡

የአሁንዋ አመልካች ሟች ደጃዝማች ጫኔ የመረጡ የሞቱት በ1978 ሲሆን ክስ የቀረበው በ1990 ዓ.ም በመሆኑ ጉዳዩ በይርጋ ይታገዳል በማለት የይርጋ ጥያቄ አነሱ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ዝርዝር መልስም አቀረቡ፡፡ በተነሣው የይርጋ ጥያቄ ላይ በየደረጃው ያሉ ፍርድ ቤቶች የተለያየ ውሣኔ ሰጡ፡፡ ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ውሣኔ የሰጠው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይርጋው ጥያቄ ውድቅ በማድረግ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የይርጋውን ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ የሰጠው ምክንያት የፍትሐብሔር ሕግ ቁ. 1000(1) በዚሁ ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት የለውም በማለት

ነው፡፡ ይኸው ድንጋጌ ተፈፃሚ አይሆንም ያለውም በሁለት ምክንያት ነው፡፡ አንደኛው ምክንያት ድንጋጌው በወራሾች መካከል የሚነሳን ክርክር የሚመለከት እንጂ በሟች ሚስት እና በወራሾች መካከል የሚነሣ ሙግትን የሚሸፍን አይደለም የሚል ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ጥያቄ የቀረበበት ቤት ርስት በመሆኑ በድንጋጌው አይታቀፍም በማለት ነው፡፡ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይህን ምክንያት በመስጠት ቀደም ሲል የይርጋው ጥያቄ ተቀብሎ የነበረውን የጉንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሯል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ሲሆን ይዘቱ የይርጋውን ጥያቄ መታለፍን የሚመለከትና ሌሎቹንም ጠቅላይ ፍ/ቤት የጉዳዩ ፍሬ ነገር ላይ የሰጣቸውን ውሣኔዎች የሚመለከት ነው፡፡

ይህ ችሎት የይርጋው ጥያቄ አስመልክቶ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የሰጠውን ውሣኔ ትክክለኛነት ለመመልከት ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ብሎ መልስ ሰጭዎች መልስ እንዲሰጡበት አድርጓል፡፡ መልስ ሰጪዎች ባቀረቡት መልስ የይርጋ ጥያቄውን በሚመለከት ዘርዘር ያለ ክርክር አቅርበዋል፡፡ የክርክራቸው መሠረተ ሀሣብ የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀፅ 1000(1) ተፈፃሚነት የሚኖረው አንድ ወራሽ ሌላውን በወራሽነት ዓቅም የውርስ ሀብት የያዘን ሰው ሲከስ ነው፣ አመልካች ንብረቱን የያዙት በሚስትነት እንጂ በወራሽነት ባለመሆኑ ድንጋጌው አግባብነት የለውም፤ ከዚህ ባሻገር በአንቀጽ 1000/2/ እንደተመለከተው አከራካሪ ንብረት ከቤተሰብ የተገኘ ንብረት በመሆኑ በሦስት ዓመቱ ይርጋ ሊታጠር አይገባውም፣ ቤቱ በአመልካች መያዙን መልስ ሰጪዎች ያወቁት በ1999 ዓ.ም ክስ ሲያቀርቡ በመሆኑ ካወቁበት ጊዜ ሲቆጠር የይርጋው ጊዜ አልፎባቸዋል ሊባል አይችልም፣ የሚል ነው፡፡

ይህ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያቀረቡትን የይርጋ ክርክር አግባብ ካላቸው የሕጉ ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ መርምሮአል፡፡

ችሎቱ በቅድሚያ የተመለከተው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 (1) እና (2) ተፈፃሚነትና ከአሁን ጉዳይ ጋር ያለው ተዛማጅነት ነው፡፡ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ በዚህ አንቀፅ የሰፈረው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚ የሚሆነው አንድ ወራሽ በሌላ በወራሽነት የውርስ ሀብት በያዘ ሰው ላይ ክስ ሲያቀርብ ነው የሚል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ የሕጉ አተረጓጉም ይህ ፍ/ቤትም ይስማማል፡፡ የአሁን አመልካች የሟች ወራሽ ባለመሆናቸውና ንብረቱንም የያዙት በወራሽነት ስላልሆነ በዚህ ሕግ የተጠቀሰው የ3 ዓመት የይርጋ ጊዜ ወራሾች በሚያነሱት ክስ ላይ ሊጠቅማቸው አይችልም፡፡ የዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ይርጋው የሚቆምበትን የመጨረሻ ጊዜ የሚሰጥ ከሚሆን በቀር መነሻ - ሀሣቡ በአውራሾች መካከል የሚደረግን ክስ የሚመለከት በመሆኑ ይኸው ድንጋጌም ለጉዳዩ አግባብነት የለውም በመሆኑም ጠቅላይ ፍ/ቤቱ መልስ ሰጪዎች ያቀረቡት ክስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000(1) መሠረት በ3 ዓመት በይርጋ አይታገድም በማለት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ቀጥሎ የሚነሣው



ጥያቄ ክሱን በ1000/1/ መሠረት በይርጋ አይታገድም ማለት የዚህ ዓይነት ክስ ጭራሽ ይርጋ አይመለከተውም ማለት ነው? የሚለው ነው፡፡

የስር ከሣሾች በአሁንዋ አመልካች ያቀረቡት በይዞታቸው ያደረጉት የአባታችን ንብረት ይመልሱልን የሚል ነው፡፡ ከመዝገቡ ለመረዳት የቻልነው አመልካችና የመልስ ሰጪዎች አውራሽ ባልና ሚስት ሆነው ለረዥም ዓመታት አብረው ከኖሩ በኋላ የመልስ ሰጪ አውራሽ በ1978 ዓ.ም መሞታቸው ነው፡፡ አመልካችና ሟች ደጃዝማች ጫኔ የመረጡ ባልና ሚስት ከነበሩ በሁለቱም መካከል የነበረው ጋብቻ የፈረሰው በ1978 ዓ.ም ነው ማለት ነው፡፡ የፍትሐብሔር ሕጉ ጋብቻ ሲፈርስ በሁለቱም ተጋቢዎች መካከል ያለው ንብረት ሕጉ በሚያዘው መሠረት መከፋፈል እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ በጋብቻው የነበረው ንብረት መከፋፈል ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ በምን ያህል ጊዜ ነው አንድ ሰው በክፍፍሉ የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብት ያለአግባብ ለሌላኛው ተጋቢ ተሰጥቶብኛል ማለት የሚችለው? የሚለው ነው፡፡ ለጉዳዩ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው የፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 17 ጋብቻ በአንዱ ተጋቢ ሞት ምክንያት ሲፈርስ "ከተጋቢዎቹ እያንዳንዱ የግል ሀብቱ መሆኑን አስረድቶ የግል ድርሻ ሀብት በዓይነቱ መልሶ ለመውሰድ መብት አላቸው" በማለት በአንቀጽ 684 ደንግጓል፡፡ ይህ ድንጋጌ ጋብቻው ሲፈርስ እያንዳንዱ ተጋቢ የራሱ ንብረት መሆኑን የማስረዱት ኃላፊነት እንዳለበት የሚያሣይ ሲሆን ይህን ጥያቄ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለበት ግን አይደነግግም፡፡ ጥያቄው በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለበት በግልጽ አለመደንገጉ ግን ይህ በይርጋ ሕግ የማይገዛ አንደኛው ወገን በፈለገ ጊዜ የሚያነሣው ነው ወደሚል መደምደሚያ የሚወስድ አይደለም፡፡ በጋብቻ ጊዜ የተፈራው ሀብትም ሆነ በግል የተፈራው ሀብት ሣይከፋፈል ለረዥም ጊዜ መቆየት ያለበት አይደለም በመሆኑም የሕጉ እሳቤ የዚህ ዓይነት ጥያቄ ያለገደብ ጋብቻው ከፈረሰ ከረዥም ጊዜ በኋላም እንዲነሣ ይፈቅዳል ብሎ ማሰብ አይችልም፡፡

ጋብቻ ልዩ ባህርይ ቢኖረውም ከሁለቱም ተጋቢዎች ስምምነት የሚመነጭ መብትና ግዴታም የሚጥል በመሆኑ በቤተሰብ ሕግ ግልጽ ድንጋጌ ሣይኖር ሲቀር በውል ሕግ መርሆች ወይም ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ማድረግ የውል ሕግ አንቀጽ 1677ም የሚፈቅደው ነው፡፡ ይኸው ድንጋጌ «ግዴታዎቹ ከውል የተገኙ ባይሆኑም የዚህ አንቀፅ ደንቦች ይፈፀሙባቸዋል» በማለት ይደነግጋል፡፡ አሁን የያዝነው የባልና ሚስት የንብረት ክርክር የተለየ የይርጋ ጊዜ ስለሌለው በዚህ ድንጋጌ መሠረት የውል ሕግ የይርጋ ድንጋጌዎች እንዲገዛ ማድረግ ተገቢ ሆኖ

አግኝተነዋል፡፡ የወል ሕግ ይርጋ አጠቃላይ ድንጋጌ በአንቀፅ 1845 እንደተገለፀው በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር 10 ዓመት ነው፡፡ አሁን በቀረበልን ጉዳይ ጋብቻው በሞት የፈረሰው በ1978 ዓ.ም ሲሆን የአንዱን ተግጋቢ የግል ንብረት በሕይወት ካሉት ተጋቢ ለማስለቀቅ ጥያቄ የቀረበው በ1990 ዓ.ም ነው፡፡ በመሆኑም ክሱ የቀረበው 10 ዓመት ካለፈው በኋላ በመሆኑ በይርጋ ሊታገድ የሚገባው ነው፡፡

ከዚህ በላይ በተገለፁ ምክንያቶች የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሕጉን አንቀጽ 1000(1) እና(2) በመመልከት ብቻ ከ12 ዓመት በኋላ የቀረበውን ክስ ይርጋ አያግደውም በማለት ክሱ እንዲቀጥል በማድረግ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሣኔ መስጠቱ ትክክል አይደለም፡፡ የአሁኑ አመልካች የይርጋ ጥያቄ እስከአቀረበ ድረስ ጥያቄውን በትክክለኛው አንቀጽ መሠረት እንዲመራ ማድረጉ ደግሞ የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ነው፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

(1) የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጥቅምት 24 ቀን 1997 በመዝገብ ቁጥር 0314 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

(2) መልስ ሰጪዎች የካቲት 11 ቀን 1990 ዓ.ም በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ በይርጋ ይታገዳል ብለናል፡፡

(3) ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡



የሰ/መ/ቁ. 20938

ሚያዝያ 11/99 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

ወ/ት ሒሩት መለሠ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሸዋዬ ተሰማ

**ተጠሪ፡-** እነ ወ/ሮ ሣራ ልንጋነ

*ጋብቻ - የጋብቻን መፍረስ ስለማስረዳት*

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ የሚች የአቶ ይልማ ወ/ሃና ሚስት ናቸው ሲል የሰጠውን ውሣኔ በማፅናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>**ውሣኔ፡ -**</u> የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. ጋብቻ የሚፈርሰው ህጉ ባስቀመጣቸው ውሱን ምክንያቶች ነው፡፡
2. ጋብቻ የሚፈርስበትን ምክንያት መፍረሱን ከማስረዳት መለየት ያስፈልጋል፡፡
3. ተጋቢዎች ምንም እንኳን ቀደም ብሎ የተፈፀመ ጋብቻ የነበራቸው ቢሆንም በመካከላቸው በተፈጠረ አለመግባባት ምክንያት መቀጠል አለመቻላቸውና ሁለቱ በየፊናቸው የየራሳቸውን ሕይወት መጀመራቸው እያለ ፍቺ መፈፀሙን አንደኛው ተጋቢ አላስረዳም የሚል ውሣኔ ትክክለኛ የህግ አተረጓጎም አይደለም፡፡

የሰ/መ/ቁ. 20938

ሚያዝያ 11/99 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ አሰግድ ጋሻው
ወ/ት ሒሩት መለሠ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሸዋዬ ተሰማ ቀርባለች፡፡

**መልስ ሰጪ፡-** ወ/ሮ ሣራ ልንጋነ አልቀረበችም፡፡

**ፍ ር ድ**

አመልካች ለሰበር ችሎት ያቀረቡት ማመልከቻ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መልስ ሰጪ የሟች የአቶ ይልማ ወ/ሃና ሚስት ነበሩ በማለት የሰጠው ውሣኔ እንዲሻርላቸው የሚጠይቅ ነው፡፡ አመልካች መ/ሰጪ የሟቹ የአቶ ይልማ ወ/ሃና ሚስት አይደሉም በማለት ተቃውሞ ያቀረቡት ለፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት ነው፡፡ ተቃውሞው ለዚህ ፍ/ቤት ያቀረቡት ፍ/ቤት ቀደም ሲል ግንቦት 15/95 በዋለው ችሎት መልስ ሰጪ ወ/ሮ ሣራ ልንጋነ የሟች የአቶ ይልማ ወ/ሃና ሚስት ነች በማለት በመስጠቱ ነው፡፡ ተቃውሞው የቀረበለት ፍ/ቤትም አመልካች ሚስት መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቅርበዋል በሌላ በኩል መልስ ሰጪ ከሟቹ ጋር ጋብቻ የነበራቸው መሆኑ ስለተረጋገጠና በአመልካቹ በኩል ውላቸው መፍረሱን የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ ቀደም ሲል መልስ ሰጪ የሟች ሚስት ናት በማለት የተሰጠው ውሣኔ የሚለወጥበት ምክንያት የለም በማለት ውሣኔው አጽንቶታል፡፡

አመልካች ይግባኝ ለከፍተኛው ፍ/ቤት ቢያቀርቡም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ማመልከቻውን አይቶ ይግባኙን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት አያስቀርብም በማለት ዘግቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡

የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ቅሬታ መልስ ሰጪ ከሟች ጋር የነበራት ጋብቻ በገዛ ፈቃዷ አፍርሳ ከሌላ ሰው ጋር ከ1977 በፊት ጀምሮ ትዳር በመመስረቷ የሟቹ ሚስት ፊት ሊባል አይገባም፣ ሟች ከአመልካች ጋብቻ የፈፀመው ሌላ ጋብቻ ስላልፈፀመ ነው፣ የመልስ መሰጪን ጋብቻ መፍረስ ያውቁ የነበሩ ምስክር ቀርበው እንዳይመሰክሩ መደረጉ እውነቱ እንዳይወጣ መደረጉን ያሳያል፡፡ አቶ ይልማ የሞቱት በ1989 ሆኖ ሣለ መልስ ሰጪ ግን በ1981 ነው የሞቱት ብላ ለፍ/ቤት ማመልከቷ ጉዳዩን የተቀነባበረና የሚስትነት ጥያቄውን ከ14 ዓመት በኋላ መቅረቡን ያስረዳል የሚል ነው፡፡



በመልስ ሰጪ የቀረበው መልስ ደግሞ መልስ ሰጪና ሟች መጋባታቸው በማስረጃ ስለተረጋገጠና ጋብቻ የሚፈርስባቸው በሕግ ከሚታወቅባቸው ምክንያቶት አንዱ መኖሩ ስላልተረጋገጠ የሟችና የመልስ ሰጪ ጋብቻ ፈርሷል ሊባል አይችልም፣ የሟችና የአመልካች ጋብቻ መጀመሪያ የተፈፀመውን ጋብቻ አያስቀርም፣ መልስ ሰጪ ከሌላ ሰው ሁለት ልጆች መውለዳቸውም ሆነ የሞቱበትን ቀን 1981 ብለው መጥቀሳቸውም እንደዚሁ ሚስትታቸውን አያስቀርም፤ የሚስትነት ማረጋገጫው የተሰጠው ሟቹ በ1989 ዓ.ም. ሞተዋል በማለት በመሆኑ የአመልካች ቅሬታ መሠረት የለውም፣ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ የሕግ ስህተት ስለሌለበት ሊፀና ይገባል የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብ ካላቸው ሕጎች ጋር በማያያዝ ተመልክቷል፡፡ ከመዝገቡ እንደተረዳነው አመልካችም ሆነ መልስ ሰጪ ከሟች አቶ ይልማ ወ/ሃና ጋር ጋብቻ መፈፀማቸው ተረጋግጦአል፡፡ መ/ሰጪ ሚስት መሆናቸውን ለማረጋገጥ በ1966 የተጋቡበት የጋብቻ ውል በ6/6/72 የተሞላ የሕይወት ታሪክ /ሟች ይሰሩበት ከነበረው የቡና ገበያ ድርጅት ማኀደር የተገኘ/ እንዲሁም ጥር 19/1974 በጡረታ ቅጽ ላይ ሚስት ተብለው የተሞላበት ሰነድ ቀርቦአል፡፡ አመልካቹ በበኩላቸው በ1987 ዓ.ም. ከሟች ጋር መጋባታቸው ማስረጃ ቀርቦ ሚስትታቸው በሌላ ተረጋግጧል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ባቀረቡት መቃወሚያ መነሻነት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባደረገው ማጣራት መልስ ሰጪ ለፍርድ ቤቱ በሰጡት ቃል ሟቹና መ/ሰጪ እስከ 1985 አብረው ከኖሩ በኋላ በ1985 ዓ.ም. ተጣልተው መ/ሰጪ ወደ አዲስ አበባ መምጣታቸውን በኋላ ደግሞ ሟቹ አቶ ይልማ አመልካቿን ወ/ሮ ሸዋዬን አግብተው አጋሮ መሄዳቸውን እንደሰሙ በፍርዱ ቤቱ አስረድተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከሟች ጋር የነበረው ጋብቻ በፍቺ አለመፍረሱም ገልፀዋል በቃል በተደረገው ማብራሪያ የአሁን አመልካች ስለፍቺው ያውቁ እንደሆነ ተጠይቀው ሟቹ ከመልስ ሰጪ ጋር ጋብቻ የነበረው መሆኑን ስለማናውቅ ስለፍቺው አናውቅም ብለዋል፡፡

ከዚህ መገንዘብ የቻልነው የአሁንዋ መልስ ሰጪ ምንም እንኳ ከሟቹ ጋር ቀደም ብሎ የተፈፀመ ጋብቻ የነበራቸው ቢሆንም በመካከላቸው በተፈጠረ አለመግባባት ምክንያት በነበረው ጋብቻ መቀጠል አለመቻላቸውንና ሁለቱ በየፊናቸው የየራሳቸው ሕይወት መጀመራቸውን ነው፡፡ የአሁን መልስ ሰጪ ጋብቻው በፍቺ ምክንያት አልፈረሰም ይባል እንጂ ለፍርድ ቤቱ የሰጡት ማረጋገጫ ጋብቻው መፍረሱን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ጋብቻ የሚፈርሰው ሕጉ ባስቀመጣቸው ውሱን ምክንያት መሆኑን ይህም ፍ/ቤት ይቀበለዋል፡፡ በሌላ

በኩል ለጋብቻ መፍረስ ምክንያቶች የሆኑ ነገሮች መኖር አለመኖራቸውን የሚረጋግጠው እንዴት ነው የሚለው ጥያቄና ነጥብ በሁለቱም ተጋቢዎች ከነበረው ሁኔታ ጭምር መረዳት የሚችል ነው፡፡ ጋብቻ የሚፈርስበትን ምክንያት መፍረሱን ከማስረዳት መለየትም ያስፈልጋል፡፡ አሁን በቀረበልን ጉዳይ የመልስ ሰጪ መከራከሪያ ፍቺ መፈፀሙን አመልካች አላስረዳችም የሚል ነው፡፡ ነገር ግን የመልስ ሰጪና የሟች ግንኙነት ማንም ሌላ ማስረጃ ሊያስረዳ ከሚችለው ከሚገልፀው በላይ በመካከላቸው የነበረው የጋብቻ ግንኙነት መፍረሱ ሁለቱም ሌላ ሕይወት ጀምረው ሟቹ የአሁንዋን አመልካች ማግባታቸውን፣ ይህንንም ጋብቻ የአሁኗን መልስ ሰጪ ያውቁ እንደነበር ያስረዳል፡፡ ይህ በመሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ የአሁንዋን መልስ ሰጪ ቀደም ሲል የፈፀመችውን ጋብቻ መሠረት በማድረግ ብቻ ሚስት ናት ብሎ መወሰኑ ትክክለኛ የሕግ አተረጓጎም አይደለም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

- የፌዴራል መጀመሪያት በመ/ቁ 4796 ሚያዝያ 18 ቀን 1997 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
- ወ/ሮ ሣራ ልንጋነ የሟች የአቶ ይልማ ወ/ሃና ሚስት አይደለችም በማለት ወስነናል፣ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡



የሰ/መ/ቁ. 22243

ሚያዝያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ መስፍን እቁበዮናስ

ወ/ሪት ሒሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካቾች፡-** እነ ወ/ሮ ደሐብ ሰኢድ

**ተጠሪ፡-** አቶ አብረሃም ካሣ

*ልጅነትን ስለመካድ - አባትነትን በግምት መወሰን - በማወቅ አባትነት የሚረጋገጥበት መሰረት - የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ቁ/126/1/፣ 143/መ/ና/ሠ/*

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሟች አቶ እንድሪስ አደም የተጠሪው ወላጅ አባት ናቸው ሲል የሰጠውን ውሣኔ በማፅናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራል መጀመሪያና ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ቁ. 143 መሠረት አባትነትን በፍርድ መንገር የሚቻለው አባት ማን ነው የሚለውን ለአባትነት መነሻ የሆኑትን በአንቀጽ 125/1/ መሠረት በህግ ግምት ማወቅ ካልተቻለ ወይም በአንቀጽ 125/2/ መሠረት አባት የተባለው ሰው ልጅነትን ሳይቀበል የቀረበ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡
2. አንድ እናት በህጋዊ ጋብቻ ውስጥ እያለች ልጅ ከተወለደ የልጁ አባት ማን ነው የሚለው ምላሽ የሚያገኘው በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ቁ. አንቀጽ 128/1/ እና ከአንቀጽ 126 — 128 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ህግ ያስቀመጠውን ግምት መነሻ በማድረግ ነው፡፡
3. በህጉ ግምት አባት የተባለው ሰው ህጉ ያስቀመጠውን ግምት ሊያፈርስ የሚችል ክርክር በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ቁ. 167 ሊያቀርበ ይችላል፡፡

የሰ/መ/ቁ. 22243

ሚያዝያ 16 ቀን 1999 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ አሰግድ ጋሻው
አቶ መስፍን እቁበዮናስ
ወ/ሪት ሒሩት መለሠ
አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካቾች፡-** 1. ወ/ሮ ደሐብ ሰኢድ
2. ወ/ሮ ሶፊያ እንድሪስ
3. አቶ ዑመር እንድሪስ
} ወ/ሮ ሦፍያ እንድሪስ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ አብረሃም ካሣ - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን ፍረድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ውሣኔ የተሰጠው በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡

የአሁን አመልካቾች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ከዚህ በፊት ተጠሪው ለዚህ የመጀመሪያ ደረጀ ፍ/ቤት የአቶ እንድሪስ አደም ልጅ ነኝ በማለት ያስወሰነ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ሆኖም አቶ እንድሪስ አደም 1ኛ ተቃዋሚን ወ/ሮ ደሐብ ሲይድን አግብተው የኖሩ ከመሆኑ በስተቀር ሌላ ሚስትም ሆነ ልጅ የላቸውም፡፡ ስለዚህ ውሣኔው ይሻርልን የሚል አቤቱታ አቅርብዋል፡፡

የአሁን ተጠሪም በአመልካቾች በኩል የቀረበው ተቃውሞ ሕጋዊ መሠረት የለውም ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ አቶ አብርሃም ካሣ የአቶ እንድሪስ አደም ልጅ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ጋር አገናዝቦ ከተመለከተ በኋላ ሰኔ 18 ቀን 1996 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ተጠሪ አቶ አብርሃም ካሣ በተወለዱ ጊዜ እናታቸው እና ሟች አቶ እንድሪስ አደም ቀጣይነት ያለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሲፈጽሙ የነበረ በመሆኑና ሟቿም ልጁን /ተጠሪን/ በማሳደግ ሂደት ሲሳተፉ የነበረ ለመሆኑ በተጠሪ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ሲሆን የአመልካቾች ማስረጃ ይህንኑ አላስተባበለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 143/መ/ እና /ሠ/ መሠረት አቶ እንድሪስ አደም የተጠሪው የአብርሃም ካሣ ወላጅ አባት መሆናቸው የተገመተ ስለሆነ በተቃዋሚዎች አማካይነት የቀረበውን የውሣኔ ይሰረዝልን ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡

ይህም ውሣኔ ጉድለት የሌለበት መሆኑን በመግለጽ የፌ/ከፍተኛው ፍ/ቤት በትዕዛዝ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአቤቱታው ፍሬ ቃልም፡-



በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 126/1/ በጋብቻ ውስጥ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባቱ ነው የሚባለው ባልየው ነው ተብሎ የተደነገገውን በመተው በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የነበረው ጋብቻ ሳይፈርስ ከሌላ ጋር ወዳጅነት በመፍጠር ልጅ ወልጃለሁ የሚለውን ተቀብለው የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ መስጠታቸው የሕግ ስህተትን ያስከተለ ነው፡፡ ለዚሁ ሕግ አንቀጽ 143/መ/ እና /ሠ/ መሠረት ፍ/ቤት አባትነትን በግምት ሊወስን የሚቻለው ከዚሁ ድንጋጌ ከፍ ብለው በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የልጅ አባት ያልታወቀ ወይም የተካዳ ሲሆን ብቻ መሆኑ እየታወቀ ይህ ሁሉ ታልፎ የተሰጠው ውሣኔ የቤተሰብን ሕግ የተከተለ አይደለም የሚል ነው፡፡

ተጠሪም በበኩሉ የተጠሪ እናት ባል ነበራቸው በሚል በአመልካቾች በኩል የቀረበ ክርክር የለም፤ በተጠሪ እናት እና በአቶ ካሣ መካከል ጋብቻ ነበረ እንኳ ቢባል ለረጅም ጊዜ ተለያይተው መተማመንና መረዳዳት በጠፋበት ሁኔታ ትዳር/ጋብቻ አለ ማለት አይቻልም፡፡ ትዳር አለ የሚለውን መነሻ በማድረግ የሕግ ግምት የሚወሰድ ከሆነ የተፈጥሮ አባትነት የሚያሰጥ ነው፡፡ ስለሆነም ትዳር አለ ቢባል እንኳን የተለያዩት ለረዥም ዓመት በመሆኑ ግላዊ ግንኙነቱ የጠፋ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የቤተሰብ ሕጉን ዓላማ በተቃረነ መልኩ ሕጉ መተርጎም ይገባዋል የሚለው ክርክር ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካለው ሕግ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በዚህ ጉዳይ አከራካሪው ነጥብ ተጠሪ የሟች የአቶ እንድሪስ አደም ልጅ መሆኑን ስለአባትነት ማወቅ /Ascertainment of paternity/ ሕጉ በደነገገው መሠረት አስረድቷል ወይስ አላስረዳም? የሚለው ነው፡፡

ይህንን ጭብጥ አስመልክቶ የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ መሠረት ያደረገው በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 በአንቀጽ 125/3/ አና 143 /መ/ እና /ሠ/ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች እንደሆነ ከመዝገቡ ግልባጭ ተረድተናል፡፡

ሆኖም በዚሁ ሕግ በአንቀጽ 143 መሠረት አባትነትን በፍርድ መንገር የሚቻለው አባት ማነው? የሚለውን በሚመለከት ለአባትነት ማወቅ መነሻ የሆኑትን በአንቀጽ 125/1/ መሠረት በሕግ ግምት አባትነትን ማወቅ ካልተቻለ ወይም በአንቀጽ 125/2/ መሠረት አባት የተባለው ሰው ልጅነት ሳይቀበል የቀረበ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የልጁ አባት ያልታወቀ እንደሆነ ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሟሉ አባትነት በፍርዱ ውሣኔ ሊታወቅ ይችላል በሚል በአንቀጽ 143 ተደንግጓል፡፡ ከአንቀጽ 143 በላይ ያሉት ድንጋጌዎች ደግሞ በሕግ ግምት ወይም በማወቅ /Acknowledgment/ መሠረት አባትነት የሚረጋገጥበትን መንገድ የሚዘረዝሩ

ናቸው። ይህም የሚያሳየው በአንቀጽ 125/1/ አባትነት በሕግ ግምት ሊታወቅ ከቻለ ወይም 125/2/ መሠረት በማወቅ ከተረጋገጠ ይህንን አልፎ አባትነትን በፍርድ መንገር /Ascertainment of [paternity by Judicial Declaration/ የማይቻል መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው።

አሁን በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የተፀነሰው ወይም የተወለደው የተጠሪ እናት ከሌላ ሰው ጋር በሕግ ፀንቶ በቆየ ጋብቻ ተሳስራ በነበረበት ጊዜ የነበረ ስለመሆኑ እራሳቸው የተጠሪ የሰው ማስረጃዎች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው። ይህንን በማስመልከት የሰጡትን አግባብነት ያለውን ቃል ለመጥቀስ ያሕልም የተጠሪ እናት ከ1960 ዓ.ም. ጀምሮ ባል አግብተው ይኖሩ ነበረ። ባልየው በሥራ ምክንያት ወደ ክ/ሀገር በሄደበት ጊዜ ከሟች ከእንዱሪስ አደም ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፍጠራቸውን እናውቃለን። በዚህም ግንኙነት ሳቢያ ተጠሪ በ1972 ዓ.ም. ተወለደ። በ1975 ዓ.ም. የተጠሪ እናት ባል ከሄደበት የሥራ ቦታ ተመልሰው ከተጠሪ እናት ጋር መኖር ቀጠሉ። ድሮውንም ቢሆን አልተፋቱም ነበር። ተጠሪም የሚጠራው በዚሁ ሰው በባልየው ስም ነው የሚለው ይገኝበታል።

እነዚህ ፍሬ ነገሮች እስከተረጋገጡ ድረስ የተጠሪ አባት ማን የሚለውን ጥያቄ ምላሽ የሚያገኘው በአዋጅ ቁጥር 213/92 በአንቀጽ 128/1/ እና ከአንቀጽ 126-128 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ሕግ ያስቀመጠውን ግምት መነሻ በማድረግ ይሆናል። በዚህም መሠረት የተጠሪ አባት የተጠሪን እናት አግብተው የነበሩት የተጠሪ እናት ባል እንጂ ሟች አቶ እንድሪስ አደም ሊሆኑ አይችሉም።

በሕጉ ግምት አባት የተባለው ሰው በበኩሉ ሕግ ያስቀመጠውን ግምት ሊያፈርስ የሚችል ክርክር በማቅረብ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 167 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ልጁን የካዱ መሆኑን መነሻ በማድረግ የቀረበ ክርክርም አልተገኘም።

በዚህ ሁሉ ምክንያት የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት በግራ ቀኙ ክርክር አግባብነት የሌላቸውን በአንቀጽ 143/መ/ እና /ሠ/ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ውሣኔ መስጠቱ የሕግ ስህተት መፈፀሙን አረጋግጠናል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 3753 በ18/10/96 የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 33498 በ25/01/98 የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ ተሽሯል።
2. ሟች እንድሪስ አደም የተጠሪ የአብርሃም ለማ አባት መሆናቸው አልተረጋገም በማለት ወስነናል።

ይህ የሰበር ክርክር ላስከተለው ኪሣራና ወጭ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል። መዝገቡ ተዘግቷል።



**የሰበር መ/ቁ. 17058**

**መጋቢት 25/1999**

**ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ**

**" ፍስሐ ወርቅነህ**

**" አብዱልቃድር መሐመድ**

**" መስፍን ዕቁበዮናስ**

**" ተሻገር ገ/ሥላሴ**

**አመልካች፡- አቶ አንበሶ ወ/ገብርኤል**

**መልስ ሰጭ፡- አቶ መሣይ መኰንን**

*ውርስ - ኑዛዜ - የኑዛዜ መፅደቅ የሚያስከትለው ውጤት - የወራሽነት የምስክር ወረቀት ውሣኔ ስላለመሆኑ - የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 881፣ 884፣ 892፣ 996 — 1000፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.5*

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወራሽነት ምስክር ወረቀት መስጠት በአንድ የውርስ ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ እንደተሰጠ አያስቆጥርም በሚል የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ እንዲወስን በመወሰኑ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው።

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል።

1. የትኛውም የኑዛዜ አይነት በህግ ፊት የፀና እንዲሆን ፍርድ ቤት መጽደቅ አያስፈልገውም።
2. ኑዛዜ ህጋዊ ነው መባሉ ሌሎች ሰዎች በሰነዱ ላይ ተቃውሞ ካላቸው ጉዳዩ በዳኝነት መታየትን የሚከለክል አይደለም።
3. በመሠረቱ ፍርድ ቤቶች ኑዛዜ ይጽደቅልኝ በማለት የሚቀርብላቸውን ጥያቄ የሚያስተናግዱበት ምክንያት መኖር የለበትም።
4. ፍርድ ቤቶች የወራሽነት ምስክር ወረቀት የሚሰጡት ጥያቄ ያቀረበው ወገን አለኝ የሚለውን ማስረጃ እንዲያቀርብ ካደረጉ በኋላ እንጂ በጉዳዩ ላይ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ህግ በሚያዘው መሠረት ከሌሎች ሰዎች ጋር ሙግት እንዲገጥም በማድረግ አይደለም።

የሰበር መ/ቁ. 17058

መጋቢት 25/1999

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

" ፍስሐ ወርቅነህ

" አብዱልቃድር መሐመድ

" መስፍን ዕቁበዮናስ

" ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- አቶ አንበሶ ወ/ገብርኤል ጠበቃ የሸጥላ አሰፋ ቀረበ

መልስ ሰጭ፡- አቶ መሣይ መኩንን - ጠበቃ በየነ ገብሬ ጋር ቀረበ፡፡

በዚህ መዝገብ የቀረበልንን ጉዳይ መርምረን ቀጥሎ ያለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ሙግት የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች አተረጓገምና አፈፃፀምን የሚመለከት ነው፡፡ ለክርክሩ መንስኤ የሆነውን ክስ የመሠረተው የአሁን መልስ ሰጪ ሲሆኑ የክሱ ፍሬ ሀሣብ የአባቴ ብቸኛ ወራሽ እኔ በመሆኔ የአሁን አመልካች የአባቴን ንብረት በእጁ ይዞ ስለሚገኝ እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ የአሁን አመልካች ለክሱ ባቀረበው መልስ የመልስ ሰጪ አባት ኑዛዜ መተዋቸውን፣ በዚሁ ኑዛዜ ለአሁኑ መልስ ሰጪ የተሰጠው ብር ሃያ ሺህ (20,000) ብቻ መሆኑን፣ ይኸው ኑዛዜ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት በቦረና ዞን በአዳላ ፍ/ቤት የፀደቀ መሆኑን መልስ ሰጪ በዚሁ ሂደት ተቃዋሚ ሆኖ አለመቅረቡ በመግለፅ መልስ አቀረበ፡፡

ጉዳዩን የያዘው ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ኑዛዜው በአዶላ ወረዳ ፍ/ቤት የፀደቀ መሆኑ ስለተረጋገጠ - ከሣሽ የሚያቀርበው ጥያቄ ካለ መቅረብ የነበረበት ኑዛዜውን ባፀደቀው ፍ/ቤት ነው፣ በማለት ከሣሽ ማግኘት የሚችለው በኑዛዜው እንዲያገኝ የተወሰነበትን ብር 20,000 (ሃያ ሺህ ብር) በቻ ነው ሲል ወሰነ፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤት እዚህ መደምደሚያ ላይ ሊደርስ የቻለው ኑዛዜው በፍርድ ቤት መጽደቁና በሌላ ውሣኔ አለመሻሩን ምክንያት በማድረግ ነው፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር የተሰኘው የአሁን መልስ ሰጪ ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በማቅረቡ አመልካች መልስ እንዲሰጥበት ከተደረገበት በኋለው ሣኔው በጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ተሽሯል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የከፍተኛውን ውሣኔ የሻረው የአሁን መልስ ሰጪ ለአዶላ ወረዳ ፍ/ቤት ያቀረበውን ጥያቄ መሠረት በማድረግ የወራሽነት የምስክር ወረቀት መስጠቱ በጉዳዩ ላይ ውሣኔ እንደሰጠ የሚያስቆጥረው አይደለም፣ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንደማንኛውም ሌላ ማስረጃ የሚታይ እንጂ በኑዛዜው ላይ ሌላ ክርክር እንዳይደረግ የሚከለክል አይደለም የሚሉና ሌሎችም ተጓዳኝ ምክንያቶች በመስጠት ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ የወራሽነት የምስክር ወረቀት መገኘት ሌላ የውርስ ሀብት ይገባኛል የሚል ሰው ጥያቄ ሊያስቀር አይገባውም በማለት የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሮ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክር መርምሮ የመሰለውን ውሣኔ ይስጥ በማለት ጉዳዩን ወደ ከፍተኛ ፍ/ቤት መለሰው፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ 1ኛ ተጠሪ በኑዛዜ ወራሽ ሆኖ እያለ የጠቅላይ ፍ/ቤት ያለኑዛዜ ወራሽ እንደሆነ አድርጐ የውርስ ሀብት የመጠየቅ መብት አለው - ያለው ያለአግባብ ነው፡፡ 2ኛ ተጠሪ ኑዛዜ ሲፈስ የነበሩ በመሆናቸው እንደሕጉ በኑዛዜው ላይ ያላቸውን ተቃውሞ በ15 ቀን ውስጥ ያላሰሙ በመሆናቸው ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ከተሰጠው የመቃወሚያ ጊዜ ውጪ የቀረበው አቤቱታ መቀበሉ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

መልስ ሰጪ በቀረበው የሰበር አቤቱታ ላይ የጽሑፍ መልስ አቅርቧል፡፡ ዋናውና መከራከሪያዎቹ፣

1. የሰበር አቤቱታው የመጨረሻ ውሣኔ ባላረፈበት ጉዳይ የቀረበ በመሆኑ ለሰበር ሊቀርብ አይገባውም፣
2. ጉዳዩ ለከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲመለስ በመወሰኑ በሁለቱ ፍ/ቤቶች እንዲቀጥል መደረጉ አግባብ አይደለም፡፡
3. ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ጉዳዩ እንደገና ታይቶ እንዲወሰን ወደ ከፍተኛ ፍ/ቤት መመለሱ አግባብ ነው፡፡

የሚሉ ናቸው፡፡ አመልካቹ የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ ጉዳዩ የያዘው ይህ የሰበር ችሎት በዚህ መዝገብ የቀረበውን ጉዳይ ተመልክቷል ለክርክሩ አወሳሰን ቀጥሎ የተመለከቱትን ጥያቄዎች መመለስ ተገቢ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

(1) የኑዛዜ መጽደቅ የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት ምንድ ነው?

(2) የወራሽነት የምስክር ወረቀት ውሣኔ ፍርድ ነው ወይስ አይደለም?

የከፍተኛው ፍ/ቤት በግራ ቀኙ የተነሱትን በርካታ ክርክሮች አልተመለከተም ለዚህ ምክንያት የሆነው የቀረቡት ክርክሮች መታየት ያለባቸው ኑዛዜውን ባፀደቀው በአዶላ ወረዳ ፍ/ቤት በሚገኘው መዝገብ ነው በማለት ነው፡፡ ይህ የፍርድ ቤቱ አካሄድ የኑዛዜ መጽደቅ ትርጉም ምንድነው የሚለው ጥያቄ እንዲነሣ ስለሚያደርግ ይህን መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡

በመሠረቱ ኑዛዜ አንድ ሰው ሊፈጽማቸው ከሚችሉ ሕጋውያን ተግባራት (Juridical acts) መካከል አንዱ ነው ማንም ሰው በሕይወቱ እያለ ከህልፈቱ በኋላ ንብረቱንም ሆነ ሌሎች ሕግ በኑዛዜ እንዲከናወኑ የሚፈቅዳቸውን ተግባራት በማስመልከት ፍላጐቱንና ፈቃዱን የሚገልፅበት ሕጋዊ ሰነዱ ነው፡፡ ኑዛዜ በሕግ ፊት የፀና የሚሆነው ሕጉ ያሰፈራቸውን መለኪያዎች አሟልቶ ሲገኝ ነው፡፡ ኑዛዜ የሚሰጥበት ሥርዓት እንደኑዛዜው ዓይነት የተለያየ ቢሆንም የትኛውም የኑዛዜ ዓይነት በሕግ ፊት የፀና እንዲሆን በፍርድ ቤት መጽደቅ አያስፈልገውም፡፡ ግልጽ ኑዛዜ በሕግ ፊት የፀና እንዲሆን መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች በሕጉ አንቀፅ 881 ተቀምጠዋል፣ ከነዚህ መካከል በፍርድ ቤት ቀርቦ መጽደቅ የሚል መለኪያ አይገኝበትም፡፡ በመሆኑም ግልጽ ኑዛዜ በተጠቀሰው አንቀጽ ያሉትን መስፈርቶች እስከአሟላ ድረስ በፍርድ ቤት ተጨማሪ ቡራኬና ውሣኔ ሣያስፈልገው በሕግ ተፈፃሚነትና ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ በተናዛዡ የእጅ ጽሑፍ የሚደረግ ኑዛዜ (አንቀጽ 884) በማስመልከት ካሉት ድንጋጌዎች መመልከት የሚቻለውም ለፍርድ ቤት ቀርቦ ውሣኔ መሰጠት ከኑዛዜው ተቀባይነት ጋር ተያያዥነት ያለው ጉዳይ አለመሆኑ ነው፡፡ በተናዛዡ የእጅ ጽሑፍ የሚደረግ ኑዛዜ በ7 ዓመት ውስጥ ፍርድ ቤቱ ወይም አዋዋይ ዘንድ መቀመጥ ካልተቀመጡ ፈራሽ ነው የሚለውም ቢሆን ከኑዛዜ ውድቅ መሆን (Lapse of wills) ጋር የተያያዘ ነው፡፡ መከናወንም ያለበት ተናዛዥ በሕይወት እያለ ነው፡፡ የቃል ኑዛዜውም የተለየ አይደለም አንቀጽ 892 በመሆኑም የትኛውም የኑዛዜ ዓይነት ቢሆን በሕግ የፀና እንዲሆንና ተፈፃሚነት እንዲኖረው በየትኛውም ፍርድ ቤት ቀርቦ መጽደቅ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ኑዛዜ ሕግ ያስቀመጣቸውን ሌሎች መስፈርቶች እስከአሟላ ድረስ በፍርድ ቤት መጽናት አለመጽናቱ የሚጨምርለትም የሚቀንስበትም ጉዳይ የለም፡፡ ውሎች የፍርድ ቤት ውሣኔ ሣያስፈልጋው በተዋዋዬች መካከል ሕግ የመሆናቸውን ያህል ኑዛዜም ሕጉ ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች እስካሟላ ድረስ በፍርድ ቤት መጽደቅ ሣያስፈልገው ተናዛዡ ከሞተበት ቀን አንስቶ ሕጋዊ አስገዳጅነት ያለው ነው፡፡ ኑዛዜው ሕጋዊ ነው መባሉ ሌሎች ሰዎች በሰነዱ ላይ ተቃውሞ ካላቸው ጉዳዩ በዳኝነት መታየትን የሚከለክል አይደለም ሆኖም የዚህ ዓይነት ጉዳይ የሚታየው ኑዛዜው ተቀባይነት የለውም የሚል ወገን ሲቀርብ እንጂ ባለጉዳዩ በሌለበት አንድ ሰው ኑዛዜውን አፀደቅኩ በሚለው የተናጠል ሂደት አይደለም፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቶች በመሠረቱ ኑዛዜ ይጽደቅልኝ በማለት የሚቀርብላቸውን ጥያቄ የሚያስተናግዱበት ምክንያት መኖር የለበትም፡፡ በሕግ ኃይል ያለተጨማሪ መዳኘት የፀናውን ሰነድ አጽንቻለሁ ብሎ «ውሣኔ» መስጠት ትርጉም የማይሰጥ አላስፈላጊ ሂደት ነው፡፡ ይህ ሂደት አላስፈላጊ ከመሆኑም ባሻገር የሌሎችን መብት ሊጉዳ በሚችል መንገድም ሥራ ላይ ሊውል አይገባውም፡፡ በኑዛዜው ላይ ጥያቄ ያለው ወገን የኑዛዜ ተጠቃሚ ነኝ የሚለውን ወገን የሕጉን ሥርዓት በመከተል ሊሞግተው ይችላል፡፡ ኑዛዜ የማፀደቅ አላስፈላጊ ሂደት ይህን መሠረታዊ መብት የሚንድ መሆን አይገባውም፡፡ የኑዛዜ ይጽደቅልኝ ጥያቄ የሚቀርበው ተለይተው በታወቁ መልስ ሰጪዎች ላይ አይደለም፡፡ "ፍርድም" ሆነ "ውሣኔ" የሚሰጠውም በማንም ተለይቶ በሚታወቅ ሰው ላይ አይደለም፡፡ በመሆኑም የከፍተኛው ፍርድ ቤት እንዳተተው የኑዛዜው ይጽደቅልኝ አቤቱታ በማስመልከት በጋዜጣ ጥሪ እንኳን ተደርጉ ቢሆን ኑዛዜው የማንን መብት እንደሚነካ ቀድሞ ስለማይታወቅ ማንኛውም ሰው የጋዜጣው ጥሪ መሠረት በማድረግ አልተከራከርክም ተብሎ ኑዛዜውን አስመልክቶ ሌላ ጥያቄ ከማንሣት ሊከለከል አይገባውም፡፡ በሥነ ሥርዓት ሕጉም ቢሆን አንድ ሰው ድጋሚ ክስ ከማንሣት የሚከለክለው በአንቀፅ 5 መሠረት ተሟጋቾቹ ቀድመው



የተከራከሩበትና የተሣተፉበት ወይም እንደተከራከሩበት የሚያስቆጥራቸው ሂደት ከነበረ ነው ከላይ እንደተመለከተው የኑዛዜ ይጽናልኝ ጥያቄ በመሠረቱ ለአመልካቹ ምንም ተጨማሪ መፍትሄ (relief) የማይሰጥ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ሊያስተናግዱት የማይገባ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ ወይም ሌላ ምክንያት "የማፅናት ውሣኔ" ተሰጥቷል፡፡ ቢባል እንኳ በክርክሩ ያልነበሩ ሰዎችን በሥነ ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 5 መሠረት ሌላ ክስ እንዳያቀርቡ ሊያግዳቸው አይገባም፡፡ በኑዛዜ ይጽደቅልኝ ክሱ ተከራካሪ ስላልነበሩ (named defendants) የተሰጠውን ውሣኔ በይግባኝ እንዲያሽሩም አይጠበቅባቸውም፡፡

ቀጥሎ የምንመለከተው የወራሽነት የምስክር ወረቀት ያለውን ሕጋዊ ውጤት ነው፡፡ የወራሽነት የምስክር ወረቀት የፍትሐብሔር ሕጉን የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች በመከተል የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው (አንቀጽ 996- 1002) አንቀጽ 996(1) "ወራሽ የሆነው ሰው ለሟቹ ወራሽ መሆኑና ከውርሱ ላይ የሚያገኘውን ድርሻ የያመለከት የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጡት ዳኞችን ለመጠየቅ ይችላል" በማለት ይደነግጋል፡፡ 997(1) ደግሞ "የምስክር ወረቀቱ እስከተሰረከዘ ድረስ ወራሹ በተባለው የምስክር ወረቀት እንደተገለጠው ወራሽ እንደሆነ ይገመታል" በማለት ይደነግጋል፡፡ ከነዚህ ድንጋጌዎች ለመገንዘብ የሚቻለው የወራሽነት የምስክር ወረቀት አንድ ሰው ወራሽ ሆኖ የመገመትን ሁኔታ እንዲፈጠርለት የሚያደርግ ነው፡፡ ከሰሙም በግልጽ እንደሚታየው ይህ ሰነድ አንድ ሰው በሰነዱ በተጠቀሰው መጠን ወራሽነቱን የሚያስረዳ ሰርቲፊኬት ነው፡፡ ይህን ሰርቲፊኬት ለማግኘት የፍርድ ቤት ትእዛዝ የሚሻ ቢሆንም መጨረሻ ላይ የሚሰጠው ሰነድ ግን አንድን ሁኔታ የሚያስረዳ ማስረጃ ነው፡፡ ከአንቀፅ 996 (2) ለመገንዘብ እንደሚቻለውም ይህ ሰርቲፊኬት የሚሰጠው ጥያቄ ያቀረበው ወገን አለኝ የሚለውን ማስረጃ እንዲያቀርብ ካደረጉ በኋላ እንጂ በጉዳዩ ላይ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ በሚያዘው መሠረት ከሌሎች ሰዎች ጋር ሙግት እንዲገጥም በማድረግ አይደለም፡፡ የውርስ ሰርቲፊኬት አንድ ሰው የራሱ ወራሽነት ለማስረዳት የሚወስደው ማስረጃ እንጂ ሌሎች ወራሾች አለመኖራቸውን የሚያሣይ ሰነድ አይደለም ኑዛዜ በሚኖርበት ጊዜ በተለይ በኑዛዜው የተጠቀሰው በርካታ ተጠቃሚዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ የሰርቲፊኬቱ ሁኔታም ከዚህ አንፃር መመርመር ይኖርበታል፡፡ ኑዛዜው ጠቅላላ ኑዛዜ ወይም ልዩ ኑዛዜ ሊሆን ይችላል፡፡ ኑዛዜው ጠቅላላ ኑዛዜ ከሆነ የውርሱ ሰርቲፊኬት መኖር ብቻውን ሁሉንም ንብረት ጠቅልሎ እንዲወስድ የሚያደርገው ሊሆን አይችልም፡፡ የውርስ ሰርቲፊኬት ኖረም አልኖረም የጠቅላላ ኑዛዜ ውጤት የሚታየው አግባብነት ካላቸው የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች አንፃር ነው፡፡ ለሰርቲፊኬቱ መነሻ በሆነው ኑዛዜ ላይ የተጠቀሱ ሌሎች ሰዎች ያሉ እንደሆነም የሰርቲፊኬቱ መሰጠት እነሱን የሚነካ ሊሆን አይችልም፡፡ በውርሱ ተነቀለ የተባሉ ሰው ካለ ሌላ ስጦታ የተሰጠው ሰው ካለ ወይም በኑዛዜው ውስጥ በሌላ ጉዳይ ላይ የተሰጠ ሌላ ትእዛዝ ካለ ለአንዱ ሰው

የተሰጠው የኑዛዜ ሰርቲፊኬት እነዚህ ሌሎች ሰዎች ኑዛዜውን አስመልክቶ ጥያቄ እንዳያነሱ ሊያደርጋቸው አይችልም፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ኑዛዜ በአንድ ሰው ጠያቂነት ፀና ቢባልም ይኸው የመጽናት ጥያቄ ሌሎች በኑዛዜው ጥቅም የሚያገኙ ወይም በኑዛዜው ጥቅማቸው የተነካ ሰዎች በዚህ ኑዛዜ ላይ ያላቸውን ክርክር ሊያቀርቡ ሊፈቀድላቸው ይገባል፡፡ በአጠቃላይ አነጋገር የወራሽነት ሰርቲፊኬት በሰርቲፊኬቱ ላይ የተገለፀውን ፍሬ ነገር በሚመለከት የወራሽነት ግምት የሚፈጥር ማስረጃ ከመሆን አልፎ እንደሌሎች በፍርድ ቤት እንደሚሰጡ ፍርዶች ሊወሰዱ አይገባውም፡፡ የወራሽነት ሰርቲፊኬት እስካልተሰረዘ ድረስ የወራሽነት ግምት እንደሚፈጥር ሰርቲፊኬቱ መሰረዝ የሚችለው በፍ/ቤት መሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 998 ተደንግጓል፡፡ ሆኖም የወራሽነት የምስክርነት ወረቀት ለማሰረዝ የሚደረግ ጥያቄ ኑዛዜውን በመቃወም ከሚቀርብ ጥያቄ ጋር አንድ ተደርጐ ሊወሰድ አይገባውም፡፡ ኑዛዜ መቃወም የግድ የወራሽነት ሰርቲፊኬት መሠረዝ አያስከትልም፡፡ የወራሽነት ምስክር ወረቀት መሰረዝ የሚያስከትልም ቢሆን ኑዛዜውን በሌላ ምክንያት መቃወም የሚፈልግ ሰው የግድ የወራሽነት ሰርቲፊኬት በሰጠው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ መገደዱ አግባብ አይደለም፡፡

ለማጠቃለል ለጠቅላይ ፍ/ቤት የኑዛዜ መጽናቱን በማስመልከት የሚቀርቡ ክሶች የሕግ መሠረት የሌላቸው መሆኑን የውርስ ሰርቲፊኬት ማስረጃ መሆኑን በማተት የከፍተኛውን ፍርድ ውሣኔ መሻሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መሥራቱን የሚያመለክት አይደለም፡፡ ይልቁንም ከፍተኛው ፍርድቤት የቀረበለትን ኑዛዜ በማስመልከት በርካታ ክርክሮች ቀርበውለት እያለ ኑዛዜው በሌላ ፍርድ ቤት የፀና ስለሆነ ክርክሮቹን ለማየት አልችልም ማለቱ አግባብ አልነበረም፡፡ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የቀረበው ኑዛዜ የሟቹ አይደለም፣ ኑዛዜው አፀደቀ የተባለው ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን አልነበረውም፣ በኑዛዜው የተጠቀሰው ምክንያት ከውርስ ለመነቀል የሚያበቃ አይደለም፣ ኑዛዜ ነው የተባለው ሰነድ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881ን የሚያሟላ አይደለም የሚሉ ክርክሮች ቢቀርቡበትም እነዚህ ነጥቦች መነሣት ይችሉ የነበረው ኑዛዜውን ባፀናው ፍ/ቤት ቀርበው ቢሆን ነበረ በማለት አልፎላቸዋል፡፡ ከላይ በተገለፀው ምክንያት ይህ የፍርድ ቤቱ አካሄድ ትክክል አይደለም፡፡ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በነዚህና በሌሎች በሥር ተከሣሽ በሚነሱ ነጥቦች ላይ የመሰለውን እንዲወስን መዝገቡን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ቁጥር 341(1) መሠረት መመለሱ አግባብ ነው፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

(1) ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰኔ 17 ቀን 1996 በፍ/ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 13988 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

(2) ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ያየራሣቸውን ይቻሉ፡፡፡



የሰ/መ/ቁ. 22712

ሚያዚያ 9 ቀን 1999 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
አቶ አሰግድ ጋሻው
ወ/ት ሂሩት መለሠ

**አመልካች፡-** አቶ እንዳሻው በቀለ

**ተጠሪ፡-** እነ ወ/ት አይናለም ያለው

*ውርስ - ኑዛዜ - የኑዛዜ አፃፃፍ ስርአት - የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 881፣*

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ሟች አቶ በቀለ ወልዴ የሰጡት ኑዛዜ ከተፃፈ በኋላ መነበቡን ስለማይገልጽ ፈራሽ ነው ብሎ የሰጠውን ውሣኔ በማፅናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. የኑዛዜ ስነ ስርአት ጥብቅ መሆን ዋና አላማ ኑዛዜ የሟች ፍላጐት በትክክል የሚገልጽ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡
2. ሰነዶች ፎርማሊቲውን ያሟሉ እንደሆነ መመርመር የሚገባቸው ከዚህ አላማ አንፃር ነው፡፡
3. የኑዛዜ እያንዳንዱ መስፈርት መሟላት መመዘን የሚገባው የኑዛዜውን አጠቃላይ ሁኔታ በመመልከትና ተናዛዡም ሆነ ምስክሮች /እማኞች/ በኑዛዜው ባሰፈሩት ቃላትና ሃረጎች ሊሰጡ የሚችለውን ትርጉም ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

የሰ/መ/ቁ. 22712

ሚያዚያ 9 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሠ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን ዕቁበዮናስ

አሰግድ ጋሻው

ሂሩት መለሠ

**አመልካች፡-** አቶ እንዳሻው በቀለ - ጠበቃ አሰፋ ዝቅአርጋቸው ቀረቡ፡፡

**መልስ ሰጭ፡-** 1. ወ/ት አይናለም ያለው - አልቀረበችም፡፡

2. ወ/ት የሺሀረግ ሺመልስ - ቀርባለች

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበልን ጉዳይ የኑዛዜ አፃፃፍ ሥርዓትን የሚመለከት ነው፡፡ ለዚሁ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሟች አቶ በቀለ ወልዴ የሰጡት ኑዛዜ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 በሚያዘው መሠረት ኑዛዜው ከተፃፈ በኋላ መነበቡን ስለማይገልፅ ኑዛዜው ፈራሽ ብሎ በመወሰኑ ነው፡፡ ኑዛዜው ፈራሽ መሆን አለበት የሚለውን ጥያቄ ያቀረቡት የአሁን መልስ ሰጪዎች ናቸው፡፡ ተቃውሞውን ያቀረቡት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ቢሆንም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡትን የኑዛዜ ይፍረስልን ተቃውሞ አልተቀበለውም ነበር፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም የቀረበለትን ይግባኝ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የቀረበው የሰበር አቤቱታ ኑዛዜው የህጉን መስፈርት የሚያሟላ በመሆኑ ይፍረስ መባሉ ትክክል አይደለም የሚል ነው፡፡ መልስ ሰጪዎች በቃል ክርክር የሰጡት መልስ ደግሞ ኑዛዜው ሕጉ የሚጠይቀውን መስፈርት እስካላሟላ ድረስ ፈራሽ ነው መባሉ አግባብ ነው የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎት አከራካሪ የሆነውን ኑዛዜ አቅርቦ ተመልክቷል፡፡ ኑዛዜው በህጉ መሠረት በአራት ምስክሮች የተፈረመ ነው፡፡ ትናዛዡ ፈርመውበታል፡፡ ይኸው ፊርማ በእርግጥ የተናዛዡ መሆኑም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በፖሊስ የቴክኒከ ምርመራ ተረጋግጧል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የኑዛዜው የመጨረሻው ክፍል "እኛም ከዚህ በላይ ስማችን የተጠቀሰው እማኞች ይህንን ኑዛዜ አቶ በቀለ ወልዴ በህይወትና በንፁህ አዕምሮ እያሉ እና በተስተካከለ የጤና አቋም ላይ እያሉ ሲናዘዙ ሰምተናል" ይላል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ "እኔም ከዚህ በላይ የተገለፀውን የኑዛዜውን ቃል ተፈጻሚ ይሆን ዘንድ በተለመደው ፊርማዬ አረጋግጣለሁ" የሚል ዐረፍተ ነገርና ፊርማ ይገኝበታል፡፡



የፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 881 ኑዛዜው በተናዛዡና በአራት ምስክሮች ፊት ካልተነበበ ዋጋ እንደማይኖረው ይደነግጋል፡፡ ይህ ሥርዓት መፈፀሙ በኑዛዜው ላይ መገለጽ እንዳለበትም ይደነግጋል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ኑዛዜው ውድቅ ያደረገው ኑዛዜው ምስክሮች ሟቹ ቃላቸውን ሲሰጡ መስማታቸውን ቢገልጽም ኑዛዜው ከተፃፈ በኋላ መነበቡን የሚገልጽ ነገር የለውም በማለት ነው፡፡ ሆኖም ከላይ ከተጠቀሰው የኑዛዜው ክፍል መገንዘብ እንደሚቻለው ምስክሮቹ ሟቹ ሲናዘዝ መስማታቸውን ይገልፃል፡፡ ይህ የኑዛዜው አገላለጽ ሟቹ ሲናገሩ መስማታቸውን ብቻ ሳይሆን የኑዛዜው ይዘት ከንግግሩ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ማረጋገጣቸው እንደሚገልጽ ሆኖ መወሰድ ይኖርበታል፡፡ የኑዛዜው ሂደት ተከታትለው የሟች ንግግር /ቃል/ ከኑዛዜው ይዘት ጋር ለማመሳከር እድል የነበራቸው እንደሆነ በመገመት "ሲናዘዙ ሰምተናል" የሚለው ቃል ኑዛዜው ሲፃፍ የነበረውን ሂደት በአጠቃላይ በሚገልጽ ሁኔታ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የከፍተኛው ፍ/ቤት ከተፃፈ በኋላ ኑዛዜው መነበቡን አይገልጽም የሚለው መደምደምያ ከኑዛዜው ይዘት ጋር የሚጣጣም አይደለም፡፡ ኑዛዜ ጥብቅ የሆነ ሥርዓት እንዲከተል የሚፈለግ መሆኑ ከፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 881 መገንዘብ የሚቻል ቢሆንም የእያንዳንዱ መስፈርት መሟላት መመዘን የሚገባው ግን የኑዛዜውን አጠቃላይ ሁኔታ በመመልከትም ጭምርና ተናዛዥም ሆነ ምስክሮች /እማኞች/ በኑዛዜው ባሰፈሩት ቃላትና ሀረጎች ሊሰጡ የሚችለውንም ትርጉም ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ የኑዛዜ ሥነ ሥርዓት ጥብቅ መሆን ዋና አላማ ኑዛዜ የሟች ፍላጐት በትክክል የሚገልጽ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ሰነዶች ፎርማሊቲው ያሟሉ እንደሆነ መመርመር የሚገባቸውም ከዚሁ አንፃር ነው፡፡ አሁን በያዝነው ጉዳይ ምስክሮች ኑዛዜው ሟቹ በትክክለኛ አእምሮ እያሉ ሲሰጡ መስማታቸውን ገልፀዋል፡፡ የኑዛዜ መሰጠት ሥርዓት ተናዛዥ ሲናገር ማድመጥ ብቻ ሳይሆን የተባለውን ሁሉ በጽሁፍ ማስፈርን የሚያጠቃልል ነው፡፡ በመሆኑም ይኸው አገላለጽ ምስክሮች ኑዛዜው ሲነበብ መስማታቸውን ለመግለጽ ጭምር እንደተጠቀሙበት መገንዘብ የተሻለ የኑዛዜው አተረጓጐም ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 13751 ጥቅምት 18 ቀን 1998 እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22174 ታህሣሥ 26 ቀን 1998 የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 373/93 በ4/11/94 የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡

የሰ/መ/ቁ. 22162

ሚያዝያ 09 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች:- አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች ፡- አፍሪካ ኢንሹራንስ**

**ተጠሪ ፡- አቶ ብስራት ጉላ**

*የኢንሹራንስ ክርክር - የኢንሹራንስ ውል - ከውል ውጪ ኃላፊነት*

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የኦሮሚያ ም/ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ቀረብኝ የሚለውን የተጣራ ገቢ በቀን ብር 250 በድምሩ ብር 28000 እንዲከፈለው የሰጠውን ውሣኔ በማፅናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

<u>ውሣኔ፡ -</u> የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ም/ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. የኢንሹራንስ ሽፋን ያለው ተከሣሽ በሶስተኛ ወገን ላይ ጉዳት ባደረሰ ጊዜ ፍርድ ቤቶች የተከራካሪዎችን መብትና ግዴታ ለመወሰን ውልንና ከውል ውጪ ያሉ ሕጐችን ተፈፃሚ ማድረግ ይችላሉ፡፡
2. በመድን ሰጪውና በተከሣሹ መካከል ያለው ግንኙነት በውል ላይ የተመሠረተ በመሆኑ መድን ሰጪው ሊገደድ የሚችልበት የካሳ መጠን በመድን ውሉ የተመለከተው ነው፡፡



የሰ/መ/ቁ. 22162

ሚያዝያ 09 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች:- መንበረፀሐይ ታደሠ

አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

አቶ አሰግድ ጋሻው

ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች ፡- አፍሪካ ኢንሹራንስ - አልቀረበም ፡፡**

**መልስ ሰጪ ፡- አቶ ብስራት ጉላ -ቀርበዋል፡፡**

<u>**ፍ ር ድ**</u>

በዚህ መዝገብ የቀረበልን ጉዳይ የኢንሹራንስ ጉዳይን የሚመለከት ነው፡፡ ተያይዘው ከቀረቡት ፍርዶችና ሌሎች ሰነዶች ለመረዳት እንደቻልነው የመልስ ሰጪ መኪና በደረሰበት ግጭት ምክንያት ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጪ ስለሆነ የመልስ ሰጪ ኢንሹራንስ ኩባንያ የነበረው ህብረት ባንክ በምትኩ አዲስ መኪና ሰጥቶታል፡፡ ህብረት ባንክ ደግሞ ሂሳቡን ከአሁን አመልካች ከአፍሪካ ኢንሹራንስ ተረክቧል፡፡ የአሁን አመልካች ክፍያውን የፈፀመው ጉዳት ያደረሰው መኪና የመድን ሽፋን ስለነበረው ነው፡፡

ይህ ሁሉ ከተፈፀመ በኋላ የአሁን መልስ ሰጪ መኪናዋ ለቆመችበት ለ112 ቀናት በቀን ብር 250 ሂሳብ ብር 28,000 ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ጉዳቱን ባደረሰው በቢፍቱ ዲንሽ ማህበር ላይ ክስ መሠረተ፡፡ የአፍሪካ ኢንሹራንስም ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር ፍ/ቤቱ ባዘዘው መሠረት በጉዳዩ ላይ ገብቶ ክርክር ቀጠለ፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ቢፍቱ ዲንሽ አ.ማ ለተቋረጠው ገቢ ኃላፊ መሆኑን በመግለፅ አፍሪካ ኢንሹራንስ ብር 28,000 /ሃያ ስምንት ሺህ ብር/ እንዲከፍል ወሰነ፤ ወጪና ኪሣራ የማቅረብ መብት የተጠበቀ ነውም አለ፤ ጉዳዩ በይግባኝ ወደሚቀጥለው ፍርድ ቤት የቀረበ ቢሆንም የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ አልተለወጠም፡፡

የሰበር ማመልከቻ የቀረበው ይህን ውሣኔ ለማስለወጥ ሲሆን የአቤቱታው መሰረተ ሃሳብ የሚከተለው ነው፡ -

1. መልስ ሰጪ በወደመችው መኪና ምትክ ሌላ አዲስ መኪና ያገኙ በመሆኑ ከመኪናው ዋጋ በላይ ተጨማሪ ካሳ መጠየቅ አይገባቸውም፡፡ አመልካች መኪናውን በማስረከብ ሂደት ተሳትፎ ስላልነበረው ጉዳትም ደርሶ ከሆነ ተጠያቂ ሊሆን አይገባውም
2. የአመልካች ግዴታ የሚመነጨው ከውል ግንኙነት በመሆኑ ፍ/ቤቱ ከውል ውጪ /Extra Contractual/ ህግን መሠረት አድርጐ ካሳ ክፈል መባሉ አግባብ አይደለም
3. መኪናዋ ሙሉ በሙሉ በመውደሟ መኪናዋ ብትኖር ኖሮ አገኝ የነበረው ጥቅም ይከፈለኝ የሚለው ጥያቄ ተቀባይነት ያለው አይደለም፣ ክፍያ ዘግይቶም ከሆነ ወለድ ከሚጠይቅ በቀር የተቋረጠ ገቢ ሊጠይቅ አይገባም፡፡

   መልስ ሰጪ ባቀረቡት የአመልካች ቅሬታዎች ላይ የሚከተለውን መልስ ሰጥቷል፡ -

1. ክሱ የቀረበው ጉዳቱ ባደረሰው በቢፍቱ ዲንሽ አ.ማ. በመሆኑ ክሱም ሆነ ውሳኔው ከውል ውጪ ሕግን መሠረት ማድረጉ አግባበ ነው
2. መኪናዋ በመውደሟ ንብረት ማጣት ብቻ ሳይሆን ከንብረቱ የሚገኝ ገቢም በመቋረጡ ኃላፊ የሆነው ወገን ካሣ እንዲከፍል መወሰኑ አገባብ ነው
3. ለመዘግየቱ ምክንያት ሌላ ሦስተኛ ወገን ቢሆንም አመልካች ከኃላፊነት ነፃ ሊሆን አይችልም

ይህ ችሎት ጉዳዩን አግባበነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማዛመድ መርምሮአል፡፡ ዋናው መታየት ያለበት ነጥብም አመልካች የአፍሪካ ኢንሹራንስ ኩባንያ የተጠሪ መኪና ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጪ  በመሆንዋ የተቋረጠውን ገቢ ለመተካት በህግ ይገደዳል ወይስ አይገደድም የሚለው ነው፡፡

ከመዝገቡ ለመረዳት እንደቻልነው የመልስ ሰጪ መኪና ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጪ በመሆንዋ መልስ ሰጪ ከራሱ መድን ሰጪ ከነበረው ከህብረት ኢንሹራንስ ሌላ መኪና ተረክቧል፡፡መልስ ሰጪ ክስ ያቀረበው መኪናዋ በደረሰው አደጋ ምክንያት ከ11/09/96 እስከ 2/13/96 ዓ.ም.ድረስ ለ112 ቀናት በመቆምዋ ሳይገኝ የቀረበው የተጣራ ገቢ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ነው፡፡መልሰ ሰጪው ቀረብኝ የሚለው የተጣራ ገቢ በቀን ብር 250 በድምሩ 28,000 /ሃያ አምስት ሺህ ብር/ ነው፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት



የምሥራቅ ሀረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት መልስ ሰጪ አዲሱን መኪና እስኪረከብ ድረስ የ112 ቀናት ገቢ ስለተቋረጠበት ለዚሁ ጉዳት ቢፍቱ ዲንሽ ኃላፊ ነው ካለ በኋላ አፍሪካ ኢንሹራንስ ከቢፍቱ ዲንሽ ጋር ባለው የመድን ውል መነሻነት ቀረ የተባለውን ብር 28,000 /ሃያ ስምንት ሺህ/ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

ለመልስ ሰጪ ክስ መነሻ የነበረው በመኪናው ላይ የደረሰው ጉዳት በመሆኑ ጉዳዩ ከውል ውጪ ለሚደርስ ኃላፊነት አግባብ ባለው ህግ መሰረት መታየቱ አመልካች እንደሚለው ከህግ ያፈነገጠ አሰራር አይደለም፡፡ አመልካች ከቢፍቱ ዲንሽ ጋር ያለው ግንኙነት በውል ላይ የተመሠረተ ቢሆንም ጉዳት ደረሰብኝ የሚል ሦስተኛ ወገንን በሚመለከት የኃላፊነቱም ሁኔታም ሆነ የግምቱ መጠን በሚመለከት የውል ህግ ብቻ ተፈፃሚ ይሆናል የሚለው ክርክር የሚያስኬድ አይደለም፡፡ ጉዳቱ የደረሰው በውል ግንኙነት ውስጥ ባለመሆኑ የመልስ ሰጭ ጉዳይ በውል ሕግ ብቻ ሊስተናገድ አይችልም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች ኃላፊ የሚሆነው ከቢፍቱ ዲንሽ ጋር በነበረው የመድን ውል መነሻነት በመሆኑ ሊከፍል የሚገደደው የካሣ መጠን በመድን ውሉ በተመለከተው ሁኔታ ውስጥ መሆኑ የሚቀር አይደለም፡፡ በዚህ መሠረት አመልካች በምትክ የተሰጠውን የመኪና ዋጋ ለህብረት ኢንሹራንስ መተካቱ ከውሣኔው ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ኢንሹራንስ ኩባንያው ከዚህ በተጨማሪ በመኪናው መውደም ምክንያት ለደረሰው ጉደት /Consequential loss/ ተጠያቂ አይደለም፡፡ መልስ ሰጪ የደረሰው ኪሣራ በአመልካች ጥፋት ምክንያት የደረሰ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ ይልቁንም መልስ ሰጪ የ112 ቀናት ሂሳብ አስልቶ ያቀረበው የመድን ሽፋን ሰጥቶት የነበረው የሕብረት ኢንሹራንስ መኪናውን ለመተካት 112 ቀናት በመውሰዱ ነው፡፡ በመሆኑም የአሁን አመልካች አፍሪካ ኢንሹራንስ በጉዳት ምክንያት የቀረ ገቢን ለመተካት ግዴታ ስለሌለበት ጥፋት መፈፀሙ የሚያሳይ ማስረጃም ስላልቀረበ መኪናው ለቆመበት 112 ቀናት የቀረውን ገቢ ብር 28,000 /ሃያ ስምንት ሺህ/ ሊከፍል ይገባል ተብሎ መወሰኑ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የምሥራቅ ሀረርጌ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 2073 በ13/10/97 የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁ.20745 በ16/2/98 የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ኡንሹራንስ ኩባንያ የተጠየቀውን የጉዳት ካሳ ብር 28,000 /ሃያ አምስት ሺህ ብር/ ለመልስ ሰጪ ሊከፍል አይገባም ብለናል፡፡

የሰ/መ/ቁ. 16195

*ሚያዚያ 11 ቀን 1999 ዓ.ም*

**ዳኞች፡-** *አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ*

*አቶ አሰግድ ጋሻው*

*አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ*

*ወ/ት ሂሩት መለሠ*

*አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ*

**አመልካች፡-** የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት

**ተጠሪዎች፡-** እነ ልዕልት ተናኘወርቅ ኃ/ሥላሴ

*የቤት አበል ክፍያ - የተወረሰ ቤት - የጠቅላይ ሚ/ር ስልጣን - የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 74(4) - የአስፈፃሚ አካላትን ስልጣን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁ. 4/87 አንቀጽ 11/1/ - አዋጅ ቁ. 47/67 አንቀጽ 21(2)*

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ቤት የተወረሰባቸው በመሆኑ አበል ሊከፈላቸው ይገባል ሲል የሰጠውን ውሣኔ በማፅናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

**ውሣኔ: -** የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚኒስቴር መ/ቤቶችን በበላይነት የመምራትና ስራዎቻቸውንም የመቆጣጠር ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡
2. ሚኒስቴር መ/ቤቶች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የፈፀሙትን ስህተት ማረምና ማስተካከል በጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው፡፡





**ዳኞች፡-** 1. *አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ*
2. *አቶ አሰግድ ጋሻው*
3. *አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ*
4. *ወ/ት ሂሩት መለሠ*
5. *አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ*

**አመልካች፡-** የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት - ነ/ፈጅ ሂሩት አስራት ቀረቡ፡፡

**መልስ ሰጭ፡-** እነ ልዕልት ተናኘወርቅ ኃ/ሥላሴ /6 ሠዎች/ - ጠበቃ አቶ ብስራት ሐመልማል ቀረቡ፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡

ተጠሪዎች ለዚህ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ መንግስት የግል መኖሪያ ቤቶቻቸውንና አከራይተው የነበሩትን ሌሎች ቤቶች ወርሶ እያስተዳደረ በመሆኑና ምንም ገቢ ስላልነበራቸው አበል እንዲከፈላቸው ለሥራና ከተማ ሚ/ር አመልክተው እንዲከፈላቸው የተወሰነ ቢሆንም ተጠሪ አበሉን ለመክፈል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከ1/12/67 - 30/8/87 ያለው ውዝፍ አበልና ወደፊት ያለው አበልም ለዘለቄታው እንዲከፍል እንዲወሠንበት ጠይቀዋል፡፡ ጉዳዩን ያየው ፍ/ቤትም ውዝፍ አበሉ እንዲከፈልና ከክሱ በኂላ ያለው ግን ዳኝነት ያልተከፈለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱን ውሣኔ አፅንቷል፡፡

የአሁን የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታም የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር የሰጠው ውሣኔ በጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ ተሽሯል፣ ተጠሪዎች እስር ቤት በነበሩበት ጊዜ መንግስት ወጪ እያደረገ ያኖራቸው በመሆኑ ተጠሪዎች ውጭ አገር ነዋሪዎች በመሆናቸው ከቤት ኪራይ በቀር ሌላ ገቢ እንደሌላቸው ሣይጣራና ሣይታወቅ የተፈቀደው አበል ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር የሰጠው ውሣኔ በጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ ተሽሮ እያለ የተጠራቀመው የቤት ኪራይ ይከፈል መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት አቤቱታው ለችሎቱ ቀርቦ እንዲታይ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት ተጠሪዎች ቤታቸው በመወረሱ ምክንያት አበል እንዲከፈላቸው ክስ ለማቅረብ የቻሉት የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር አበሉ እንደከፈላቸው የሠጠውን ውሣኔ መሠረት አድርገው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር በአ/ቁ. 47/67 አንቀጽ 21/2/ መሠረት ትርፍ

ቤት የተወረሠበት ቤተሠብ ወይም ግለሠብ ከቤት ኪራይ በስተቀር ለመኖሪያ የሚሆን ሌላ ገቢ የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ በመሥራት ገቢ አስከሚያገኝ ድረስ በየወሩ ለመተዳደሪያ አበል እንዲከፈለው ሊወስን እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በዚህም መሠረት ህጉ የሠጠውን ስልጣን መሠረት አድርጐ የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር ለተጠሪዎች አበል እንደከፈላቸው ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ግን ይህ ውሳኔ በጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ የተሻረ መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ የተጠሪዎች ክርክር የስራና ከተማ ልማት ሚ/ር በአ/ቁ 47/67 የተሰጠውን ስልጣን መሠረት አድርጎ የሠጠውን ውሣኔ የጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ ለመሻር የሚያስችል ስልጣን የለውም የሚል ነው፡፡

ከመዝገቡ የጠቅላይ ሚ/ር ቢሮ የሥራና ከተማ ልማት የሠጠውን ውሣኔ የሻረው በ29/12/87 እንደሆነ ተረድተናል፡፡ በዚህን ወቅት ደግሞ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት ከነሐሴ 15/1987 ጀምሮ ስራ ላይ ውሏል፡፡ በዚህ ህገ-መንግስት አንቀጽ 74/4/ ሁሉም ሚኒስቴሮች የሚገኙበትን የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደሚመራ፣ እንደሚያስተባብርና እንደሚወክል ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም ከነሐሴ 17/1987 ጀምሮ ስራ ላይ በነበረው የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አ/ቁ 4/87 አንቀጽ 11/1/ ሥር እያንዳንዱ ሚኒስትር፣ የሚመራውን ሚኒስቴር መ/ቤት የሚመለከቱ ሥራዎች ፕሮግራሞችና ህጎች አፈፃፀም ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስቴሮች ምክር ቤት መሆኑ ተገልጿል፡፡ ከነዚህ ህጎች አኳያ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚኒስቴር መ/ቤቶችን በበላይነት የመመራትና ስራቸውንም የመቆጣጠር ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በመሆኑም ሚኒስቴር መ/ቤቶቹ ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የፈፀሙትን ስህተት ማረምና ማስተካከል በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣን ስር የሚወድቅ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይም የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ለተጠሪዎች አበል እንዲከፈል የሠጠው ውሣኔ አግባብ ሆኖ ባለመገኘቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ውሣኔው መሻሩ ከስልጣኑ ውጪ ነው የሚያሠኝ አይሆንም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም በአ/ቁ 47/67 ሥር የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የሚሰጠውን ውሣኔ የጠቅላይ ሚኒስቴር ሊሽር፣ ሊያሻሽል ወይም ሊለውጥ የሚያስችለው ስልጣን በግልጽ አልተመለከተም በማለት ብቻ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ያለውን አጠቃላይ ስልጣን ከግንዛቤ ባለመክተት ውሣኔው የተሻረው ስልጣን በሌለው አካል ስለሆነ ውጤት የለውም ማለታቸው የህግ ስህተት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሆኑም ምንም እንኳን አበል ለተጠሪዎች እንዲከፈል ሥልጣን የነበረው አካል ወስኖ የነበረ ቢሆንም ይኸው ውሣኔ ሥልጣን ባለው የበላይ አካል የተሻረ በመሆኑ ተጠሪዎች አበል እንዲከፈላቸው የተሰጣቸውን መብት አጥተዋል፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቶቹ አበሉ እንዲከፈል መወሠናቸው የህግ ስህተት ነው፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 03721 በ27/05/95 እና በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 18942 በ8/8/96 የተሰጡት ውሣኔዎች ተሰሯል፡፡
2. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
3. ከሥር ፍ/ቤት የመጣው መዝገብ ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡



የሰ/መ/ቁ. 23339

መጋቢት 13 ቀን 1999 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አቶ ከማል በድሪ
አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
አቶ ጌታቸው ምህረቱ
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

**አመልካች፡-** የኢት.ጉምሩክ ባለስልጣን

**ተጠሪ፡-** እነ አቶ አበሮ ኢርጋኖ

*የመንግሥት ሰራተኞች የስራ ክርክር - የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤት ስልጣን - የጉምሩክ ሰራተኞችን አስተዳደር በተመለከተ የገቢዎች ሚኒስትር የሚያወጣው መመሪያ - አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀጽ 6/2/ለ*

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍርድ ቤት የተጠሪዎቹን ክርክር ተቀብሎ ያስተናግድ ሲል የወሰነውን ውሣኔ በመቃወም የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

**ውሣኔ: -** የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

የጉምሩክ ሰራተኞች የመንግሥት ሰራተኞች ቢሆኑም ከሌሎች የፌዴራል መ/ቤቶች ተለይተው የሚተዳደሩት የገቢዎች ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ እንጂ በፌዴራል መንግሥት ሰራተኞች አዋጅ ቁ. 262/1994 አይደለም፡፡

የሰ/መ/ቁ. 23339

13/7 ቀን 1999 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ ከማል በድሪ

2. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ

3. አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ

4. አቶ ጌታቸው ምህረቱ

5. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

አመልካች፡- የኢት.ጉምሩክ ባለስልጣን

ተጠሪ፡- እነ አቶ አበሮ ኢርጋኖ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፣

**ፍ ር ድ፣**

መዝገቡ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የአሁኑ አመልካች የካቲት 20 ቀን 1998 ጽፎ ባቀረበው የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡ ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ክርክር የተጀመረው የአሁኖቹ ተጠሪዎች የአመልካች ድርጅት ሠራተኞች የነበሩ መሆናቸውን ገልፀው ጊዜው ያለፈ ይግባኝ ለማቅረብ እንዲፈቀድላቸው ለፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍ/ቤት የይግባኝ ማስፈቀጃ በማቅረባቸው ነው፡፡ የኮሚሽኑ ፍ/ቤት የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ አመልካችን ሳይጠራ የአስተዳደር ፍ/ቤቱ የቀረበውን አቤቱታ ተቀብሎ ለመወሰን ሥልጣን የሌለው መሆኑን በመግለጽ ብይን ሰጥቷል፡፡ የተሰጠው ብይን በመቃወም ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቀርቦ ፍ/ቤቱ ታህሣሥ 12 ቀን 1998 በዋለው ችሎት የፌ/ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍ/ቤት የሰጠውን ብይን በመሻር ይግባኙ ሊፈቀድ ይገባል አይገባም የሚለውን አከራክሮ እንዲወስን በማዘዝ ጉዳዩን ወደ አስተዳደር ፍ/ቤት መልሶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ የቀረበው በዚሁ ነጥብ ላይ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች በሰበር ቅሬታ ማመልከቻው ላይ እንደገለፀው፣ በአዋጅ ቁጥር 368/95 አንቀጽ 6/2/ /ለ/ መሠረት የባለሥልጣኑ መ/ቤት ሠራተኞች ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚተዳደር መሆኑ እየታወቀና፣ የገቢዎች ሚኒስቴርም የባለሥልጣኑን ሠራተኞች አስተዳደር አስመልክቶ ቁ.01/22/41/3 በ23/02/98 የሠራተኞች አስተዳደር አጠቃላይ መመሪያ አውጥቶ እና በሥራ ላይ አውለው እያለ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የአመልካች መ/ቤት ሠራተኞች የሥራ ክርክር በፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ይታይ ማለቱ የህግ ሥህተት ያለበት ነው ብለዋል፡፡

ጉዳዩ ለሰበር ይቀርባል ተብሎ የግራ ቀኙ ክርክር ሰኔ 5 ቀን 1998 ተሰምቷል፡፡ በዚህ ጉዳይ በዋነኛነት የተያዘው ጭብጥ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ሠራተኞች



የሆኑት የተጠሪዎች ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 262/94 መስተናገድ ይገባዋል ወይስ አይገባውም? የሚለው ይሆናል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 368/1995 በአንቀጽ 6/2/ /ለ/ መሠረት "የፌዴራል መንግስት አዋጅ ቁጥር 262/1994 ቢኖርም እንኳን የባለሥልጣኑ ሠራተኞች አስተዳደር ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡" በማለት የደነገገ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህንንም ተከትሎ በገቢዎች ቦርድ የሠራተኞቹን አስተዳደር በሚመለከት መመሪያ ወጥቶ ከጥቅምት 23 ቀን 1996 ጀምሮ በሥራ ላይ መዋሉ ተረጋግጧል፡፡ ይህ በዚህ ሁኔታ ተከናውኖ እያለ የሥር ፍ/ቤት "---የባለስልጣኑን ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል የሚለው ቢተረጐም ስለሠራተኞቹ አስተዳደር ነክ ጉዳዮችን የሚመለከት መመሪያ ይሆን እንደሆን እንጂ በሠራተኞቹ በኩል የሚኖረው የዳኝነት ጥያቄ የት ቦታ? በማን ይታይ? የሚለውን በመመሪያ ሊወሰን ይችላል የሚል ትርጉም ሊሰጥ አይችልም፡፡" በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ከህጉ ዓላማና መንፈስ የራቀ ትርጉም የተሰጠበት መሆኑን ያመለክታል፡፡ የአመልካች መ/ቤት የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት መሆኑ ቢታወቅም፣ ሕግ አውጭው የአመልካች መ/ቤት ከሚያከናውናቸው ተግባራት አኳያ ከሌሎቹ የፌዴራል መ/ቤቶች ተለይቶ እንዲተዳደር በአዋጅ በግልጽ አመላክቶ እያለ የሥር ፍ/ቤቱ የባለሥልጣኑ ሠራተኞች አስተዳደርን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል የሚለው የሠራተኞቹን አስተዳደር ነክ ጉዳዮች ብቻ በመመሪያው መሠረት ይታያሉ በማለት የሰጠው ትርጉም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

- የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት የፌዴራሉ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አስተዳደር ፍ/ቤት የአሁኖቹን ተጠሪዎች ክርክር ተቀብሎ ያስተናግድ በማለት ታህሣሥ 12 ቀን 1998 ዓ.ም በወ/ይ/መ/ቁ. 20709 የሠጠው ውሳኔ ተሽሯል፣
- የዚህን ፍ/ቤት ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፣
- መዝገቡ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰ/መ/ቁ. 22317

ሚያዚያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ

አቶ አሰግድ ጋሻው

አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

ወ/ት ሂሩት መለሠ

አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

**አመልካች፡-** በምስራቅ ቀጠና ጉምሩክ የሐረር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ

**ተጠሪ፡-** አቶ አብዲ አሊ ሳዬ

*የጉምሩክ ክርክር - ኮንትሮባንድ - የተቋረጠ ጥቅም ክፍያ - አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 5 - 6 የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2010/2/*

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የኦሮሚያ ም/ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የ393 ቀናት የተቋረጠ ገቢ ለተጠሪ እንዲከፍልና መኪናውን ወይም ዋጋውን ብር 50000 እንዲተካ የሰጠውን ውሳኔ በማፅናቱ በተቃውሞ የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

**ውሣኔ፡ -** የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የኦሮሚያ ም/ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

1. የጉምሩክ ባለሥልጣን በኮንትሮባንድ ወደ አገር የሚገቡትን ወይም ከአገር የሚወጡትን እቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠር፣ የሚንቀሳቀሱ እቃዎችንና ማጓጓዣዎችን የመያዝና አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡
2. የጉምሩክ ባለሥልጣን በሕገ ወጥ መንገድ መገልገያ የሆኑ መጓጓዣዎችን ጭምር ይዞ ለምርመራ በጥበቃ ሥር ለማቆየት ግልፅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡
3. የመንግሥት መ/ቤት ባለሥልጣን ራሱ የመረመራቸውን ሰነዶች ቃላት መቃወም የሚቻለው ዳኞች በተለይ ከፈቀዱ ብቻ ነው፡፡



የሰ/መ/ቁ. 22317

ሚያዚያ 18 ቀን 1999 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሠ

2. አቶ አሰግድ ጋሻው

3. አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ

4. ወ/ት ሂሩት መለሠ

5. አቶ ተሻገር ገ/ስላሴ

**አመልካች፡-** በምስራቅ ቀጠና ጉምሩክ የሐረር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ - ነ/ፈጅ አቶ ጕሳዬ ነጋሽ ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ አብዲ አሊ ሳዬ - ቀረበ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

መዝገቡ ለሠበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የአሁኑ አመልካች በ12/4/98 ጽፎ ባቀረበው የሰበር ቅሬታ ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ የአሁኑ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረበው ክስ የአሁኑ አመልካች የኮንትሮባንድ ዕቃ ሳልጭን ጭነሀል በማለት መኪናዬን ከሕግ ውጭ ይዞ ስላቆመብኝ በቀን አገኘው የነበረው ገቢ ብር 250 /ሁለት መቶ ሀምሳ/ ብር በ150 ቀኖች ተባዝቶ የአሁን አመልካች ብር 37,500 /ሰላሣ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ብር/ እንዲከፍለው በተጨማሪም የመኪናውን ዋጋ ብር 50,000 ወይም መኪናውን እንዲያስረክበው ጠይቋል፡፡ የሥር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር አድምጦ ጥር 27 ቀን 1997 በዋለው ችሎት የአሁኑ አመልካች የ393 ቀናት የተቋረጠ ገቢ ለተጠሪ እንዲከፍልና መኪናውን ወይም ዋጋውን ብር 50,000 እንዲተካ ታዟል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት መኪናው በመያዙ ምክንያት የአሁኑ ተጠሪ ጠይቆ የነበረው የተቋረጠ ገቢ የ150 ቀናት ብቻ ሆኖ እያለ የሥር ፍ/ቤት የ393 ቀናት መወሰኑ ትክክል ባይሆንም ይግባኝ ባይ በዚህ በኩል ያቀረበው አቤቱታ ስለሌለ ታልፏል ብሎ የይግባኝ መዝገቡን ዘግቶ መልሶታል፡፡

ይህ ችሎት ሚያዚያ 2 ቀን 1998 ዓ.ም. መዝገቡ ለሰበር ይቀርባል በማለት ወስኖ ጉዳዩን ለመስማት በተያዘው ቀጠሮ ተጠሪን አግኝቶ መጥሪያውን ማድረስ ያልቻለ መሆኑን አመልካች በመግለፁ ይህ ችሎት ግንቦት 2 ቀን 1998 ዓ.ም. ተጠሪ የጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግለት ታዟል፡፡የአሁኑ ተጠሪ ሰኔ 28 ቀን 1998 ሆነ በሚቀጥሉት ቀናት ባለመቅረቡ ፍ/ቤቱ በሌለበት እንዲታይ ብይን ሰጥቷል፡፡

በዚህ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤቶች የአሁኑ አመልካች ለተጠሪ የተቋረጠ ገቢ ኃላፊ ነው ለማለት መሠረት ያደረጉት ምክንያት የአሁኑ አመልካች

የኮንትሮባንድ ዕቃ ዝርዝር የሚያሳያ የጽሁፍ ማስረጃ ቢያቀርብም የተባሉት ዕቃዎች ከተጠሪ መኪና ላይ መያዙን አይገልጽም፤ አመልካች ለሕግ ተቃራኒ በሆነ መንገድ መኪናውን ይዞ በቁጥጥር ስር ማዋሉ ደግሞ ተጠሪን ሆነ ብሎ ለመጉዳት ነው በሚል መደምደሚያ እንደነበር ይህ ችሎት ተረድቶታል፡፡ በዚህ መሠረት ይህ ችሎት የተጠሪ መኪና ለህግ ተቃራኒ በሆነ መንገድ ተይዟል ተብሎ የአሁኑ አመልካች በውሳኔው የተመለከተውን ገንዘብ ይከፈል መባሉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ይህ ችሎት መርምሯል፡፡

አዋጅ ቁጥር 60/89 የጉምሩክ ባለሥልጣንን እንደገና ለማቋቋምና አሰራሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ነው፡፡ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 6 ላይ የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባር በዝርዝር የተመለከተ ሲሆን በተለይ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለውን ንዑስ ቁጥር 5 ስንመለከት በኮንትሮባንድ ወደ አገር የሚገቡትን ወይም ከአገር የሚወጡትን ዕቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠር፣ የሚንቀሳቀሱ፣ እቃዎችንና ማጓጓዣዎችን የመያዝና አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ስልጣን የተሰጠው መሆኑ ተገልጿል፡፡ አመልካች በዚህ በተሰጠው ሥልጣን ተጠቅሞ በኮንትሮባንድ ወንጀል ተግባር ይዞ በቁጥጥር ሥር ባቆየው መኪና ላይ በገቢ ዕቃ መመዝገቢያ ሞዴል ላይ የተሞላውን ዝርዝር የኮንትሮባንድ ዕቃ በሰነድ ማስረጃነት አያይዞ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት የቀረቡት የገቢ መመዝገቢያ ሞዴሎችን ሕጋዊነት የተቀበለ ቢሆንም በመቀጠል ግን ማስረጃው የዕቃዎች ዝርዝር የሚገልጽ እንጂ ዕቃው በከሳሽ መኪና ላይ መያዙን አይገልጽም ብቻ በማለት ውድቅ ማድረጉ ከማስረጃ ሕግ ዓላማና በፍ/ሕ/ቁ. 2010/2/ መሠረት በባለስልጣን ስለተረጋገጡ ሠነዶች ተቀባይነት የሚደረገውን ሕግ የሚጥስ አካሄድ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአሁን አመልካች በአዋጁ አንቀጽ 58/1/ /ለ/ መሠረት በሕገወጥ መንገድ መገልገያ የሆኑ መጓጓዣዎችን ጭምር ይዞ ለምርመራ በጥበቃ ሥር ለማቆየት ግልጽ ሥልጣን ተሰጥቶት እያለ የሥር ፍ/ቤት የተያዘ የኮንትሮባንድ ዕቃ ዝርዝር የቀረበ መሆኑን ተቀብሎ ከአሁኑ ተጠሪ መኪና ላይ ስለመያዙ ማስረጃ አልቀረበም በሚል የተቋረጠ ገቢ ይክፈል ብሎ ማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ብለናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

የአሁኑ አመልካች በሕግ አግባብ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ተግባሩ ሲወጣ ይዞ ላቆየው ተሽከርካሪ የተቋረጠው ገቢ ይክፈል በማለት የምስራቅ ሐረርጌ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 271/96 በ22/04/97 እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 25132 በ15/3/98 የሰጡትን የውሳኔ ክፍሎች ሽረናል፤ የአሁኑ አመልካች መኪናውን ለተጠሪ ያስረክብ ብለን የሥር ፍ/ቤት ውሳኔዎች አሻሽለን ወስነናል፤

መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡



የሰበር መ/ቁ. 12025

መጋቢት 18/1999

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ አሰግድ ጋሻው
አቶ መስፍን ዕቁበዮናስ
ወ/ት ሂሩት መለሠ
አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- አቶ ምናሴ አልማው

መልስ ሰጪ፡- ዐቃቤ ሕግ

*የወንጀል ጉዳይ ክርክር - ማታለል - የጥብቅና ፈቃድ ከተሰረዘ በኋላ የጥብቅና ስራ እሰራለሁ ብሎ ገንዘብ መቀበል - የመከላከል መብት - የ1949 ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁ. 656(ሀ) ና (ለ)*

አመልካች በቤንሻንጉል ጉምዝ ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የህግ ስህተት ያለበት ነው በሚል የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

__ውሣኔ: -__ የቤንሻንጉል ጉምዝ ከፍተኛና ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ጸንቷል፡፡

1. የጥብቅና ፈቃድ ከተሰረዘ በኋላ ጉዳይ አስፈጽማለሁ ብሎ ገንዘብ መቀበል የማታለል ወንጀል ነው፡፡
2. የመከላከል መብት ህገ-መንግሥታዊ መብት ነው፡፡

የሰበር መ/ቁ. 12025

መጋቢት 18/1999

ዳኞች፡- 1. መንበረፀሐይ ታደሰ

2. አሰግድ ጋሻው

3. መስፍን ዕቁበዮናስ

4. ሂሩት መለሠ

5. ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- አቶ ምናሴ አልማው አልቀረቡም

መልስ ሰጪ፡- ዐቃቤ ሕግ አልቀረበም

## ፍ ር ድ

ይህ መዝገብ ለሰበር ችሎት የቀረበው አመልካች በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ የሕግ ስህተት መኖሩን በሚያመለክት ሁኔታ የተሰጠ በመሆኑ ውሣኔዎቹ ይሻሩልኝ ሲል በማመልከቱ ነው፡፡

ይህ ፍርድ ቤት የአመልካችን አቤቱታ ከስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔዎች እንዲሁም በዚህ ፍርድ ቤት ከተደረገው የጽሑፍ ክርክርና አግባብነት ካላቸው ሌሎች ሕጐች ጋር በማገናዘብ መርምሮአል፡፡

በዚህም መሠረት አመልካች የተከሰሰውና ጥፋተኛ የተባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 656(ሀ) እና (ለ)ን በመተላለፍ ሲሆን ለፍርድ ቤቶቹ ውሣኔ ምክንያት የሆነው አመልካች የጥብቅና ፈቃድ ሣይኖረው የጥብቅና ፈቃድ ያለው በማስመሰል የግል ተበዳዮችን ጉዳይ አስፈጽምላችኋለሁ በማለት ብር 3830 (ሶስት ሺህ ሦስት መቶ ሰላሣ) መወሰዱ በመረጋገጡ ነው፡፡ አመልካች በዚህ ችሎት ማስረጃ አልቀረበብኝም ቢልም የስር ፍርድ ቤቶች በቂ ማስረጃ ቀርቦበት የወሰኑ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ይልቁንም አመልካች ቀደም



ሲል ተሰጥቶት የነበረው የጥብቅና ፈቃድ መሠረዙ ከተገለፀለት በኋላ ይህን ድርጊት መፈፀሙ በማስረጃ ተረጋግጦበታል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች የመከላከል መብቴ አልተጠበቀልኝም ቢልም ተደጋጋሚ እድል ተሰጥቶት የመከላከያ ማስረጃውን ሊያቀርብ አለመቻሉ ከመዝገቡ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ተከሣሹ የመከላከል መብቱ ሕገመንግሥታዊ መብት መሆኑ ባያከራክርም ተከሣሽ በሆነበት ጉዳይ ላይ በተገቢው አጭር ጊዜ ውስጥ የመከላከያ ማስረጃ ካለው እንዲያቀርብ ፍርድ ቤቶች ተደጋጋሚ ቀጠሮ ቢሰጡም አመልካቹ እድሉን ባለመጠቀሙ ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ሕግ መንግሥታዊ መብት ጣሱ ሊያሰኛቸው አይችልም፡፡ በመሆኑም አመልካች በስር ፍርድ ቤት የቀረበበት ክስ በበቂ ማስረጃ የተረጋገጠበት በመሆኑና የተጣለበት የሁለት ዓመት ቅጣትም ሕጉ በሚያዘው ክልል ውስጥ በመሆኑ ሂደቱም ሆነ ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን የሚያሣይ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## ው ሣ ኔ

(1) በዚህ ጉዳይ የቀረበው የሰበር ማመልከቻ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

(2) የቤንሻጉል ጉምዝ የከፍተኛና የጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ፀንቷል፡፡